ጅማ ዩኒቨርስቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል


ድሕረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የምትሃታዊ እውነታዊነት ባህርያት በ"ኤጭ…!" ልቦለድ ማሳያነት

ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት


በ

ወንድዬ ካሳ



2013 ዓ.ም

ጅማ

ጅማ ዩኒቨርስቲ
የሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ አማርኛ
ትምህርት ክፍል

# የምትሃታዊ እውነታዊነት ጥቁር አስማት ባህርያት
# በኤጭ…! ልቦለድ ማሳያነት

በ
ወንድዬ ካሳ

| አማካሪዎች | ፊርማ |
|---|---|
| ማንያለው አባተ (ዶ/ር) | _______________ |
| የውስጥ ፈታኝ | _______________ |
| የውጪ ፈታኝ | _______________ |

# ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ

# ማሟያነት ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች ከፊል ማሟያነት

# የቀረበ ጥናት

በ

ወንድዬ ካሳ

አማካሪዎች

ዶክተር ማንያለው አባተ (ዋና አማካሪ)

አቶ ሀብታሙ እንግዳው (ረዳት አማካሪ)

ጅማ ዩኒቨርስቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድሕረ ምረቃ መርሃ ግብር

2013 ዓ.ም

ጅማ

# ምስጋና

ሁሉም ነገር የሆነው በልዑል እግዚአብሔር ፍቃድ ነውና እዚህ ያደረስከኝ እኔ ማነኝ? በሚል ስለ ፈጣሪ ድንቅ ችሮታ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ እውቀት በማስጨበጥና በማስተማር ጎዶሎዬን ከመሙላት ባለፈ የመመረቂያ ወረቀቴን ያለመታከት በማረም ለደከማችሁ መምህሮቼ ለዶ/ር ማንያለው አባተ እና ለዶ/ር ለማ ንጋቱ ፈጣሪ እድሜ ዘመናችሁን ይባርክልኝ ብያለሁ፡፡ በኔ የመማር ብርታት ውስጥ ባለቤቴ መስታወት ጌታቸው እና ልጄ ሔኖን ወንድዬ የከፈላችሁት ዋጋ ከፍ ያለ ነውና ይህ ውጤት ለናንተ የተበረከተ ሆኗል፡፡ ውድ ጓደኞቼ ያለመሰልቸት ያደረጋችሁልኝንና ምንጊዜም ከጎኔ መሆናችሁን ሳስብ የሰው ልጅ ሀብቱ ገንዘብ ሳይሆን ሰው መሆኑን እንድመሰክር አድርጋችሁኛልና ምንም እንኳን ስማችሁን ዘርዝሬ ምስጋና ለማድረስ ባይቻለኝም ሁሉን ማድረግ የማይሳነው ፈጣሪ ብድሩን ይክፈላችሁ ስል በክብር ነው፡፡ እህትና ወንድሞቼ በተለይ ገነት ገብሬ በኔ ጉዳይ ቀድሞ መገኘት ግዴታችሁ ቢሆንም እናንተ ግን ከዚህ በላይ ሆናችሁ ተገኝታችኋልና ፈጣሪ ጸጋና በረከቱን ያብዛላችሁ፡፡ ከቃላት እርምት ጀምሮ ይህ ጥናት ከዳር እንዲደርስ ያለመታከት ለደከምከውና ሙያዊ ምክር በመለገስ ለደከምከው መምህር ኪዳኔ ደበበ ምስጋናዬ ይድረስህ ከማለት ባሻገር ፈጣሪ እንዳንተ አይነት ቅን አሳቢዎችን አይንሳን በማለት ነው፡፡ ከመፅሃፍ ግዢ በላይ ቀለብ ሸመታ በበዛበት በዚህ ዘመን ያለስስት መጽሃፍ ገዝተህ ያለስስት የፈለኩትን መጽሃፍ በማዋስ የትምህርት ቆይታዬ የተሳካ እንዲሆን አድርገሃልና ገዛኸኝ አስገዶም እነሆ ምስጋናዬ ይድረስህ፡፡

# አጠቃሎ

ስነጽሁፍ ስለ ሕይወትና ተፈጥሮ ያለንን ዕውቀት ከማስፋቱም በላይ አካባቢያችንና ማህበረሰባችንን እንድንረዳ ያደርገናል፡፡ ስነጽሁፍ በዘመን መንፈስ ውስጥ የራሱን ጭብጥ እየያዘ እራሱንም በተለያዩ የአጻጻፍ ስልቶች እያሳደገ የማህበረሰቡ ተጨባጭ ሕይወትና ኑሮ መልሶ ለማህበረሰቡ ያቀርባል፡፡ በጊዜ ሂደት የስነጽሁፍ ጭብጥ ማጠንጠኛ ዘውግ መሆን ከቻሉ ስልቶች መካከል ምትሃታዊ እውነታዊነት አንዱ በመሆን ይጠቀሳል፡፡ በላቲን አሜሪካ በ Roh (1927) የተጀመረው ምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ በረቂቅ ስዕልነት ሲተገበር ቆይቶ ወደ ስነጽሁፋዊ ጭብጥ ማጠንጠኛነት ተሸጋግሯል፡፡ ምትሃታዊ እውነታዊነት በሀገራችን የቀደመ ታሪክ ቢኖረውም ለስነጽሁፍ ጭብጥ ማጠንጠኛነት ሲውል ግን አይታይም፡፡ ዘርፉ ትኩረት እያገኘ መምጣቱን ግን በቅረቡ ለንባብ ከበቁት ክቡር ድንጋይ፣ የኦጋዴን ድመቶችና ኤጭ…! ልቦለድ መጻህፍቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በዚሁ ረገድ ኤጭ…! ልቦለድ በምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፋዊ ዘውግ በመቅረብ በጥንቁልና አማካኝነት እየደረሰ ያለውን ማህበረሰባዊ ተጽዕኖ አመልክቶናል፡፡ ይህ ጥናት መጽሃፉ በምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፋዊ ዘውግ ተዘጋጅቶ የቀረበ መሆኑን ከመጽሃፉ በተሰበሰቡ መረጃዎች አማካኝነት በትንተና ማሳየት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የጥናቱ ውጤት ከንድፈ ሃሳብ ባህርያት አንጻር የተመረጠው ልቦለድ በምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ መቅረቡን፣ ምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ የስነጽሁፍ ጭብጥ ማጠንጠኛ ሆኖ ሲቀርብ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው መመልከት ተችሏል፡፡ ይህ ጥናት በምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፍ ዘውግ መቅረቡን ለማመልከት ተያያዥ የሆኑ ጽንሰ ሃሳቦች፣ ንድፈ ሃሳቦችና ዘውጎች ከመጽሃፉ ተሰብስበው በተደራጁ መረጃዎች አማካኝነት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## ሙዳየ ቃላት

ምትሃት - እንደ ሕልም እንደ ጥላ ታይቶ የሚጠፋ ጋኔን፣ ሰይጣን፤ እርኩስ መንፈስ፡፡

መተት - አዚም፣ ድግምት፣ አስማት፣ አፍዝ አደንግዝ፣ በሰው ላይ ጉዳት ለማድረስ በልብስ፣ በቁሳቁስ፣ በእንሰሳትና በሌሎች ነገሮች ላይ የሚደረግ ድግምት፡፡

ድግምት - የተደገመ፣ ድጋም፣ አስማት፡፡

ጥንቁልና - መጻፍ፣ ትንቢት መናገር፣ በአስማት ጠጠር መጣል፣ ይህ ይሆናል ብሎ መናገር፣ በመተት አስደናቂ ትዕይንት የመፈጸም ተግባር፡፡

ጠልሰም - ጠለሳም፣ ባለጠለስ፣ በያይነቱ የአስማት ስዕል ለራስ ምታት፣ ለሆድ ቁርጠት፣ በክታብ ውስጥ ጠንቋዮች የሚስሉት፣ እስላሞች ባንገታቸው የሚያደርጉት የብር ወይም የወርቅ አሸንክታብ፡፡

ጥንዳዊ ተቃርኖ - አንዱ ሌላውን የሚቃረንበት አግባብ፡፡

ነጭ አስማት - ሰዎችን የማይጎዳና ሰዎች ከገቡበት ችግር እንዲወጡ የሚረዳ የአስማት አይነት፡፡

ጥቁር አስማት - ሰዎችን ለመግደልና ለመጉዳት የሚደረግ የአስማት አይነት፡፡

ማውጫ ገጽ


ምስጋና ..... i
አጠቃሎ ..... ii
ምዕራፍ አንድ ..... 1
መግቢያ ..... 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ..... 2
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ..... 5
1.3. የምርምር ጥያቄዎች ..... 6
1.4. የጥናቱ ዓላማ ..... 6
1.4.1. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎ ..... 6
1.4.2. ይህ ጥናት ተከታዮቹ ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡ ..... 6
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ..... 7
1.6. የጥናቱ ወሰን ..... 7
ክለሳ ድርሳናት ..... 8
2.1. ጽንሰ ሃሳባዊ ቅኝት ..... 8
2.1.1. ምትሃት ምንድነው ? ..... 8
2.1.2. የምትሃት አጀማመር ..... 9
2.1.3. ምትሃታዊ እውነታዊነትና ስነጽሁፍ ..... 10
2.1.4. የምትሃት አይነቶች ..... 12
2.1.5. ምትሃታዊ እውነታዊነት ከሌሎች ዘውጎች ጋር ያለው ግንኙነት ..... 13
2.2. የምትሃታዊ እውነታዊነት ባህርያት /Character of magic realism/ ..... 15
2.2.1. ሊታመኑ የማይችሉ ድርጊቶችና ገጸባህርያት ..... 15
2.2.2. መቀላቀል ..... 16
2.2.3. የደራሲው ገለልተኛነት ..... 16
2.2.4. ጥንዳዊ ተቃርኖ ..... 16
2.2.5. ሚስጢራዊነት ..... 16

2.2.6. የፖለቲካ ትችት........16
2.3. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት........17
2.3.1. ቀዳማይ ንድፈ ሃሳብ........17
2.3.2. ድህረ ዘመናዊ ንድፈ ሃሳብ........17
2.4. ዘመናዊነትና ማህበራዊ ሒስ........18
2.4.1. ዘመናዊነት........18
2.4.2. ከወቅቱ ጋር አብሮ መዘመን........18
2.4.3. ዘመናዊ አስተሳሰብ........18
2.5. የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት........19
ምዕራፍ ሦስት........22
የጥናቱ ስነ ዘዴና ንድፍ........22
3.1. የመረጃ ምንጭና አመራረጥ........22
3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ........22
3.3. የመረጃ አደረጃጀትና መተንተኛ ስልት........23
3.3.1. የመረጃ አደረጃጀት........23
3.3.2. የመረጃ መተንተኛ ስልት........23
ምዕራፍ አራት........24
የመረጃ ትንተና........24
4.1.1. ሊታመኑ የማይችሉ ድርጊቶችና ገጸባህርያት........25
4.1.2. መቀላቀል ወይም ድብልቅነት /Hybridity/........30
4.1.3. የደራሲው ገለልተኛነት እና ተጨባጭ ማስረጃ አለማቅረብ........33
4.1.4. ጥንዳዊ ተቃርኖ /Binery opposition/........37
4.1.5. ምስጢራዊነት........39
4.1.6. የፖለቲካ ትችት /poltical critique/........43
4.2. ድሕረ ዘመናዊያን ምድፈ ሃሳብ........47

4.3. ዘመናዊነትና ማህበራዊ ሒስ ....................................................................50

4.3.1. ዘመናዊነት /Modernity……………………………………………………...52

4.3.2. ወቅትን የተከተለ ዘመናዊነት /Modernization/………………………………..53

4.3.3. ዘመናዊ አስተሳሰብ /Modernism/……………………………………………..55

4.5. የምትሃታዊ እውነታዊነት ጭብጥ ለልቦለድ ያለው አስተዋጽኦ ..........................56

4.5.1. ማህበረሰባዊ ችግሮችን ነቅሶ ለማሳየት ይረዳል…………………………………56

4.5.2. የአፃፃፍ ስልት ልዩነት ለማምጣት ያገለግላል…………………………………...56

5.1. ማጠቃለያ................................................................................................................58

5.2. አስተያየት ..........................................................................................................59

ዋቢ ጽሁፎች...............................................................................................................60

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ስነጽሁፍ የሰውን ሀዘንና ደስታ፣ ጥላቻና ፍቅር፣ ድልና ሽንፈት፣ ምቾትና ጉስቁልና፣ ውድቀት ብልጽግና፣ ህይወትና ሞት እንዲሁም ሰናይና እኩይ ባህርያቱንና ሌሎችንም የሕይወት ገጽታዎቹን ለማሳየት አቅም አለው (ዘሪሁን 2009)፡፡

ስነጽሁፍ ከሌሎች ሙያዎች በላቀ ከሰው ልጅ ሕልውና ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ከማጀት እስከ አደባባይ ከምድር እስከ ሰማይ አይመለከተኝም የሚለው አንድም የኑሮ ፈርጅ የለም (ቴዎድሮስ 2001)፡፡

ስነጽሁፍ ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እራሱን ከተለያዩ ንድፈ ሃሳቦች ጋር እያስማማ በመጓዙ ዛሬ ላይ በስነጽሁፍ ውስጥ የተለያዩ ርዕዮተ ዓለሞችንና የአጻጻፍ ቴክኒኮችን ለመግለጽ እንዲሁም ለመተንተን ተመራጭ ዘዴ ሊሆን መብቃቱን Carpentier (1949) ያስረዳል፡፡

ይህ ጥናት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ትኩረት እያገኙ ከመጡ ስነጽሁፋዊ ዘውጎች ውስጥ አንዱ በሆነው በምትሃታዊ እውነታዊነት /Magic realism/ ላይ ተንተርሶ አዘርግ (2010) በጻፈው "ኤጭ…!" ልቦለድ መጽሃፍ ላይ ትኩረት አድርጎ የቀረበ ነው፡፡

በዚሁ መነሻነት ምትሃታዊ እውነታዊነት ምንድነው? የምትሃታዊ እውነታዊነት ንድፈ ሃሳቦች እና ጽንሰ ሃሳቦች እንዴት ይታያሉ? በተጠቀሰው ልቦለድ ውስጥ የምትሃታዊ እውነታዊነት አሉታዊ የስነጽሁፍ ጭብጥ ማሳያዎች ምን አይነት ትርጓሜ አላቸው? ጥቁር አስማት በግለሰብ፣ በማህበረሰብና በሀገር አቀፍ ደረጃ ምን አይነት ጉዳት እያደረሰ ነው? በሚል በቀረበው ልቦለድ ውስጥ የምትሃታዊ እውነታዊነት ጥቁር አስማት መረጃዎችን በመምረጥ ማሳያ አድርጎ በትንታኔ አቅርቧል፡፡

ጥናቱ ተዋረዳዊ ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ አምስት ምዕራፎች አሉት፡፡ በመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የምርምር ጥያቄ፣ የጥናቱ ዋና ዓላማ እና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰንና የጥናቱ ውስንነት ይዟል፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ክለሳ ድርሳናት መረጃዎችን ለመተንተን የሚያስችሉ ትወራዊ ማዕቀፎችና ጽንሰ ሃሳቦች

እንዲሁም ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች ተመሳስሎና ልዩነት ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ ሦስት የጥናቱ ስነ ዘዴ፣ የጥናቱ ንድፍ፣ የናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ፣ የመረጃ አደራጃጀትና መተንተኛ ስልት የቀረበ ሲሆን በምዕራፍ አራት ደግሞ የተሰበሰበው መረጃ በትኩረት ተተንትኗል፡፡ በምዕራፍ አምስትና በመጨረሻው ክፍል ማጠቃለያና የመደምደሚያ ሃሳብ ተካቷል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ እየጎለበተ ቢመጣም የምትሃት ጥበብ ግን ከእምነት ስርአቶች ጋር የተያያዘና የራሱ የሆነ መነሻ ታሪክ ያለው መሆኑን አባይነህ (2012) ያስረዳሉ፡፡

በአውሮፓውያን ከ1920-1930ዎቹ ባሉት ዓመታት እንደተጀመረ የሚነገረው ምትሃታዊ እውነታዊነት /Magic realism/ Roh፣ Carpenter፣ Montompoly ንድፈ ዘውጉን ከስነጽሁፍ ጋር በማወዳጀት ስራዎቻቸውን ማቅረብ መጀመራቸው እውን ቢሆንም በተለይ አዳዲስ ፍልስፍናዊ እሳቤዎች በራቸው እንደተዘጋ ነው ሲሉ ቴዎድሮስ (2010) ገልጸዋል፡፡

ምትሃታዊ እውነታዊነት የስነጽሁፍ ዘውግ የጭብጥ ማጠንጠኛ መሆን ከጀመረ ወዲህ ጠቀሜታውን አስመልክቶ Stphen Solomon (2004) ምትሃታዊ እውነታዊነት ሁለት የተለያዩ ነገሮችን በጥምረት የያዘ በመሆኑ ከድህረ ቅኝ ግዛት በኋላ ለተፈጠረው የባህል መቀየጥ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮ ነበር Stphen Solomon (2004)፡፡ Bower (2004) ደግሞ ጸረ ኮሎኒያሊዝም የሆኑ እሳቤዎችን ለተደራሲያን ለማጋባትና በቅኝ ግዛት ወቅት አንድ ሃይል ነጻ ያወጣናል የሚለው እሳቤ ማየሉ በካናዳ ለንድፈ ሃሳቡ ማበብ በምክንያትነት እንደሚጠቀስ አስረድተዋል፡፡

ምትሃታዊ እውነታዊነት /Magic realism/ የሚለው መጠሪያ ቃል እውን ሊሆን የቻለው በጀርመናዊው Roh (1925) አማካኝነት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ምትሃት የሚለው ቃል ረቂቅ በሆኑ የስዕል ስራዎች ይገለጽ እንደነበር ገልጿል፡፡

ምትሃታዊ እውነታዊነት መጀመሪያ ላይ ቃሉ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በዚሁ ምክንያት Carpentier (1949) የ Roh (1925) ስያሜ ውድቅ በማድረግ ምትሃታዊ እውነታዊነትን

ወደ አስደናቂ ትዕይትነት የመቀየር ሀሳብ ያደረበት በመሆኑ ምትሃታዊ እውነታዊነት ከእውነት የራቀና ያልተለመደ ጉዳይ /Fantasy/ ነው የሚል እሳቤ አራምዷል፡፡

ምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፍን በማቀንቀንና በማስተዋወቅ ረገድ Eladio (1959)፣ Joyce (2002)፣ Stephen (2004)፣ Angel (1955)፣ Roh (1925)፣ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ምትሃታዊ እውነታዊነት /Magic realism/ በተለያዩ ጉዳዮች ውስጥ አልፎ ከ1920ዎቹ ድህረ አብዮት በኋላ የድህረ ዘመናዊያን ንድፈ ሃሳብ በመሆን ይበልጥ እየተስፋፋ ሊመጣ ችሏል፡፡

Mattew (1998) ምን እንደተፈጠረ በከፍተኛ ማብራሪያ ከነዝርዝሩ እውነታዊነትን መሰረት ባደረገ መቼት በሆነ አካል ባልተለመደ መልክ ተከውኖ ለማሳመን የሚካሄድ ክዋኔ ነው ሲል የምትሃታዊ እውነታዊነትን አጀማመር ገልጿታል፡፡

የጀርመናዊው Roh (1925) የምትሃታዊ እውነታዊነት ጅማሮ በ1930ዎቹና በ1940ዎቹ በኢጣሊያዊው ጸሃፊ Bontempelli (1974) ተስተጋብቶ ምትሃታዊ እውነታዊነትን እውን በማድረግ አስደናቂነቱን፣ ሚስጠራዊነቱን እንዲሁም ተፈጥሮዋዊ እውነታውን አስተዋውቋል፡፡ Carpentier (1949) እንደሚለው የአስደናቂ እውነታ ጥበብን በተግባር፣ በግልጽና በተጨባጭ ምትሃትን በማሳየት በአንድ አካባቢ ባሉ የተለያዩ ባህሎች ውስጥ መመልከት እንችላለን፡፡

ምትሃታዊ እውነታዊነት በተለይም በቀደመው ዘመን ተአማኒነት እና በጋራ የሚያስማማ ሃሳብ የሌለው ከመሆኑ ባሻገር እንደ አስፈሪ የድርጊት ትዕይንት ስለሚቆጠር በዚህ ዘርፍ ጥናትና ምርምር ማካሄድ አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል፡፡

በላቲን አሜሪካ ምትሃታዊ እውነታዊነትን ከስነጽሁፍ ጋር የማወዳጀት ጅማሮ ለምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ ማበብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ በዚሁ መነሻ በእንግሊዝ በ1970 በካናዳና በሰሜን አፍሪካ፣ በስፔን፣ በሕንድና አውስትራሊያ ዘግየት ብሎ ሊቀላቀል ችሏል (Bower 2004፣34-35)፡፡

ምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ መነሻው ከላቲን አሜሪካ ቢሆንም በተለይ ይህን የትረካ ስልት በመጠቀም ምዕራባውያን የሚደርስባቸውን የሰብዓዊ መብት መጣስ ፣ ግፍና

ጭካኔ የተሞላበት አገዛዝና ሌሎች ችግሮችን ያስተጋቡበት መሆኑን በእናትላይ (2010) ባደረገችው ጥናት ገልጻለች፡፡

የምትሃታዊ እውነታዊነት በምዕራባውያን የተጀመረ ቢሆንም ዘውጉ ግን ዓለም አቀፋዊ ገጽታ ያለው መሆኑን በርካታ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ የሚስተዋሉት የግዕዝና የተለያየ ጭብጥ ያላቸው የስነጽሁፍ ውጤቶች በምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ የሚቀርቡ በመሆኑ ያልተለመደና አዲስ አያደርገውም፡፡

የመንግስት አስተዳደር ስርአትን መሰረት አድርጎ የሚጓዘው የሀገራችን የስነጽሁፍ ጭብጥ በአብዛኛው ሀይማኖታዊ፣ ስነምግባራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁነቶችን የሚከተል ሲሆን ታይቷል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገራችን ስነጽሁፍ ውስጥ የምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ ጭብጥ መታየት የጀመረ በመሆኑ ምትሃታዊ እውነታዊነትን በተሟላ መንገድ በስነጽሁፍ ውስጥ መጠቀም የተለመደ ከመሆን አልፎ በጊዜ ሒደት ምትሃት ላይ ትኩረት ያደረጉ ስራዎች መታየት ጀምረዋል፡፡ ለምሳሌ የይስማከ ወርቁ ክቡር ድንጋይ (2005)፣ የኦጋዴን ድመቶች (2009) እና አዘርግ (2010) መጻሕፍቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግን አስመልክቶ በሀገራችን የተጠኑ ጥናቶች ውስን ሆነው ቢታዩም በአዲስ አበባ፣ በጅማ፣ በባህር ዳርና በሌሎች ዩኒቨርስቲዎች ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ከእነዚህ ጥናቶች መካከል ጥቂቶቹ የምትሃታዊ እውነታዊነት የትረካ ስልት የድህረ ቅኝ አገዛዝ ሁኔታዎችን ለማሳየት በውጪ ሀገር ልቦለዶች ላይ የነበረውን ስነጽሁፋዊ ፋይዳ ተንትነው ለማሳየት የቀረቡ ሲሆን ቀሪዎቹ ደግሞ የምትሃታዊ እውነታዊነት መገለጫና የአቀራረብ ንጽጽር ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው (አቤኔዘር 2010)፡፡

ይህ ጥናት በምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ በተጻፈ መጽሃፍ ላይ ትኩረት ያደረገበት ዋነኛ ምክንያት ምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ በሀገራችን ትኩረት ተደርጎ ቢሰራበት ማህበረሰቡን በስነጽሁፍ አማካኝነት ማስተማር የሚያስችል ሃይል እንዳለውና በዚሁ ዘርፍ የተጠኑ ጥናቶች ትኩረት ያላደረጉበትን የምትሃት አይነት የሆነው ጥንቁልና በግለሰብ፣ በማህበረሰብና በሀገር አቀፍ ደረጃ እያደረሰ ያለው ችግር በስነጽሁፍ

አማካኝነት እንዴት እንደቀረበ ለማሳየት ነው፡፡ ለዚህ ጥናት ተግባራዊነት ሲባል አዘርግ (2010) ኤጭ…! ልቦለድ መጽሃፍ ተመርጧል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በሀገራችን አልፎ አልፎ የምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግን በመጽሃፎቻቸው ውስጥ በማካተት ሊጠቀሙበት ከሞከሩ ጸሃፊዎች መካከል ጀማል ሱሌማንና የዝና ወርቁ የተሸጠው ሰይጣን፤ ስብሃት ገ/እግዚአብሄር አጋፋሪ እንደሻው፤ አለማየሁ ገላጋይ ወሪሳ፣ ኩርቢት፣ በፍቅር ስም፣ ታለ፣ ሀሰተኛው (በእምነት ስም)፤ አዘርግ ኤጭ…! ማዕበል ፈጠነ "ሀሽማል"፤ አለማየሁ ዋሴ "እመጓ ፣ ዝጎራና መርበብት"፤ አሌክስ አብርሃም "ከዕለታት ግማሽ ቀን" በሚል በወግ እና በወጥ ስራዎቻቸው ውስጥ ሊያካትቱ የሞከሩ ሲሆን ከዚህ ባንጻሩ የይስማከ "ክቡር ድንጋይ" እና "የአጋዴን ድመቶች" መጽሃፍቶች ሙሉ በሙሉ የምትሃታዊ እውነታዊነት ጭብጥ ማጠንጠኛ ሆነው ቀርበዋል፡፡

በነዚህ የስነጽሁፍ ስራዎች አማካኝነት በሀገረሰባዊ ልማድ ስር ባሉ አስማት፣ ሟርት፣ ቆሌ፣ መተትና ድግምትን ተተኳሪ በማድረግ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ከዘመን መንፈስ አንጻር የተቃኙባቸው ናቸው፡፡

ለዚህ ጥናት ግላዊ ምክንያቴ መፅሃፉ የያዘውን አሉታዊ ጭብጥ አስመልክቶ በአንደኛ አመት የትምህርት ቆይታዬ በግምገማ መልክ በማዘጋጀት ያቀረብኩ መሆኑን ተከትሎ ሲሆን በሌላ በኩል መጽሃፉን ካነበቡ ግለሰቦች ጋር ባደረኩት ውይይት መጽሃፉ ጥናት ቢካሄድበት ምትሃታዊ ዘውግን መሰረት በማድረግ በስነጽሁፍ አማካኝነት ማህበረሰባዊ ችግሮችን ነቅሶ ማሳየት እንደሚቻል የሚያመላክት መሆኑን በመረዳት ነው፡፡

ከዚህ በተጓዳኝ ምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ ለስነጽሁፍ ያለውን ኪናዊ ፋይዳ ከማመላከት ባለፈ በዚሁ ዘርፍ ጥናት ለሚያደርጉ እንደ መረጃ ምንጭ ያገለግላል በሚል ተነሳሽነት ነው፡፡

አካባቢያዊ ምክንያቴ አስማት በጥንቆላ ሳቢያ እያደረሰ ያለውን ግለሰባዊ፣ ማህበረሰባዊና ሀገራዊ ተጽዕኖ ከመጽሃፉ በተሰበሰቡ መረጃዎች አማካኝነት ማሳያ አድርጎ ለማመልከት ነው፡፡

በማህበረሰቡ ውስጥ ምትሃት፣ አስማት፣ ጥንቆላ፣ መተት፣ ድግምት የተሰኙና ሌሎች ግልጽነት የጎደላቸውን ትርጓሜዎች ግልጽ በማድረግ ስነጽሁፍና ምትሃት በጋራ

ሲቀናጁ ያላቸውን ኪናዊ ፋይዳ መጠቀም ሌላኛው የዚህ ጥናት ትኩረት ሆኖ ቀርቧል፡፡

## 1.3. የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

1. በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ ምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ የሚገለጽባቸው ባህርያት ምን ይመስላሉ?
2. አስማት በግለሰብ፣ በማህበረሰብና በሀገር አቀፍ ደረጃ ምን አይነት ጉዳት እያደረሰ ነው?
3. የምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ ምን አይነት ኪናዊ ፋይዳ ነበረው?
4. በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ የተንጸባረቀው ምትሃት አውዳዊ ትርጓሜው ምንድነው?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት ተከታዮቹ ዋና ዓላማ እና ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

### 1.4.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ኤጭ…! ልቦለድ የምትሃታዊ እውነታዊነት አሉታዊ ዘርፍ በሆነው ጥቁር አስማት ዘርፍ መቅረቡን ከመጽሃፉ በሚሰበሰቡ መረጃዎች አማካኝነት ማሳያ አድርጎ ማቅረብ ነው፡፡

### 1.4.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

ይህ ጥናት ተከታዮቹ ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

1. በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ ምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ ማሳያ ሆኖ የቀረበበትን ባህርያት ያብራራል፤
2. አስማት በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ በግለሰብ፣ በማህበረሰብና በሀገር አቀፍ ደረጃ ያደረሰውን ጉዳት ያስረዳል፤
3. የምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ የነበረውን ኪናዊ ፋይዳ ይጠቁማል፤

4. በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ የቀረበው አስማት ካደረሰው ችግር አንጻር ምን አይነት አውዳዊ ፍቺ እንዳለው ይጠቁማል፤

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ የስነጽሁፍ ጭብጥ ማጠንጠኛ በመሆን የማህበረሰቡን ችግር ነቅሶ ለማቅረብ አይነተኛ መንገድ መሆኑን የማሳየት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ ምትሃታዊ እውነታዊነት ላይ ትኩረት አድርገው ለሚያጠኑ ጀማሪ አጥኚዎች መነሻ ሃሳብ በመሆን ያገለግላል፡፡

ስለ ምትሃት በወሬ ደረጃ የሚነገረውን መላምት ግልጽ አድርጎ በመተንተን የሚያቀርብ በመሆኑ ያለውን እውነት ያሳውቃል፡፡ ምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ ትኩረት እንዲያገኝ በማድረግ ለስነጽሁፋዊ ሂስ መጎልበት ድርሻ ይኖረዋል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ኤጭ…! ልቦለድ በምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ ተጽፎ መቅረቡን በጽንሰ ሃሳብ ባህርያት አማካኝነት አስደግፎ በማሳየት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ በጥናቱ የሚተነተነውን ምትሃታዊ እውነታዊነት /magic realism theory/ መሰረት ያደረጉ ንድፈ ሃሳቦችን እና ጽንሰ ሃሳቦችን በመመልከት የጥናቱን ፍሬ ጉዳይ ለመተንተን የሚያስችሉ ባህርያትን ለይቶ በማሳየት እንዲሁም የሌሎችን ጥናቶች ትኩረትና ተመሳስሎ እንዲሁም ልዩነት በማብራራት ጥናቱ የሚሞላቸው ክፍተቶች የቀረበበት ክፍል ነው፡፡

## 2.2. ጽንሰ ሃሳባዊ ቅኝት

ይህ ክፍል ምትሃት ምንድነው? ከሚለው ጥያቄ ጀምሮ ከምትሃታዊ እውነታዊነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጽንሰ ሃሳቦች ተብራርተው የሚቀርቡበት ነው፡፡

### 2.2.1. ምትሃት ምንድነው ?

ባህሩ ዘርጋው (2004) የአማርኛ መዝገበ ቃላት ምትሃት የሚለውን ቃል "ያልሆነውን እንደ ህልም እንደ ጥላ ታይቶ የሚጠፋ፣ ጋኔን፣ ሰይጣን፣ እርኩስ መንፈስ" በሚል ፍቺ ሰጥተውታል፡፡ መተት የሚለውን ቃል ደግሞ "አዚም፣ ድግምት፣ አስማት፣ አፍዝ አደንግዝ በሰው ላይ ጉዳት ለማድረስ በተለያዩ ነገሮች በልብስ፣ በቁሳቁስ፣ በእንሰሳትና በሌሎች ነገሮች ላይ የሚያደርገው ድግምት" ሲሉ ገልጸዋል (ገጽ፣142)፡፡

ባህሩ (2004) በተጨማሪም ከዚሁ ሃሳብ ጋር ተመሳስሎ ያላቸውን ድግምትን "የተደገመ፣ ድጋም፣ አስማት" ካሉ በኋላ ጥንቆላን ደግሞ "መጻፍ፣ ትንቢት መናገር፣ በአስማት ጠጠር መጣል፣ ይህ ይሆናል ብሎ መናገር፣ በመተት አስገራሚ ትዕይንት የመፈጸም ተግባር" ሲሉ አብራርተውታል፡፡

ደስታ (1970) በኢትዮጵያ የሚታወቀውን ከአስማት ጥበብ ጋር ተያያዥነት ያለውን ጠልሰም የተሰኘውን ቃል "ጠለሳም፣ ባለጠለስ፣ በያይነቱ የአስማት ስዕል ለራስ ምታት፣ ለሆድ ቁርጠት፣ ለቁርጥማት፣ በክታብ ውስጥ ጠንቋዮች የሚስሉት እስላሞች ባንገታቸው የሚያደርጉት የብር ወይም የወርቅ አሸንክታብ" እንደሆነ ጠቅሷል (ገጽ፣558)፡፡ Rushdie Slemon (1995) ምትሃት የሚለው ቃል በጥንዳዊ ተቃርኖ (Binary

opposition) በሚገለጸው የእውነታ መገለጫና ድንቅ በሆኑ ነገሮች መካከል አንዱ ሌላውን የሚቃረን (Oxymeron) እንደሆነ ይገልጻል፡፡

የምትሃታዊ እውነታዊነት ስያሜን አስመልክቶ የተለያዩ ምሁራን የተለያዩ ትርጓሜዎችን ሰጥተዋል፡፡ የኩባው ፀሃፊ Alejo Carpenter (1960) (Lo real marvellons) አስደናቂ እውነታ (American reality) የሚል ትርጓሜ ሰጥተዋል፡፡

ከዚሁ የትርጓሜ ሃሳብ ጋር ተያይዞ ምትሃት በየሃገሩ ገቢራዊ የሚሆንበት መንገድ የራሱ ስያሜ የሚኖረው ቢሆንም ምትሃት ባንድ በኩል አስደናቂ ክስተት የሚታይበት ሲሆን በሌላ መልኩ ደግሞ እውነታ የሰው ልጆች የለት ተለት ተተኳሪ ጉዳይ በመሆኑ Alejo Carpenter (1960) እንዳሉት አስደናቂ እውነታ የሚለው ስያሜ ሊገልጸው ይችላል፡፡

## 2.2.2. የምትሃት አጀማመር

ዓባይነህ (2012፣24-26) መጽሃፈ ሔኖክ በሚል ባሳተሙት መጽሃፍ ስለ ምትሃት አመጣጥ ተከታዩን አስፍረዋል፡፡

> የሰው ልጆች ከበዙ በኋላ እንዲህ ሆነ፡፡ በእነዚያ ወራት መልከ መልካሞችና ደመግቡዎች ሴቶች ተወለዱላቸው፡፡ የሰማይ ልጆች መላዕክትም እነርሱን አይተው ወደዷቸው፡፡ እርስ በርሳቸውም ለኛ ከሰው ልጆች እንምረጥ ለእኛም ልጆች እንውለድ አሉ፡፡ ፈጣሪ ለመላዕክት እነሆ ጥበብ ሲል ተለይተው ሁሉን እንዲያውቁ ጥበብ ሰጣቸው፡፡ ከሰው ልጆች ጋርም ጋብቻ ፈጸሙ፡፡ በዚሁ ምክንያት ለሰው ልጆችም ሟርትንና ምታት መስራትን አስተማሯቸው፡፡ ስር መማስንና ቅጠል መበጠስንም አወቁ፡፡

ዓባይነህ (2012) አያይዘው "ቃኤላውያን ሕይወታቸውን ለማሰንበት ሲሉ፣ ተፈጥሮን በመመራመር ለቁስላቸው ዕጽዋትን ቀመሙ፡፡ ለጠላቶቻቸው ሰይፍና ጎራዴን፣ ቢለዋና ሳንጃን፣ ቀስትና ፍላጻን አበጁ፡፡ ለሰብላቸው ዩኒቨርስንና ክዋክብትን ተመራመሩ፡፡ የሴቶቻቸውን እጆች ሳይቀር እንሶስላ መቀባት የጀመሩት እነርሱ ናቸው፡፡ ለአንገታቸው ጥቁራትና ንቅሳትም እንዲሁ"፡፡

ምትሃታዊ እውነታዊነት ምትሃትና እውነት ከሚሉ ቃላት የተመሰረተና አንዱ ሌላውን በመደገፍ የገሃዱን ዓለም በተለየ ዘዴ ለመተርጎም የሚያስችል ከ20ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ከረቂቅ የስዕል ጥበብነት ተሻግሮ የምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ በመሆን እየዳበረ የመጣ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ Hegerfeldet (2005፡12) ምትሃታዊ እውነታዊነት የሚለው ቃል ውስብስብና የሁለቱንም ሃሳቦች ትርጉም ሙሉ በሙሉ በመተው በአዲስ መልክ የተመሰረተ (in these terminological complexities which might be grounds for ababdoming the concept altogether it retains a strange seductiveness) እንደሆነ ያስረዳል፡፡

## 2.2.3. ምትሃታዊ እውነታዊነትና ስነጽሁፍ

በቀደመው ዘመን በስዕል አማካኝነት ረቂቅ ጥበብ እንደሆነ ሲታመንበት የነበረው የአስማት ጥበብ ከተረክ አልፎ ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወዲህ ግን በስነጽሁፍ በኩል እራሱን የቻለ ንድፈ ሃሳብ በመሆን ብቅ ሊል ችሏል፡፡ ምትሃታዊ እውነታዊነት /magic realism theory/ የሚለውን መጠሪያ ቃል የሰየመው ጀርመናዊው Roh (1925) ነው፡፡

Stephen (2004) ምትሃታዊ እውነታዊነት ሁለት የተለያዩ ነገሮችን በጥምረት የያዘ በመሆኑ ከድህረ ቅኝ ግዛት በኋላ ለነበረው መስፋፋት የተፈጠረው የባህል መቀየጥ ምቹ ሁኔታ እንደነበር አስረድቷል፡፡

የምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ እንዲጎለብት ኢጣሊያዊው Bontemplli (1974)፣ ሜክሲኮዋዊው Carpentier (1949) እና Flores (1955) አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

"ምትሃታዊ እውነታዊነት በአካባቢያችን የምናየውን ተራ ዓለም በተራ ቁሳቁሶች ላይ ትርጉም በሚሰጥ እና ጠቀሜታ ባለው መልክ ሊገለጽ የሚችለው በስነጥበብ አማካኝነት ነው Roh (1925)፡፡

ከምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ ጋር በተያያዘ የተለያዩ ተንታኞች የተለያየ እሳቤ ሰንዝረዋል፡፡ Carpenter በ Zamora እና Faris (2004) እንዳስቀመጠው ምትሃታዊ እውነታዊነት የስነጽሁፍ ስልት የምትሃት፣ የእውነታ፣ የሚትና ድንቃ ድንቅ የሆኑ ነገሮችን በአንድነት የያዘ መሆኑን ተናግሯል፡፡

Hegerfeidt (2005፣32) ምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ ተጠየቃዊ የሆኑትን እና ተጠየቃዊ ያልሆኑትን የሰዎችን ልምድና ገጠመኝ ለማየት የሚያስችል ዓለም አቀፍ ገጽታ ያለው ነው፡፡

Russdie Sleman (1995፣410) ምትሃታዊ እውነታዊነት እንደ ድህረ ቅኝ አገዛዝ ዲስኩር (magical realism as a post colonial descours) በሚል ርዕስ ባዘጋጀው ጽሁፍ የሁለትዮሽ (binarism) እና ጥምር (dualities) አሰራር ምክንያት በምዕራባውያን ተጀምሮ በድህረ ቅኝ አገዛዝ ጸሃፊዎች አማካኝነት የቅኝ አገዛዝ ግፎችን ይፋ ለማውጣት በስፋት የተተገበረ ስነጽሁፋዊ ንድፈ ሃሳብ ነው ሲል ገልጿል፡፡

በምትሃታዊ እውነታዊነት ልቦለዶች ውስጥ ልዕለ ተፈጥሮዋዊ ሁነቶች ያልተለመዱ ገጸ-ባህርያትን በመጠቀም የገሃዱን ዓለም እውነታ በተለየ መንገድ እንደገና እንድናይ ያደርጉናል፡፡ ይህም የሚሆንበት ምክንያት የምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፋዊ ሁነቶች የሚገለጹት በእውነተኛ መቼት በመሆኑ ነው Faris (2004፣14)፡፡

ምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፋዊ ስልት በ1970 በካናዳ፣ በሰሜን አፍሪካ፣ በስፔን፣ በካረቢያን፣ በህንድና በአውስትራሊያ ዘግየት ብሎ ተቀላቅሏል Bower (2004፣34-35)፡፡

የምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፋዊ ንድፈ ሃሳብን በመላው ዓለም በማስፋፋት የሚፈለገውን ለውጥ ማምጣት ባይቻልም በአውሮፓ ምትሃታዊ እውነታዊነትን ከስነጽሁፍ ጋር የማወዳጀት ጅማሮ ግን በየሃገራቱ በርካታ ጸሃፍት እንዲነሳሱ መንገድ ከፋች ሆኗል፡፡

Tonie Morison (2019) ከአፍሪካ አሜሪካውያን ጸሃፍት መካከል አንዷ ስትሆን Beloved በተሰኘ ልቦለዷ የምትሃታዊ እውነታዊነት ትረካ ስልትን በመጠቀም በአፍሪካ አሜሪካዊያን ሕዝቦች ላይ አውሮፓውያን ሲያደርጉት የነበረውን አያሌ የባሪያ ንግድ ድብቅ ታሪክ ለማሳየት ተጠቅማበታለች፡፡

በተመሳሳይ Stephen Selmon (2004) ማጂካል ሪያሊስት ስነጽሁፋዊ ስራዎች በድህረ ቅኝ አገዛዝ ሁኔታዎችንና ግንኙነቶችን እንዲሁም ባሕሎችን እንዲሚያንጸባርቁ ይናገራል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በ Gabrial Garcia Marquze "one handred years of soltiued" ስራ ውስጥ የቀረበው "Speaking Mirror" የአተራረክ ስልት የድህረ ቅኝ አገዛዝ ሁኔታዎችንና ግንኙነቶችን ማሳየት የቻለ መሆኑን አመልክቷል፡፡

ምትሃታዊ እውነታዊነት በኢትዮጵያ የስነጽሁፍ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚፈለገውን ያህል ትኩረት ያገኘ ስልት አይደለም፡፡ ምትሃት በኢትዮጵያ ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ሲሆን በመንፈሳዊ ስርአት አማካኝነት ከግዕዝ ጋር የተሳሰረ ረጅም ታሪክ እንዳለው Braziller (1979) ገልጸዋል፡፡

በአውሮፓውያን ዘንድ በረቂቅ ስዕል አማካኝነት ወደ ስነጽሁፋዊ ስልት እንደተቀየረ የሚነገረው ምትሃታዊ እውነታዊነት ከሁለተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያውያን የሚጠቀሙበት ልዩ ጥበብ እንደነበር "የኢትዮጵያ አስማት አዘገጃጀት መጽሃፍ" በማብራራት ጠልሰምንና ምትሃትን እንዴት ማዘጋጀት እነደሚቻል ያስረዳል፡፡

ምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ በኢትዮጵያ የስነጽሁፍ ታሪክ ውስጥ እምብዛም የገዘፈ ቦታ ባይኖራቸውም በስብሃት ገ/እግዚአብሄር አጋፋሪ እንደሻው፣ በጀማል ሱሌማንና የዝና ወርቁ የተሸጠው ሰይጣን፣ በአለማየሁ ገላጋይ ወሪሳ እና ሌሎች ስራዎች፣ በአሌክስ አብርሃም ከለታት ግማሽ ቀን ስራዎች ውስጥ ሲንጸባረቅ ታይቷል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የይስማከ ወርቁ ክቡር ድንጋይ (2005) እና የኦጋዴን ድመቶች (2009) የአዘርግ ኤጭ…! (2010) ስራዎች በምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ ቀርበው ለንባብ የበቁ ስራዎች ናቸው፡፡

## 2.2.4. የምትሃት አይነቶች

Bowers (2004፣86) የተለመዱት የምትሃታዊ እውነታዊነት አይነቶች ሁለት እንደሆኑ ጠቅሶ የመጀመሪያው ልማዳዊ ምትሃታዊ እውነታዊነት (Outological magical realism) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በእውቀት የሚገኝ ምትሃታዊ እውነታዊነት (Epistomological magical realism) ይሰኛሉ፡፡ ልማዳዊ ምትሃታዊ እውነታዊነት በማህበረሰብ ልምድ እና እምነት ላይ ተመስርቶ በስነጽሁፍ ስራዎች አማካኝነት የሚገለጽ ሲሆን በእውቀት የሚገኘው ምትሃታዊ እውነታዊነት ደግሞ በምናባዊ ፈጠራ በእውቀት ተመስርቶ የሚቀርብ ጥበብ ነው፡፡

መጥፎና ጥሩ የአስማት አይነቶች ቢኖሩም ከመጥፎ የአስማት አይነት ጥበቃ የሚያስገኝ ጥሩ የአስማት አይነት እንዲሁ አለ፡፡ መጽሃፍ ቅዱስ አንዱን የአስማት አይነት ጥሩ ሌላውን ደግሞ መጥፎ እያለ አይፈርጅም፡፡ ከዚህ ይልቅ ማንኛውንም አይነት አስማታዊ ድርጊት ያወግዛል፡፡ ይህንኑ አስመልክቶ "አስማት አትስሩ፡፡" ዘሌዋውያን

(19፥16) "መናፍስት ጠሪ ወይም ጠንቋይ የሆነ ወንድ ወይም የሆነች ሴት ካሉ ይገደሉ፡፡" ዘሌዋውያን (20፥27) "አስማተኛ፣ ሞራ ገላጭ፣ ምትሃተኛ፣ መናፍስት ጠሪ፣ ጠንቋይ ወይም ሙታን አነጋጋሪ በመካከልህ አይገኝ" ዘዳግም (18፥10-14)፡፡

በአቤኔዘር ታዬ (2012) ውስጥ ተከታዮቹ የምትሃት አይነቶች ተጠቅሰዋል፡፡

- **ጥቁር አስማት**

ይህ ልዕለ ተፈጥሮዋዊ ሀይል ለጎጂ ተግባር እንዲውል የሚያደርግ ክህሎት ያለው ነው፡፡ ፓራሳይኮሎጂስቶች ይህንን የአስማት ጥበብ ከግለሰብ እስከ ሀገር ድረስ በሕይወትና በንብረት ላይ ከሚደረግ ጉዳት ጋር ያያይዙታል፡፡ እንደርቢ፣ አፍዝ አደንግዝ፣ ጥንቁልና፣ ጥላወጊና የመሳሰሉት በዚህ ስር ይካተታሉ፡፡

- **ነጭ አስማት**

ይህ ልዕለ ተፈጥሮዋዊ ሃይል ነፍስ ለማጥፋት ወይም ጉዳት ለማድረስ በሚል የሚከናወን ሳይሆን በሕይወት ጠቃሚ ናቸው ተብለው የተለዩ ጉዳዬችን ለመከወን የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- "ዕፀ-መሰውር" ሰዎችን ከጠላታቸው ለመሰወር የሚያገለግል የአስማት አይነት ሲሆን "መፍትሄ ስራይ" ደግሞ አንድ ሰው ላይ የሚደረግ የአስማት ጉዳትን ለመሻር የሚያገለግል የአስማት አይነት ነው፡፡

## 2.3. ምትሃታዊ እውነታዊነት ከሌሎች ዘውጎች ጋር ያለው ግንኙነት

- **የዘመን መንፈስ /Zeitgeist/**

ደራሲው ሲጽፍ አስተሳሰቡ፣ እምነቱና መንፈሱ በሚጽፈው መጽሃፍ ውስጥ ይንጸባረቃል፡፡ በዘመኑ አንድ ደራሲ የጻፈው ጽሁፍ ከዘመን ዘመን በተለያዩ ብያኔዎችና ስልቶች ሊሻር መቻሉ የሚያጠያይቅ አይደለም ብሌን (2007)፡፡

የዘመን መንፈስ ትኩረቱ ሳይንስና ቴክኖሎጂ አይደለም፣ ትኩረቱ አብዮት አይደለም፣ ትኩረቱ ጅሀድ ወይም የመስቀል ጦርነት አይደለም፣ ትኩረቱ እነዚህ ክስተቶች በምሁሩ ልቦና የሚፈጥሩት ወረራ ወይም በባህሉ ላይ የሚፈጥሩት ድባብ ነው ቴዎድሮስ (2001)፡፡

- **የመንፈስ ግንኙነት /telepathy/**

በ1882 በFeraderc Merss ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን በመንፈስ ግንኙነት ከስሜት ህዋሳት ውጪ አንዱ ከሌላው ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት ነው፡፡ ይህ በምትሃታዊ እውነታዊነት ውስጥ በጥቂቱ ሊኖር ይችላል፡፡ የስሜት ህዋሳትን በመጠቀም በዓይን እንደምናየው፤ በጆሮ እንደምንሰማው፤ በአፋችን እንደምንናገረው ሳይሆን የእርስ በርስ የአዕምሮ ተግባቦትን ይጠይቃል፡፡

- **ሕልውናዊነት** /Existentialism/

የሳይንስ ፈጠራ የሆነው ኒኩሌር የፈጠረው ስጋት የሰው ልጅ ለሚኖርበት ማህበራዊ ዓለም ባይተዋርና ለገዛ እራሱም ልቦናዊ ዓለም በዓድ እንዲሆን እንዲሁም ምክንያት እንዲያጣ አድርጎታል፡፡ ግለሰቦች የሚጻኙበት የጋራ እሴት መጥፋቱ ሁሉም የራሱ ምርጫና ውሳኔ እንዲኖረው አድርጎታል፡፡ በዚህ ስር ጥንዳዊ ተቃርኖ የሚኖር ሲሆን ምርጫና ውሳኔ፣ ነጻነትና ሀላፊነት፣ ባይተዋርነትና ብቸኝነት፣ ህይወትና ሞት ወዘተ የመሳሰሉት ጉዳዮች አይነተኛ መገለጫ ናቸው (ቴዎድሮስ 2001)፡፡

- **እውነታዊነት** /Realism/

ምትሃታዊ እውነታዊነት የለት ተለት ተተኳሪ ጉዳዩች የሚመነጩት እውነታን መሰረት ባደረገ መልክ በመሆኑ እውነተኛ የሕይወት አንደምታን ለመፍጠር የሚያስችል ባህሪ ያለው ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ሕይወትና ሞት፤ ወንድና ሴት፤ አዕምሮና አካል እንዲሁም ሌሎች ሊጣሱ ወይም ሊሻሻሉ ወሰን የተደረገላቸው ናቸው (Wendy 2012፣15-16)፡፡

- **ሕልማለማዊነት** /Surrealism/

በልቡሰ ጥላ የሚታይ ተደርጎ ስለሚታይ ከምትሃታዊ እውነታዊነት ጋር ተቃርኖ እንዳለው ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ምትሃታዊ እውነታዊነት እንደ ህልም አይነት የስነ ልቦና ጫና የመፍጠር ሁኔታ ያለው ነው ስትል አቤኔዘር (2012) ጸደይ (2005)ን ጠቅሳ ገልጻለች፡፡

- **ገደብ አልባ ምናባዊነት** /Fantasy/

Wolfe (1935) "ምትሃታዊ አውነታዊነት ማለት ከእውነት የራቀና የተጋነነ ተረክ ማለት ነው" ሲሉ Terry Pratchett (1986) ደግሞ "ምትሃታዊ እውነታዊነት ማለት የበላይነትን

ለማሳየት እና አግራሞትን ለመፍጠር ከፍ ያለ የምናብ ገድልን የሚጠቀም ነው" በሚል ይገልጹታል፡፡ በፋንታሲና በፋንታሲ ስነጽሁፍ መካከል ያለው ልዩነት ሲታይ በፋንታሲ ጸሃፊው ወይም አንባቢው በቀረበው ታሪክ ውስጥ መሪ ተዋናዩ ተፈጥሮዋዊ ወይም መለኮታዊ ምናባዊነት የሚስተዋሉበት መሆኑን መለየት የሚቻል ሲሆን በፋንታሲ ስነጽሁፍ ግን በአጭር ትረካ ውስጥ በማመንና ባለማመን መካከል ትዕይንቱ፡ መለኮታዊ ወይም የተጋነነ የምናብ ውጤት መሆኑን በቀላሉ መረዳት የምንችልበት ነው፡፡

- **በተፈጥሮ ሃይል ማመን** /Animist realism/

በተፈጥሮ ሀይል ማመን በተለይ በአፍሪካ ሕዝቦችና ስነጽሁፍ ውስጥ የሚታይ ሲሆን ጠንካራ የሆነ ተፈጥሮዋዊ ሀይልን እንዲሁም ባህላዊ እምነትን በመቀበል ከአያት ቅድመ አያቶቻቸው ጀምሮ በማስቀጠል እሴት የሚገለጽ ነው፡፡

- **የሰብአዊነት መንጠፍ**

ዮናስ (1992፣108) የሰብአዊነት መንጠፍ በሕሊና መጠቀም አለመቻልን፣ የግል ነጻ ፍቃድን፣ አሳልፎ መስጠትን ያመለክታል፤ በሌላ በኩል ሰዎች ሰውነታቸው ተረግጦ ሰብአዊ መብታቸው ተዋርዶና ተንቆ ከእንስሳት እና ዕቃ ተራ ተመድበው የሚታዩበትን እነሱም ይህን የማይገነዘቡበትን ሁኔታ ያመለክታል ሲል ጠቅሷል፡፡

## 2.4. የምትሃታዊ እውነታዊነት ባህርያት /Character of magic realism/

ምትሃታዊ እውነታዊነት ከሌሎች ዘርፎች የሚለይባቸው የራሱ የሆኑ ባህርያት አሉት melakneh (2010)፡፡

**ከታዬ አሰፋ እና ከመዝገቧ ታደሰ የተወሰዱ የምትሃታዊ እውነታዊነት አከፋፈል ባህርያት፡-**

### 2.4.1. ሊታመኑ የማይችሉ ድርጊቶችና እና ገጸ ባህርያት /Fantastical element and Charcters/

ለምናባዊነት የቀረቡ የተፈጥሮን ህግ የሚጥሱ ተግባራት ሊፈጸሙ የሚችሉ ከሰው ስብዕና ከፍ ያለ ልዕለ ተፈጥሮዋዊ ባህሪ የተላበሱ ገጸ ባህርያት ተግባሩን ይፈጽሙታል

Bowers (2004፣40)፡፡ ተግባሩ ያልታሰበ እውነታን የተላበሰ የሰውና የተፈጥሮ ህጎችን የሚጥስ ከተለመደው እውነታ የሚጋጭ ሲሆን ይታያል Zamora (2004፣120)፡፡

### 2.4.2. መቀላቀል /Hibridity/

Encarta (2009) መዝገበ ቃላት ንጥር ነገሮችን በማቀላቀል እንደ ድቅል በማየት ይተረጉማቸዋል፡፡ ከተለያዩ ገጽታዎች ወይም አካላት ድብልቅ የተሰራ ነገር አስማታዊ እውነታዊነት በእውነታው የተያዙ በርካታ መቀላቀሎች የሚስተዋልበት ነው፡፡

### 2.4.3. የደራሲው ገለልተኛነት እና ተጨባጭ ማረጋገጫ ያለመስጠት

በምትሃታዊ እውነታዊነት ተራኪው ትክክለኛ ገለጻዎችን በልቦለድ ውስጥ አያቀርብም፡፡ የሚቀርቡት የገጸ ባህርያት ክዋኔዎች ተጨባጭ ማስረጃ ያላቸውና ሊታመኑ የሚችሉ ሆነው አይቀርቡም፡፡ ይልቁንም ደራሲው በተለየ መንገድ አስደናቂ ሁነቶችን በመጨመር ታሪኩን በጥንቃቄ እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡ ያልተለመዱ ነገሮች እንደተራ ነገር ሆነው ይቀርባሉ ለሚቀርበው ጉዳይ ማረጋገጫ ያላቸው ሲሆን አይታይም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተራኪው ግድየለሽ ሲሆን ይታያል (Chanady 1985፣16)፡፡

### 2.4.4. ጥንዳዊ ተቃርኖ /Binary opposition/

ምትሃታዊ አውነታዊነት ጥንዳዊ ተቃርኖን በመጠቀም ይታወቃል፡፡ Zomra and Faris (1995፣6) አዕምሮዋዊና አካላዊ፣ ሕይወትና ሞት፣ መንፈሳዊና ቁሳዊ፣ ገሃዳዊ ዓለምና ምናባዊ ዓለም፣ ሴትና ወንድ እንዲሁም መሰል ጉዳዬች በምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፍ ስራዎች እንደ አዲስ ይመሰረታሉ፡፡

### 2.4.5. ሚስጢራዊነት

የምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውጎች የክዋኔዎች ሚስጢራዊነት የሚታይባቸው ሲሆን እኩል በሆነ ስሜት በየወቅቱ ያሉ ቅኝ አገዛዞችንም ሆነ ሌሎች ፖለቲካዊ ተጽዕኖዎችን የመተቸት አቅም ያላቸው ናቸው (Melakeneh 2010፣83)፡፡

### 2.4.6. የፖለቲካ ትችት /poltical critique/

ምትሃታዊ እውነታዊነት ማህበረሰብን በተለይ ደግሞ የፖለቲካ መሪዎችን ተለምዷዊ የሆነውን መንገድ በመጣስ መልከዓ ምድርን፣ ማህበረሰባዊ ሁነቶችን፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዬችን ትኩረት አድርጎ ችግሮችን ነቅሶ እንደሚያሳይ ከላቲን አሜሪካ ስነጽሁፍ መመልከት ተችሏል፡፡

## 2.5. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት

ይህን ጥናት ለመመልከት ማህበራዊ ሒስ /social critique theory/ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ማህበራዊ ሒስ የተመረጠበት ምክንያት በማህበራዊ መስተጋብር በኩል ሳይታወቅ ስር የሰደዱ ችግሮችን ለመተንተን የሚያስችል ከመሆን ባለፈ ከጥናቱ ሃሳብ ጋር የሚስማማ በመሆኑ ነው፡፡

"**ማህበራዊ ሒስ**" /social critique theory/ እ.ኤ.አ. በ1920ዎቹ እና በ1930ዎቹ ከጀርመን ፍራንክፈርት ፍልስፍና ትምህርት ቤት የተነሳ አዲስ የፍልስፍና ንቅናቄ ሲሆን ይህም ንቅናቄ በዘመናዊነት ውስጥ ያጋጠሙንን ማህበራዊ ችግሮች መንስኤያቸውን ነቅሶ የሚያወጣና የመውጫ መንገዱንም የሚጠቁም ነው፡፡ በመሆኑም ማህበራዊ ሒስ አስፈላጊ ሆኖ የመጣው ይህንን የዘመናዊነት ተቃርኖ ለመረዳትና መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል ከመሆን ባለፈ በውስጡም ሁለት አይነት ጽንሰ ሃሳቦች አሉት (Elkins 1959)፡፡

### 2.5.1. ቀዳማይ ንድፈ ሃሳብ /The Hispanic Origen theory/

ቀዳማይ የምትሃታዊ እውነታዊነት ጽንሰ ሃሳብ አራማጆች በእይታም ሆነ በጽሁፍ ወይም ደግሞ በሁለቱም አማካኝነት እውነታን በሚፈለገው መንገድ ያለችግር ማቅረብ ይቻላል የሚል እሳቤ ያራምዳሉ፡፡ ለቀዳማይ ጽንሰ ሃሳብ አራማጆች ምትሃታዊ አውነታዊነት የወርቃማው ዘመን እሳቤ መገለጫ ነው፡፡ አርጀንቲና በዚሁ መንገድ ተጠቅማለች፡፡ በላቲን አሜሪካ ሀገራትም እንዲሁ ጠቀሜታው የጎላ እንደሆነ ይነገራል (Elkins 1959)፡፡

### 2.5.2. ድህረ ዘመናዊ ንድፈ ሃሳብ /Postmodernism theory/

ከ1970ዎቹ ጀምሮ የተነሳው ድህረ ዘመናዊነት /postsmodernism/ ሁለት መገለጫዎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው አሁን በአለም ላይ ያለውን እውነታ የምንመለከትበት ሲሆን

ሁለተኛው ደግሞ ዘመናዊነት አልፎበታል ከሽፏል የሚል እሳቤ ነው፡፡ ድህረ ዘመናዊነት የቀደምት ሕይወታችንን ታላላቅ ትረካዎችን ያፈራረሰ ክስተት ነው፡፡ እናም በድህረ ዘመናዊነት አፈታሪኮችን የማናምንበት፣ የጋራ እውነት የሚባል የሌለበት፣ ሰዎች ሁሉ ትክክል የሆኑበት፣ እውነት በገሀዱ ዓለም የሚገኝ ሳይሆን በቋንቋ፣ በፖለቲካና በዲስኩር የሚገለጥ አዲስ ዓለም ነው በሚል የሚያምን ነው፡፡

## 2.6. ዘመናዊነት እና ማህበራዊ ሒስ

ዘመናዊነት ሁለት ተቃርኖዎች አሉት፡፡ በአንድ በኩል ከሰው ልጅ ነጻነትና አብርሆት ጋር በሌላ በኩል ከሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ጋር እንዲሁም ከኢኮኖሚያዊ ብልጽግና ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ በሌላ ገጹ ዘመናዊነት ውስጥ የዘር ጭፍጨፋና ኢ-ሰብአዊ የሆኑ ጭካኔዎች /Genocide, holocaust/ አሰቃቂ የአለም ጦርነቶችና የሕይወት ትርጉም የለሽነት ተስፋፍቶ ይገኝበታል፡፡

**Elkins (1959) ማህበራዊ ሒስን የምንረዳባቸው ዋና ዋና ባህርያት ተከታዮቹ እንደሆኑ ይገልጻሉ፡-**

### 2.6.1. ዘመናዊነት /Modernity/

የሰውን ልጅ ነጻነት የሚመለከት ሲሆን ይህም አመለካከት "የሰው ልጅ እራሱን ከውጫዊ ሀይሎች /ባህል፣ ተፈጥሮና ሀይማኖት/ ነጻ ባደረገ ቁጥር የተሻለ ሕይወት ይኖረዋል" በተጨማሪም "የዕውቀት፣ የመቻቻልና የማህበራዊ ፍትህ መሰረት የግለሰብ ነጻነት ነው"፡፡

### 2.6.2. ከወቅቱ ጋር አብሮ መዘመን /Modernization/

የዘመናዊነት ሐሳቦችን በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂና በኢኮኖሚያዊ እድገት የሚገለፅበት ሒደት ነው፡፡ ይህም ሃሰብ በአብዛኛው "መዘመን ማለት እንደ ምዕራባዊያን መሆን ማለት ነው" የሚል አንደምታ አለው፡፡

### 2.6.3. ዘመናዊ አስተሳሰብ /Modernism/

የኪነ ጥበብ ትችት ነው፡፡ ይህ ትችት "የሰው ልጅ ቁሳዊ እድገት ስላመጣ ብቻ፤ ከተማ ውስጥ ስለኖረ ብቻ፤ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ስላደገ ብቻ ዘምኗል ማለት አንችልም፡፡"

ከእነዚህ ነገሮች ባሻገር "የሰው ልጅ ውስጠቱን እንዲያዳምጥ አዲስ የኪነ ጥበብ ንቅናቄ ያስፈልጋል፡፡ ኪነጥበብ የሰውን ልጅ ትክክለኛ ማንነት ማሳየት ይችላል" የሚል እሳቤ ነው፡፡

## 2.7. ምትሃታዊ እውነታዊነትን የሚመለከቱ የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

"የሃገራችን የስነጽሁፍ ትምህርትና ምርምር ከተወሰኑ መምህራንና ተመራማሪዎች ግለሰባዊ ጥረት ባለፈ ዛሬም የትምህርት ፍልስፍናው አልተሻሻለም፡፡ ዛሬም ድረስ ለአዳዲስ ኪናዊ ፍልስፍናዎች የአበያየን ስልቶችና ዘውጎች በሩን እንደዘጋ ነው" (ቴዎድሮስ 2010)፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፍ ዘውግ በአዲስ መልክ እየጎለበተ የመጣ ቢሆንም በተለይ በሀገራችን በአማርኛ ቋንቋ ከተሰሩ ጥናትና ምርምሮች ይልቅ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተሰሩ ጥናቶች ተበራክተው መታየታቸው በአማርኛ ስነጽሁፍ በሚጠኑ ጥናትና ምርምሮች ላይ የራሱን አሉታዊ ተጽዕኖ ለማሳደር ምክንያት ሆኗል፡፡

በዚሁ ሳቢያ በአማርኛ ቋንቋ በምትሃታዊ እውነታዊነት ጥናትና ምርምሮች በአብዛኛው ተዛማጅ ጽሁፎች የማይገኙ በመሆኑ በዚሁ መስክ የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮች በቂ የሆነ መረጃ አይገኝላቸውም፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር በአቻ ተመሳስሎ ሳይሆን በምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፍ የተጻፉ መጽሄቶችንና በጂማ፣ በባህር ዳርና በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲዎች የተጠኑ አራት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች፤ አንድ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያለው ጥልቅ የዳሰሳ ጥናት መጽሃፍን ጨምሮ በጥቅሉ አምስት ጥናቶችን ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡

ከእነዚሁ ጥናቶች ውስጥም የምትሃታዊ እውነታዊነት መገለጫዎች "በኦጋዴን ድመቶች መጽሃፍ ማሳያነት" በሚል ርዕስ አቤኔዘር (2012) ያጠናችው ጥናት አንዱ ነው፡፡

አቤነዘር (2012) የምትሃታዊ እውነታዊነትን መገለጫዎችን ከኦጋዴን ድመቶች መጽሃፍ አንጻር በመተንተን አሳይታለች፡፡ በዚህ ጥናት የምትሃታዊ እውነታዊነት ባህርያት የተዘረዘሩ ሲሆን ከነዚሁ ባህርያት አንጻር የምትሃታዊ እውነታዊነት መገለጫ ሃሳቦች ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

ሌላው ምትሃታዊ እውነታዊነት ላይ የተደረገ ጥናት Mezegebuw (2012) ሲሆን Mezegebuw ጥናት ትኩረት A comparative study of magical realism in "one

handered years of solitude" and "the famished road" የተሰኙ ሁለት መጽሃፍቶች ላይ የተደረገ የምትሃታዊ እውነታዊነት መገለጫ ንጽጽራዊ ጥናት ነው። Mezegebuw (2012) የ Marequze ስራ የሆነውን "one handred years of solitude" መጽሃፍ እና በናይጄሪያዊው ደራሲ ቤኒ ኦኮሪ "The famished road" መጽሃፍ ላይ ምትሃታዊ እውነታዊነት የተገለጸበትን መንገድ እና በሁለቱ መካከል ያለውን የጭብጥ አደራረስ መሰረት በማድረግ የድርሰቶቹን መለያ ባህሪ ወስዳ የንጽጽር ጥናት አካሂዳለች።

Taye (2012) እንዲሁ የማርክዬዝ ስራ በሆነው "one handred years of solitude" መጽሃፍን ከ Nega መዝለቂያ "The god who begat a Jackal" ጹሁፍ ጋር የምትሃት መገለጫ ላይ ያጠናው ጥናት ሌላው ተጠቃሽ ጥናት ነው።

ታዬ የምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፍን በሀገራችን ቀደም ብሎ ከነበረው ዘመነ ፊውዳሊዝም አንጻር ለመመልከት የሞከረበት ጥናት ሲሆን በተለይም በሀገራችን ስነጽሁፍ ውስጥ የአቤ ጉበኛ ጎብላንድ፣ የመኮንን እንዳልካቸው አርሙኝ ዓለም ወረተኛ እና የድሆች ከተማ እንዲሁም የስብሃት ገ/እግዚአብሄር አጋፋሪ እንደሻው መጽሃፍቶች ምትሃታዊ እውነታን የተንተራሱ ስራዎች መሆናቸውን ጠቅሷል።

በእናትላይ (2010) እንዲሁ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ የምትሃታዊ እውነታዊነት መገለጫዎች በክቡር ድንጋይና በኦጋዴን ድመቶች መጽሃፎች ላይ ጥናት አካሂዳለች። የዚህ ጥናት ትኩረት በተጠቀሱት መጽሃፎቹ ውስጥ ከምትሃታዊ እውነታዊነት ባህርያት አንጻር በመጽሃፎቹ ውስጥ የሚስተዋሉ ምትሃታዊ መገለጫዎችን ተንትኖ ማሳየት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው።

በእናት ላይ በጥናቷ ምትሃታዊ እውነታ ፍጹምነት፣ ቁጥብነት፣ ሊታመኑ የማይችሉ ገለጻዎች፣ የመንፈስ መናበብና ሌሎች ባህርያት ያሉት መሆኑንና እነዚህም በምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፍ ውስጥ እንደሚንጸባረቁ አሳይታለች።

ከላይ ለመመልከት እንደተሞከረው ምትሃታዊ እውነታዊነት ላይ የተጠኑ ጥናቶች አብዛኛዎቹ የምትሃት መገለጫ እና የምትሃታዊ ስነጽሁፍ ንጽጽሮሽ ትንተና ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው።

በዚሁ መስክ የሚጠኑ ጥናቶች በአብዛኛው የምትሃታዊ እውነታዊነትን መገለጫና ንጽጽር እንጂ ትርጓሜያዊ መነሻውን ትኩረት አድርገው እድገትና ጉዞውን፣ አዎንታዊና አሉታዊ ጎኑን፣ ተንትነው በማሳየት ረገድ ክፍተት ይታይባቸዋል፡፡

ይህ ጥናት የምትሃታዊ እውነታዊነት ንድፈ ሃሳብ ተመሳስሎነት እንጂ ከላይ በተዛማጅ ጽሁፎች አስረጂነት ከቀረቡት ጥናቶች ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት የሌለውና አዲስ ጥናት ነው፡፡ በመሆኑም በተጠቀሱት ጥናቶች ውስጥ የሚስተዋሉትን ተመሳሳይነት ያላቸውን የምትሃታዊ እውነታዊነት መገለጫ ማሳያና የንጽጽሮሽ ጥናትን መሰረት አድርጎ ኤጭ…! ልቦለድ ምትሃታዊ እውነታዊነት ስልት መቅረቡን ከመጽሃፉ በሚሰበሰቡ መረጃዎች አማካኝነት ማሳያ አድርጎ ማቅረብ ነው፡፡

የጥናቱን ዓላማ ከዳር ለማድረስ የምትሃታዊ እውነታዊነትን አሉታዊ ተጽዕኖ  በግልጽ በማሳየት ረገድ ኤጭ…! ልቦለድ የተሟላ ሆኖ በመገኘቱ ለታሰበው ጥናት ተመራጭ ሆኖ ተተንትኗል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የጥናቱ ስነ ዘዴና ንድፍ

ይህ ጥናት አይነታዊ የምርምር ስነ ዘዴን የተከተለ ሲሆን የመረጃ ትንተናው ደግሞ ማህበራዊ ሒስ ላይ ትኩረት በማድረግ የምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ ባህርያትን ከተሰበሰቡት መረጃዎች ጋር በማገናዘብ ይተነትናል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው መጽሃፍ ፍተሻን መሰረት አድርገው ለትንታኔ የሚመረጡት መረጃዎች በቁጥር መጠናዊ ሆነው የሚገለጹ ሳይሆን በትንተና የሚቀርቡ በመሆናቸው ነው፡፡ ይኸው ተተኳሪ ዘዴ ማን፣ ምን፣ እንዴት የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ስለሚያስችልና ማህበረሰባዊ ችግሮችንና በኤጭ…! ልቦለድ መጽሃፍ ውስጥ እንዴት እንደተንጸባረቁ ማሳያ አድርጎ ለማቅረብ የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡

## 3.1. የመረጃ ምንጭና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የመረጃ ምንጭ በመሆን የሚያገለግለው አዘርግ (2010) ኤጭ…! በሚል ያሳተመው መጽሃፍ ሲሆን ከመጽሃፉ የሚሰበሰቡት መረጃዎች የሚመረጡት በዓላማ ተኮር ዘዴ ጥልቅ ንባብን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

ይህም ሊሆን የቻለው የተመረጠው መጽሃፍ በምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ መቅረቡን ለማሳየት ስለሚያስችል ነው፡፡

በዚሁ መጽሃፍ ላይ የሚካሄደው ጥናትና ምርምር በተመሳሳይ መንገድ ጥናት ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች መነሻ ሃሳብ በመሆን እንዲያገለግልና በዚሁ መንገድ የሚከናወኑ ስነጽሁፋዊ ሒሶችን ለማጎልበት ጥሩ ማሳያ ይሆናል ተብሎ ስለታሰበ ጥናቱ ትኩረት ተደርጎበታል፡፡

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያነት የዋለው ጥልቅ ንባብ ዘዴ /closed reading/ ሲሆን ይህ ዘዴ ገቢራዊ የተደረገው በመረጃ ምንጭነት የሚያገለግለው መጽሃፍ በመሆኑ ነው፡፡ ቃለ መጠይቅና የጽሁፍ መጠይቅ በተወሰነ መልኩ ለመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሚያገለግሉ ቢሆንም ከዚህ ጥናት አንጻር ግን ያላቸው አስፈላጊነት ስላልታመነበት ጥቅም ላይ አልዋሉም፡፡ ምክንያቱም የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በጥልቅ ንባብ ዘዴ ኤጭ…! ልቦለድ በምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ መቅረቡን ማሳየት እንጂ የደራሲውን

የአጻጻፍ ቴክኒክ ከአንባቢ ተጽዕኖ አንጻር ወይም ደራሲው ከድርሰቱ ጋር ያለውን ዝምድና መገምገም ስላልሆነ ነው፡፡

## 3.3. የመረጃ አደረጃጀትና መተንተኛ ስልት

### 3.3.1. የመረጃ አደረጃጀት

የተሰበሰቡት መረጃዎች ለምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ ባህሪ ትንተና በሚያመች መልኩ ተደራጅተዋል፡፡ የአደረጃጀት ሒደታቸውም በክለሳ ድርሳናት የቀረቡትን የምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ ባህርያትን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

### 3.3.2. የመረጃ መተንተኛ ስልት

ለዚህ ጥናት በመረጃ መተንተኛነት የሚያገለግለው ማህበራዊ ሒስ ትወራ ሲሆን በዚሁ ስልት ከመጽሃፉ የተሰበሰቡ ምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግን መሰረት ያደረጉ መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተና

በምትሃታዊ እውነታዊነት የስነጽሁፍ ንድፈ ሃሳብ ዙሪያ በተለይም ከባህርያቱ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ በርካታ ሃሳቦች ይነሳሉ፡፡ Roh (1927) ተአምራዊ ክዋኔዎችን አጉልቶ ለማሳየት ጥረት ማድረጉን ተከትሎ በምትሃታዊ እውነታዊነት የስነጽሁፍ ዘወግ ጥናት መስክ የተሳተፉ ከጥናታቸው በመነሳት ምትሃታዊ እውነታዊነት የስነጽሁፍ ዘውግን ያሚላል ብለው ባሰቡት መንገድ የተለያየ የአከፋፈል ባህርያትን ተጠቅመዋል፡፡

በምትሃታዊ እውነታዊነት ባህርያት አከፋፈል ላይ ከተሳተፉ ምሁራን ውስጥ Wendy (1995፣167-174) Zomora (1995) እና Borges (1935) ይጠቀሳሉ፡፡ በዚህ ጥናት የምትሃታዊ እውነታዊነትን ጥቂር አስማት አሉታዊ ጎን በኤጭ ልቦለድ ውስጥ ማሳያ አድርጎ ለመተንተን ያመች ዘንድ ለምትሃታዊ እውነታዊነት ባህርያት መተንተኛነት ከ Taye (2012) ሊታመኑ የማይችሉ ድርጊቶችና ገጸባህርያት፣ ድብልቅነትና ጥንዳዊ ተቃርኖ የተወሰዱ ሲሆን ከ Mzegebuw (2012) ደግሞ የደራሲው ገለልተኛነት፣ ምስጢራዊነት እና የፖለቲካ ትችት ተወስደዋል፡፡

## የኤጭ…! ልቦለድ መጽሃፍ አጽመ ታሪክ

*ፍቅር አብርሃም ያልተማረ ቢሆንም በጥንቁልና አማካኝነት በአጭር ጊዜ ከፍተኛ ሃብት በማፍራት ታዋቂ ባለሃብት ለመሆን የበቃ ሰው ነው፡፡ ፍቅር አብርሃም በጥንቁልና ሳቢያ ያገኘውን ሃብት ሳይታሰብ እንዳያጣ ጠንቋዩ ያዘዘውን እየፈጸመ የገዟ ልጁን ሰብአዊነት በጎደለው ሁኔታ በመድፈሩ የገዛ ባለቤቱ በሽጉጥ ገድላው እራሷንም ታጠፋለች፡፡*

*ኢ-ሰብአዊ በሆነ ሁኔታ ጉዳት የደረሰባት እሌኒ አንድ የቀራት ዘመድ ከልጅነቷ ጀምሮ እያስጠና የማንበብ ፍቅር እንዲያድርባት በማድረግ ፍቅር እየሰጠ ያሳደጋት ብቸኛ አጎቷ ሶቅራጥስ ስምኦን ብቻ ነው፡፡ ሶቅራጥስ እሌኒን በመንከባከብ ከደረሰባት የስነ ልቦና ጉዳት እንድታገግም በማድረግ ወደ ቀደመ ሕይወትና ኑሮዋ ተመልሳ ትምህርቷን በመቀጠል ለትልቅ ደረጃ እንድትደርስ ማድረጉን የመጽሃፉ የመጀመሪያ ታሪክ ያስረዳናል፡፡*

*ሁለተኛዋ በቤተሰብ የዛር ውርስ ሳቢያ በጥንቁልና ተይዛ በገዛ አባቷ የተደፈረችው ሊሊ ሽመክት ስትሆን ሊሊ ለሶስት አመት የወሲብ ጥቃት እየደረሰባት በጠንቋይ ቤት ታስራ ከቆየች በኋላ አስማንዲዮስ በተባለ እርኩስ መንፈስ ትዕዛዝ በተለያዩ ከተሞች እየተዘዋወረች አንድ ሺ ባለትዳሮችን ከትዳራቸው የመበተን፣ ሶስት መቶ የሃይስኩል ሴት ተማሪዎችን በሌዚቢያኒዝም ተመሳሳይ ጾታ ግንኙነት እንዲጠቁ ማድረግና ሶስት መቶ ሕጻናትን እየሰረቀች ለእርኩስ መንፈስ አላማ መስዋዕት እንዲሆኑ አድርጋለች፡፡*

*ሊሊ ሽመክት ይህን በማድረጓ አስማንዲዎስ ለትንሽ ግዜ ተደስታ እንድትኖር ካደረጋት በኋላ በአንድ ዓመት ውስጥ ሁሉንም ነገር በማሳጣት ሕይወቷ ለአደጋ መጋለጡን አስነብቦናል፡፡*

*በምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ የቀረበው ኤጭ…! ልቦለድ በአስማት ሳቢያ እየደረሰ ያለውን ግለሰባዊ፣ ማህበረሰባዊና ሃገራዊ ጉዳት በዚህ መልክ ማሳያ አድርጎ አቅርቦታል፡፡*

## 4.1.1. ሊታመኑ የማይችሉ ድርጊቶችና ገጸባህርያት

በኤጭ…! ልቦልድ መጽሃፍ ውስጥ ሊታመን የማይችል ከባህል፣ ከወግና ልማድ ጋር የሚጣረስ ያልተገባ ድርጊት ሲከወን ይታያል፡፡

የምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ ክዋኔዎች የጥቁር አስማት ባህርይ ያላቸው በመሆኑ በድብቅና ሊታመን በማይችል መልክ እንዲሁም ሚስጢራዊ በሆነ መንገድ የሚከወኑ ናቸው፡፡ በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥም ይኸው ያልተለመደ ተግባርና የገጸባህርይ አሳሳል ጎላ ብሎ ቀርቧል፡፡ እሌኒ አባቷ በር ዘግቶ በተለየ ቋንቋ የተለየና ያልተለመደ ጸሎት የሚያደርግ መሆኑን ስትገልጽ እንመለከታለን፡፡

> አንዳንዴ የአባቴ ሁኔታ ግራ ያጋባኛል፡፡ ብቻውን የራሱ መኝታ ቤት ይቀመጣል፤ ብቻውን ያወራል፤ በተለይ እኔ የማላውቀውን ቋንቋ እየተጠቀመ ጸሎት ያደርጋል፡፡ አንድ ቀን በጠዋት ሲነሳ ሳያየኝ ተከተልኩት፡፡ ሳሎን ውስጥ ተንበረከከ፡፡ መብራቱን ሳያበራ ድምጹን መጠነኛ አድርጎ መጸለይ ገባ፡፡ እኔ ሰምቼ የማላውቀውን ቋንቋ እያወጣ ነበር፡፡ "ቅርጭናኤል፣ ከፍትናኤል አስታስቅሮል፣ ኪራቆስኤል፣ ሐበርጅን፣ ሐበርጅን እያለ (ገጽ፣18)፡፡

ያልተለመዱ ጉዳዮችን ቅደም ተከተላዊ ጉዞ ለማመላከት እሌኒ (ገጽ፣19) ላይ ትዝብቷን ስትሰነዝር ይታያል፡፡ "ሚያዚያ 25 የልደት በዓሌ በተከበረ ሶስተኛ ቀን ሚያዚያ 28 ዕለቱ ቅዳሜ ስለነበር ተኝቼ ነበር፡፡ አባቴ ገና በጥዋቱ እኔ ጋ በመምጣት ቀሰቀሰኝ፡፡ እንደተለመደው "የእኔ ውብ ልጅ" በማለት የሚያምሩትን ውብ ከንፈሮቼን ገመጣቸው፡፡ ከዚያም በፍቅር አይን እየተመለከተኝ "የእኔ ውብ ልጅ ተነሺና ሰውነትሽን ታጥበሽ ለልደትሽ ያመጣሁልሽን ያንን ውብ ልብስሽን ልበሺና ተዘጋጂ" አለኝ፡፡

እንዲህ አይነት ሊታመኑ የማይችሉ ድርጊቶችና ያልተለመዱ የገጸ ባህርያት ክዋኔዎች ከጀርባቸው አሉታዊ ጉዳይ የሚከናወን መሆኑን አመላካች ነው፡፡

ኤጭ...! ልቦለድ በምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ የቀረበ መሆኑን በመጽሃፉ ውስጥ በሚገኙ አስረጂዎች አማካኝነት መረዳት ይቻላል፡፡ በመጽሃፉ ውስጥ ጥቁር አስማትንና ጥንቁልናን ከሚያመለክቱ ሊታመኑ ከማይችሉ ድርጊቶችና ገጸ ባህርያት አሳሳል አንጻር እሌኒ ፍቅር በጥንቁልና ሰበብ ደርሶብኛል የምትለው ችግር አንዱ ማሳያ ሆኖ ቀርቧል፡፡

> መሪጌታ ከትልቁ ሶፋ ወንበር ላይ በእርጋታ ተቀመጠ፡፡ በእነዚያ ግዙፍ አይኖቹ በትኩረት ተመለከተኝ፡፡ እጁን ዘረጋልኝ፡፡ ውስጤ እና ስድስተኛው ስሜቴ ይህን አላስፈላጊ ሰው እባክሽ አትጨብጪው አለኝ፡፡ ሳየው ሁሉ በማላውቀው ስሜት አስጠላኝ ግን ለአባቴ ቃል ስለገባሁለት እጄን ዘረጋሁለት፡፡ አንዳች አይነ ምድር እንደሚነካ ሰው ቢቀፈኝም እሱ ግን በጣም አጥብቆ ጨበጠኝ፡፡
>
> "በጣም የምታምሪ ልጅ ነሽ!"
>
> "ይሆናል"
>
> "ማን ነው ስምሽ?"
>
> "እሌኒ" አልኩ ግንባሬን ቋጥሬ፡፡
>
> "በትምህርት ጎበዝ እንደሆንሽ ሰማሁ"
>
> "የሰማኸው ልክ ይሆናል"

"እስቲ የግራ እጅሽን አምጪ"

"ለምን?"

> አባቴ ወዲያው በዓይኑና በግንባሩ ተቆጣኝ፡፡ ከዚያ እኔም ለመሪጌታው የግራ እጄን ሰጠሁት፡፡ መሪጌታው የግራ እጄን ለተወሰኑ ሴኮንዶች ጨመቃቸው፡፡ ከዚያ እጄን ለቀቀኝና ከተቀመጠበት በመነሳት እንደ አባቴ በማላውቀው ቋንቋ ይጸልይ ገባ..."ጀጀሀሜ፣ ጀጀሃሜ፣ ጸጸርኤል፣ ጸጸርኤል፣ አጥንዮንዮስ፣ አጥንዮንዮስ፣ አጥንዮንዮስ፣ ሐርጀምን፣ ሐርጀምን፣ ሐርጀምን..." ምናምን አለ፡፡ ከዚያ በትኩረት እያየኝ ተመልሶ ተቀመጠ፡፡ አባቴን እየተመለከተው "በጣም ትክክለኛ ሰአት ነው፡፡ ከሶስት ቀናት በኋላ የወር አበባዋን ታያለች እንኳን ደስ አለህ" አለው፡፡ እኔን ተንኮለኛ በሚመስል ፈገግታ እየቃኘኝ (ገጽ፣21-22)፡፡

በኤጭ...! ልቦለድ ውስጥ ጥቁር አስማት በጥንቁልና በኩል ያልተገባ ድርጊትና የገጸባህሪ ክዋኔ ሲፈጸም የሚያሳየን፣ ሰዎች ለኔ ብቻ በሚል በዘመናዊነት እሳቤ ተጠልፈው የሚባዝኑት ከፈጣሪ ቸርነት ይልቅ ለገንዘብ አምልኮ እራሳቸውን አሳልፈው በመስጠት እንደሆነ የምትገልጸው እሌኒ ፍቅር በጥንቁልና ሳቢያ ለጉዳት መጋለጧን መጽሃፉ ይጠቁመናል፡፡

ገንዘብ ለማግኘት ሲባል የሚካሄድ የጥንቁልና ተግባር ሊታመን የማይችል እና ያፈነገጠ ድርጊት መፈጸሚያ መሆኑን በኤጭ...! ልቦለድ በርካታ ማሳያዎች አማካኝነት መመልከት ይቻላል፡፡

> የገንዘብ አምልኮ የሃጢያት ሁሉ የደም ስር ነው፡፡ ገንዘብ ለአምልኮ ተግባር ከዋለ አዕምሮን አውሮ የማይደረገውን ሁሉ ያስደርጋል የሚባለው ትንቢት በእኔ ላይ ተፈጸመ፡፡ የገንዘብ አምልኮ የሃጢያት ሁሉ የደም ስር ነው፡፡ እናም የእኔ ደም በጠንቋይ ቤት መፍሰስ ለአባቴ የሀብት ማሰሪያ ውል ነበር፡፡ አባቴ ለገንዘብ ሲል አእምሮው ታውሮ ነበር፡፡ ለገንዘብ ሲል ከገዛ ልጁ ጋር ወሲብ ማድረግ፣ የገዛ ልጁን መድፈር፣ የገዛ ልጁን ማስደፈር ነበረበት! ይህ የእኔ እሌኒ ፍቅር አስቀያሚ ታሪክ ነው (ገጽ፣29)፡፡

መጽሃፉ በጥቁር አስማት አሉታዊ ስልት መቅረቡን ለመረዳት ከላይ የቀረበው የመጽሃፉ ሃሳብ ጥሩ ማሳያ ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

አቤነዘር (2012) ምትሃታዊ ድርጊቶች በተለያዩ አጋጣሚዎች ይከሰታሉ እነዚህ ምትሃታዊ ድርጊቶች ሊታመኑ የማይችሉ ሲሆኑ ከጀርባቸው ምክንያታዊ የሆነ አስረጂ አይኖርም፡፡ የልቦለድ አቀራረቡ የተወሳሰበ መሆኑ የእውነታው ዓለም ቁም ነገሮች በሚቀርቡት የሕይወት ሁኔታዎች ብቻ እንዲወሰኑ ያደርጋል፡፡

በምትሃታዊ እውነታዊነት ለሉታዊ ጎን የአጻጻፍ ስልት የቀረበው ኤጭ…! ልቦለድ ሊታመኑ የማይችሉ ድርጊቶች፣ ማግኘትና ማጣት፣ መንፈሳዊነትና ሰይጣናዊነት፣ ሕይወትና ሞት፣ ገንዘብና አምልኮ ሲፈራረቁ ያሳየናል፡፡

የምትሃታዊ እውነታዊነትን ዘውግ በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ እሌኒ ፍቅር በጥንቁልና ሳቢያ በገዛ አባቷ የመደፈር ያልተለመደ ድርጊት እንዳለ ሆኖ በመጽሃፉ ውስጥ ተመሳሳይ ታሪክ ያላት ሊሊ ሽመክት በጥንቁልና ዛር ውርስ ሳቢያ በገዛ አባቷ ተደፍራ ለጠንቋይ ቤት ተላልፋ እንደተሰጠች በማመልከት ያልተለመደ የእርኩስ መንፈስ ክዋኔ መፈጸሙን ይጠቁመናል፡፡

> እኔ የተወለድኩባቸው ቤተሰቦች በዛር መንፈስ ለተወረሰ የቃልቻ መንፈስ እራሳቸውን ለተለያዩ አጋንንት አሰራሮች የሸጡ እና ለሰይጣን አምልኮ እራሳቸውን አሳልፈው የሰጡ ናቸው፡፡ እኔም ከልጅነቴ ጀምሮ ለቃልቻ ግብር የተሰጠሁ ሴት ነበርኩ፡፡ በግድ ደፍሮኝ ሳይሆን በከፍተኛ ልመና አግባብቶኝ የመጀመሪያ ወሲቤን ያደረግሁት ለሰይጣን አሳልፎ ከሰጠኝ እውነተኛ አባቴ ጋር ነበር (ገጽ፣101)፡፡

ምትሃት ወይም አስማት ከአዎንታዊ ተግባር ይልቅ ለአሉታዊ ተግባር ሲውልና ማህበረሰባዊ ቀውስ ሲያስከትል እንዲሁም ተጽዕኖው በተለያየ መንገድ እየተስፋፋ መሆኑን የሚያመለክተው ኤጭ…! ልቦለድ ከተለመደው ውጪ የሆነ የጥቁር አስማት ክዋኔ መፈጸሙን በመጠቀም ልብ እንድንል ማሳያ አድርጎ አቅርቦልናል፡፡

ሊሊ ሽመክት በጥንቁልና በተመራ መንፈስ ተሞልታ ለአጋንንት አሰራር በተዘጋጀችበት ወቅት ከተለመደው ሰዋዊ ሕይወት ተሻግራ ሌላ ሴት መሆኗን ስትናገር (ገጽ፣105 እና 106) መመልከታችን ኤጭ…! ልቦለድ በምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ ስለመቅረቡ አንዱ ማሳያ ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

ሌላ ሴት እንደሆንኩ ለራሴ በጣም ይታወቀኛል፡፡ ውስጤ የነበረው ያ የፍርሃት መንፈስ አሁን የለም፡፡ በኩራት እየተጀነነች የምትራመድ ወጣት ሆኛለሁ፡፡ እንግሊዝኛ ሲያወሩ ትርጉሙ በሚገባ ይገባኛል፡፡ ትግርኛ፣ ወላይትኛ፣ ኦሮምኛ ሁሉንም ሲያወሩ ትርጉሙን እችላለሁ ይህ ተዓምር አይደለምን?፡፡

በኤፍ...! ልቦለድ ውስጥ በጥንቁልና ሳቢያ የደረሰባትን ችግር በራሷ አንደበት የምትተርከው ሊሊ ሽመክት በአጋንት መንፈስ በመሞላቷ ሌላ ሴት በመሆን ሊታመን የማይችል ክህሎት ባለቤት መሆኗን ስትገልጽ እንመለከታለን፡፡ ገጸባህሪዋ ሊሊ ሽመክት ሊታመን የማይችል ሃይል ለጊዜው ከሰይጣን ብትቀዳጅም የኋላ ኋላ ግን ሁሉም ከንቱ ስለመሆኑ ትናገራለች፡፡ "ሰይጣን ሀይል ይሰጣል፤ ግን የሚሰጣችሁ ላለመስጠት ነው ይህ የሰይጣን እንቆቅልሽ ነው" (ገጽ፣108)፡፡

በኤፍ...! ልቦለድ ውስጥ ሊታመኑ የማይችሉ ድርጊቶችና ገጸ ባህርያት የመጽሃፉን አሉታዊ የምትሃታዊ እውነታዊነትን አጻጻፍ ስልት ከመጠቀም ባለፈ መጽሃፉ በዚሁ መንገድ መቅረቡን ማሳያ ሆኖ ሲገለጥ ያሳየናል፡፡

የሚገርም የሚያስደንቅና የማይታመን ነው፡፡ ለመሆኑ ውስጤ የነበረው ፍርሃት የት ጠፋ? ውስጤ የነበረው ሰውን ቀና ብሎ ያለማየት ፍርሃት የት ጠፋ? ያቺ ሰዎችን ቀና ብላ ማየት እንኳ የማትችል ቦቅቧቃ ሴት አሁን በአንድ ጊዜ እንዴት ደፋር ሆነች? አስማንዲዮስ ጨርሶ ሌላ ሴት እንዳደረገኝ በእርግጠኝነት አወኩኝ፡፡ እኔ ፍጹም ሌላ ሴት ሆንኩኝ፡፡ ሌላ ማንንም የማትፈራ ደፋር አንገቷን ቀና አድርጋ መንቀሳቀስ የምትችል በአንዳች አስገራሚ በራስ መተማመን መንፈስ የተሞላች ቆፍጣና ሴት፤ እነሆ ሰይጣን በእግሩ ስር ለወደቁት እና አንተ አባታችን ነህ ብለው አምነው ራሳቸውን አሳልፈው ለሸጡለት በሀይል ይሞላቸዋል፡፡ ሰይጣን ከጸሃይ በታች የሆነችው ምድር የእርሱ ናትና ያልሆነውን እንድንሆን ያደርጋል፡፡ ለሰይጣን እኛን በሃይል መሙላት በጣም ተራ እና ቀላል ነገር ነው፡፡ ለሚያመልኩት መሻታቸውን ላለመስጠት ይሰጣል፡፡ የሚሰጣችሁ ግን ላለመስጠት መስጠትን ነው (ገጽ፣107-108)፡፡

ሊሊ ሽመክት ከአስማንዲዮስ ሰይጣናዊ መንፈስ ጋር ያደረገችው ምልልስ መጽሃፉ የተጻፈበትን አሉታዊ የምትሃታዊ እውነታዊነት ጭብጥ ማሳያ ሆኖ መቅረቡን

እንድንመለከት ያደርገናል፡፡ ሊታመን የማይችለው መናፍስታዊ ድርጊት ሊሊ በሕይወት ያለፈችበት አስደንጋጭ ታሪክ በመሆኑ ውስብስብ የነበረው ግለ ታሪኳ ሰፊ ዝርዝር ያለው ሲሆን እናያለን፡፡ ሰይጣን ሁሉንም ሰጣት መልሶ ደግሞ ሁሉንም ነጠቃት፡፡ ይህም ክስተት ኤጭ…! ልቦለድ አሉታዊ የጥቁር አስማት ጎጂ ጎን ሆኖ መቅረቡን እንመለከታለን፡፡ የአስማንዲዮስ እርኩስ መንፈስ ሊሊ ሽመክትን ብር በመስለብ ሊታመን በማይችል መንገድ ሃብት እንድታገኝ ሲያደርጋት (ገጽ፣146) የምንመለከተውም ለዚሁ ነው፡፡

> ዛሬ ታላቁን የአገልግሎት ዋጋሽን ለመቀበል ዝግጁ ነሽ?" "በሚገባ አባታችን" "አልጋሽ ስር የጅብ ኩላሊት አለ፡፡ ይህን ኩላሊት ጠዋት ጠዋት እየነካሽ ከቤት ውጪ ለሃያ ቀናት የፈለግሽውን ያህል ብር ከባንክ ቤቶች እና ዶላር መንዛሪዎች እንድትሰልቢ የመስለብ ጸጋን ሰጥቼሻለሁ፡፡ ታዲያ ማንኛውንም ብር ለመስለብ አስቀድመሽ የአንቺን ብር ማስነካት አለብሽ የብር መስለቡን ለሃያ ቀናት ብቻ በቀን ለሁለት ጊዜያት ብቻ ከአርባ ሰዎች ከሰለብሽ ይበቃል፡፡

እንዲህ አይነት ከተለመደው ሰዋዊ ኑሮና ሕይወት ያፈነገጠና ሊታመን የማይችል ድርጊት በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ መታየቱ መጽሃፉ አሉታዊ የምትሃታዊ እውነታዊነት መገለጫ በሆነው በጥቁር አስማት ፈርጅ መዘጋጀቱን ሊታመኑ በማይችሉ ድርጊቶችና ገጸባህርያት ማሳያነት መረዳት እንችላለን፡፡

## 4.1.2. መቀላቀል ወይም ድብልቅነት /Hybridity/

የምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፍ ሌላኛው ባህሪ ድብልቅነት ነው፡፡ በድብልቅነት ባህሪ ውስጥ ሕይወትና ሞት፣ እርኩሰትና ቅድስና፣ ጥሩና መጥፎ ሊገናኙ ወይም የተለመደውን እውነት ጥሰው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ በኤጭ…! ልቦለድ አሉታዊ የምትሃታዊ እውነታዊነት አቀራረብ ውስጥ የእሌኒ አባት ፍቅር አብርሃም የጥንቁልና ርኩስ መንፈስን ከሃይማኖታዊ ስርአትና ሕግጋት ጋር ሲያቀላቅል ወይም ሲያደባልቅ ይታያል፡፡ አቶ ፍቅር አብርሃም ቤት ውስጥ ለሰይጣን እየጸለየ በአደባባይ ደግሞ ቤተክርስቲያን ሲሳለም መታየቱ ሁለት የማይገናኙ ነገሮችን በማደባለቅ የተለመደውን ሕግ መጣሱን እንድንታዘብ ያደርገናል፡፡

በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ አቶ ፍቅር በጥንቁልና አማካኝነት ሃብት ለማግኘት በምስጢር በጥንቁልና ሳቢ.ያ ለሰይጣን ማደሩን እንመለከታለን፡፡ ቤቱ ውስጥ መኝታ ቤቱን እየዘጋ ይህንኑ ሚስጢራዊ የእርኩስ መንፈስ ጸሎት በተለየ ቋንቋ እንደሚጸልይ ልጁ እሌኒ ተደብቃ በማየት አረጋግጣልናለች፡፡ በሌላ በኩል አቶ ፍቅር ሐይማኖተኛ ለመምሰል ቤተክርስቲያን እየሄደ ጸሎት ያደርጋል፡፡ ለድሆች ሳንቲም በመስጠት ሰብአዊነት የተላበሰ ሰው ለመምሰል ይሞክራል፡፡ አቶ ፍቅር በዚሁ ድብቅነቱ ጽድቅና ኩነኔ፣ አማኝነትንና ኢ-አማኝነትን፣ መንፈሳዊነትንና የአጋንት አሰራርን ሲያደባልቅ መመልከታችን የምትሃታዊ እውነታዊነት አንዱ ባህሪ ስለመከሰቱ የምንታዘብበት ነው፡፡

የእሌኒ አባት ባንድ በኩል ችግረኛን በመርዳት የእግዚአብሔርን መንገድ ሲከተል ይታያል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የእርኩስ መንፈስን ስውር ተልዕኮን እያስፋፋ ሃብቱን ያሳድጋል፡፡ ይህም ሁኔታ ጽድቅና ኩነኔ ሲደባለቁ እንድንመለከት ያደርገናል፡፡

> ከአባቴ ጋር አስቦበት ሳይሆን እንደው ድንገት አንዳንዴ በመኪና ሳይሆን በእግራችን መንገድ ስንሄድ አባቴ ለማኝ ሲያገኝ አስር አስር ብር እያወጣ በታላቅ መከፈስ ይሰጣቸዋል፡፡ በጣም አሮጊቶች ከሆኑ ደግሞ ሃምሳ ብር የሚሰጥበት ጊዜም አለ፡፡ ይህ ጉዳይ ግራ ስለሚገባኝ አባቴን መጠየቅ ፈለኩ፡፡ "አባቴ ለለማኝ ገንዘብ መስጠት አስፈላጊ ነው? ስራ እንደይሰሩ ማስነፍ አይሆንም?" ስል ጠየኩት እሱም "ችግረኞችን መርዳት ያጸድቃል! አየሽ ገነት መግባት ከፈለግሽ ለማኝና ችግረኛን መርዳት አለብሽ፡፡ ሕግ ነው? ነገርኩሽ እንግዲህ!" በማለት ተቆጣኝ (ገጽ፣7)፡፡

በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ ሁለተኛ ባለታሪክ ሆና የቀረበችው ሊሊ ሽመክት በተመሳሳይ በገዛ አባቷ ተደፍራ ለጠንቋይ ቤት ተላልፋ የተሰጠችና ብዙ ችግር የደረሰባት ስትሆን በቃልቻ ቤት ታስራ ካዳሚ በነበረችበት ወቅት ምንም አይነት ትምህርት የሌላት መሆኑን ከቀረበው ትረካ እንረዳለን፡፡

ሊሊ የአስማንዲዮስን መንፈስ ወደ ተለያዩ ባለትዳሮች እንድታስተላልፍ በእርኩስ መንፈስ ከተሞላች በኋላ ግን ምንም ሳትማር ማንኛውንም መጽሃፍ በማንበብ በአንድ ጊዜ በርካታ ቋንቋ መስማትና መናገር መቻሏ አስገራሚ ከመሆን ባለፈ ማወቅና

አለማወቅ ያለምንም ምክንያታዊ ሽግግር ተደባልቀው አንደኛው ሃሳብ ሌላኛውን ሃሳብ ሲሽር እንመለከታለን፡፡

በኤጭ…! ልቦለድ ትረካ ውስጥ ሁለት ሊገናኙ የማይችሉ ነገሮች ተደባልቀውና ተፈጥሮዋዊውን ህግ ጥሰው እንመለከታለን፡፡ ከነባራዊው እውነታ የሚለየው ይኸው ጉዳይ የሰው ልጅ እንዴት ፊደል ሳይቆጥር በአንድ ጊዜ የተማረ ሆኖ በርካታ ነገሮችን ሊያቀላጥፍ ይችላል እንድንል ያደርገናል፡፡ ምክንያቱም ሁለት የማይገናኙ እውነታዎች ተደባልቀውና እውነታው ተጥሶ መታየቱ የመጽሃፉን በምትሃታዊ እውነታዊነት ጥቁር አስማት አሉታዊ ጎን መቅረቡን አመልካች ነው፡፡

> ለማንኛውም ካፍቴሪያው ጥግ የተቀመጠ አንድ ዝንጥ ያለ ወጣት ተመለከትኩ ከሌሎች ትኩረቴን እና አይኔን የሳበው መጽሃፍ እያነበበ ስለተመለከትኩት ነው፡፡ ስለ እርግዝና የሚያወራ መጽሃፍ ነበር የሚያነበው፡፡ የሚገርመው እኮ ከዚህ በፊት ለዘመናት በእስር በነበርኩበት በቃልቻው ቤት ውስጥ ቡና ከማፍላት፣ ሳር ከመጎዝጎዝ፣ እጣን ከማጫጫስ እና ሐሙስ ሐሙስ ራሴን ለወሲብ ከማዘጋጀት ባለፈ ትምህርት ቤት ሂጄ አላውቅም፡፡ ሀቁን ለመናገር የአማርኛ ፊደል ዘርን ሀ ሁ ሂ…እንኳ አላውቅም ታዲያ እንዴት ማንበብ ቻልኩኝ? ይህ ሊሆን የቻለው አባታችን አስማንዲዮስ በሞላኝ ጸጋ ነው፡፡ እንኳን የሀገሬን አማርኛ ቀርቶ እንግሊዝኛን አብጠርጥሬ አነባለሁ (ገጽ፣108)፡፡

የቀረበው ሃሳብ ሊሊ ሽመክት ምንም አይነት ትምህርት እንደሌላት ስትገልጽ ብንመለከትም ለእርኩስ መንፈስ ተልዕኮ ከታጨች በኋላ ግን በአንድ ጊዜ አማርኛን ከማንበብ አልፋ እንግሊዝኛ ሳይቀር የማንበብ ሃይል እነደተጎናጸፈች ከኤጭ…! ልቦለድ ትረካ እንረዳለን፡፡

ኤጭ…! ልቦለድ በጥቁር አስማት የምትሃታዊ እውነታዊነት አሉታዊ ጎን መቅረቡን ለማመልከት ተራኪው የምትሃታዊ እውነታዊነት ባህሪ የሆነውን ድብልቅነት ሲጠቀም ይታያል፡፡ በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ መንፈሳዊና ሰይጣናዊ፤ ሕይወትና ሞት፤ ቅድስናና እርኩሰት፤ መናፍስትነትና መለኮታዊነት ሲደባለቁ እና ሲቀላቀሉ የምንመለከተውም ለዚሁ ነው፡፡ መጽሃፉ በሊሊ ሽመክት ሕይወት ውስጥ ዝነኛነትና

ተራነት፣ እውነትና ሐሰት፣ ትክክልና ስህተት፣ ቆንጆና አስጠሊታ ድብልቅ ጉዳይ ሆነው መቅረባቸውን ያሳየናል፡፡

> በዝምታ መጠጤን እየተጎነጨሁ እና የተማሪዎችን ዳንኪራ እየኮመኮምኩ አያለሁ፡፡ ቆንጆም አስጠሊታም ያልሆነ በቅርቡ ክብደት ማንሳት መጀመሩ የሚያሳብቅበት ወጠጤ ወጣት አጠገቤ መጥቶ "Famous ተቃራኒው Notorious ነው፡፡ True ተቃራኒው false ነው፡፡ Truth ተቃራኒው error ሲሆን Ugly ደግሞ ተቃራኒው beautiful ነው፡፡ አንቺ ደግሞ beautiful ስለሆንሽ አጠገብሽ ልቀመጥ አለኝ (ገጽ፣141-142)፡፡

Encarta (2009) መዝገበ ቃላት ንጥረ ነገሮችን በማቀላቀል እንደ ድቅል በማየት ይተረጉማቸዋል፡፡ ከተለያዩ አካላት ወይም ገጽታዎች ድብልቅ የተሰራ ነገር አስማታዊ እውነታዊነት በእውነታው የተያዙ በርካታ መቀላቀሎች የሚስተዋሉበት መሆኑን ይገልጻል፡፡

### 4.1.3. የደራሲው ገለልተኛነት እና ተጨባጭ ማስረጃ አለማቅረብ

በምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፍ ተራኪው ትክክለኛ ገለጻዎችን በልቦለዱ ውስጥ አያቀርብም፡፡ የሚቀርቡት የገጸባህርያት ድርጊቶች ሊታመኑ የማይችሉ ከመሆን ባለፈ ተጨባጭ ማስረጃ የሚቀርብባቸው አይደሉም፡፡ ይልቁንም ደራሲው በተለየ መንገድ አስገራሚ ሁነቶችን በመጨመር የተጀመረው ታሪክ በጥንቃቄ እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡ ያልተለመዱ ነገሮች እንደተራ ሆነው ይቀርባሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተራኪው ገለልተኛ ሲሆን እንመለከታለን፡፡

በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ ሊሊ ሽመክት አስማንዲዮስ ከተባለ በዝሙት ሳቢያ ትዳርን ከሚያናጋ እርኩስ መንፈስ ተጽዕኖ ስር ሆና በተቃርኖ የታዘዘችውን ስትፈጽም ተራኪው ያሳየናል፡፡ በዚህ የተቃርኖ ትረካ ውስጥ ደራሲው ገለልተኛ በመሆን የታሪክ ጭብጡን አጠናክሮ ሲቀጥል እንጂ እንዴት ሊሆን ቻለ ለሚለው ጥያቄ ተጨባጭ ማስረጃ ሲያቀርብ  አንመለከትም፡፡ የምትሃታዊ እውነታዊነት አሉታዊ የጥቁር አስማት ባህሪ በደራሲው ገለልተኛነትና ተጨባጭ ማስረጃ አማካኝነት በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ ማሳያ ሆኖ ሲንጸባረቅ እናያለን፡፡

አንቺ የእኔ ነሽ! በአባትሽ በኩል በአንቺ ውስጥ በወሲብ አማካኝነት ደሜን ከደምሽ ቀላቅያለሁ፣ መንፈሴን ከመንፈስሽ አዋህጃለሁ፣ ያንቺ ነፍስና እስትንፋስ የእኔ ነች፡፡ ስለዚህ አንቺ የእኔ ንብረት ነሽ ከእኔ ጋር ዋጅቼሻለሁ! ንብረቴ አድርጌሻለሁ! ከዛሬ ጀምሮ የእኔን ስራ ብቻ ትሰሪያለሽ! ከእኔ ማምለጥ አትችይም ቀላል ስራ ትሰሪያለሽ! በመጨረሻም የክብር ስጦታ አበረክትልሻለሁ፡፡ "ምንድነው ስራው?" "እንዳልኩሽ የምጠራው አስማንዲዮስ እየተባልኩ ነው፡፡ እኔ የጥልቁ መንፈስ አባል ስሆን በትዳር ማናጋት ላይ የተመደብኩ እና ሰዎችን በወሲብ ወጥመድ የማስር ነኝ! አንቺን ለዚህ አላማዬ በክብር መርጬሻለሁ በመሆኑም ጊዜሽ ስለደረሰ ከእኔ ጋር ትሰሪያለሽ!"፡፡

"ምን?"

"ከአንድ ሺ ሰዎች ጋር ዝሙት ትፈጽሚያለሽ"

"በጭራሽ ይህን ማድረግ አልችልም"

"ትችያለሽ! በአባትሽ በኩል አንቺ ውስጥ ገብቻለሁ፡፡ አንቺ የእኔ ነሽ እናም ትችያለሽ"

"አላደርገውም"

"በትህትና የጠየኩሽን እንቢ ካልሽ ቀላል ቅጣት እቀጣሻለሁ"

"የምን ቅጣት"

"ይቅር በለኝ ጌታዬ አስማዲዮስ ሆይ ብለሽ ስሜን እየደጋገምሽ በክብር እስከምትጠሪ ድረስ እቀጣሻለሁ" መልሴን ሳይጠብቅ ተሰወረ፡፡

(ገጽ፣102-103)፡፡

ሊሊ ሽመክትን የእርኩስ መንፈስ መገለጥ የሆነው አስማንዲዮስ በአባትሽ አማካኝነት አንቺ ውስጥ በመግባት ደሜን ከደምሽ ጋር አዋህጃለሁ በሚል ትዕዛዝ ሰጥቷት የሚሰውር መሆኑን ተራኪው ቢያስረዳንም ለትረካው ግን ተጨባጭ ማስረጃ ሲያቀርብ አይታይም፡፡ ለክንውኑ መካሄድም ይህ ነው የተባለ ተጨባጭ ማስረጃ አያቀርብም፡፡ ሊሊ ከአስማንዲዮስ ጋር በመነጋገር ትዕዛዝ ስትቀበል በአካል መገለጥ ሳይኖር እንዴት

እንዲህ ሊሆን ይችላል ለሚለው ጥርጣሬ ትክክለኛ መረጃ አይሰጥም፡፡ ደራሲው ለተከናወነው ድርጊት መነሻ ምክንያት በእርኩስ መንፈስ በመሞላት ጉዞ ውስጥ ሰዋዊ ሁነት የተቀየረበትን መንገድ ገለልተኛ ከመሆን አልፎ ተጨባጭ የሆነ ማስረጃ አያቀርብልንም፡፡

እንዲህ አይነት መናፍስታዊ ክዋኔ በኤጭ…! ልቦለድ የትረካ አቀራረብ ስልት ውስጥ መጽሃፉ የቀረበበትን ጭብጥ ማሳያ አድርጎ አቅርቦልናል፡፡ በኤጭ …! ልቦለድ (ገጽ፣103) ላይ ተራኪው ይህንኑ ማሳያ ያስነብበናል፡፡

> ይህ በሆነ ሁለተኛ ቀን ሙሉቀን ሲነስረኝ ዋለ፡፡ ይህ አልበቃሽ ብሎኝ አመሻሽ ላይ ነስሩ ሲቆም መላው ሰውነቴ በብጉር ተወረረ፡፡ ምን ይሄ ብቻ በየአንድ ሰዓት ልዩነት ውስጥ ከብልቴ ትል መውጣት ያዘ፡፡ በቃላት የማይገለጽ ሕመም፤ በቃላት የማይገለጽ ስቃይና መከራ በዛብኝ፡፡ እናም ይህን ስቃይ ጨርሶ ልቋቋም አልቻልኩምና ይህ በሆነ በነጋታው ያለኝን ሀይል አሰባስቤ ምሽቱን ጠብቄ "ይቅር በለኝ ጌታዬ አስማንዲዮስ ሆይ" በማለት ጥሪ አሰማሁኝ፡፡

ሊሊ ሽመክት የአስማንዲዮስን ትዕዛዝ አልቀበልም በማለቷ አስማንዲዮስ ያሰቃያታል፡፡ ሆኖም ግን ደራሲው ይህ ድርጊት እንዲህ ሊሆን የቻለው በዚህ ምክንያት ነው የሚል ተጨባጭ ማስረጃ ካለመስጠቱም በላይ ገለልተኛ ሆኖ ሲተርክ እንመለከታለን፡፡

በትዳር ጥምርታ ውስጥ አንድ ወንድ ለአንድ ሴት፤ አንድ ሴት ለአንድ ወንድ፤ የሚለው ማህበረሰባዊ ልማድ ትላንት የነበረ፣ ዛሬም ያለ፣ ነገም የሚቀጥል ሀገራዊ እሴት ነው፡፡ በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ ግን ይህ ነባራዊ እሴት ሲጣስ ይታያል፡፡ ደራሲው ይህን ታሪክ በገለልተኝነት ሲተርክ ባልና ሚስት ለምን ከማህበረሰባዊ ህግጋት እንደሚያፈነግጡ ተጨባጭ የሆነ ማስረጃ አያቀርብም፡፡

ተራኪው በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ በተደጋጋሚ ከመናፍስት ጋር የሚደረግ የሃሳብ ልውውጥ መኖሩን ያሳየናል፡፡ ይኸው ጉዳይ የጥቁር አስማት አሉታዊ ባህሪ ማሳያ በመሆን ቢገለጽም ከመናፍስት ጋር የሚደረገው ቃለ ምልልስ ግን እውናዊ ሆኖ በተጨባጭ ማስረጃ የሚረጋገጥ አይደለም፡፡

> ከምሽቱ 6፡45 ደቂቃ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ወሊሶ ያነጋገረኝ መልኩን አሁንም ጥርት አድርጌ ለማየት ያስቸገረኝ አባታችን አስማንዲዮስ መጣ፡፡ በደስታ

ውስጤ ቀለጠች፡፡ "የእኔ ትዕዛዝ ተቀባይ በስራሽ ኮርቼብሻለሁ! ሽልማትሽ በዕጥፍ ያድግልሻል፡፡ ከዚያ በፊት ግን አሁንም አንድ ቀላል ስራ ይሰጥሻል፡፡ አይ! የመጀመሪያ ሽልማቴን ብቻ አሁን እፈልጋለሁ ካልሽም እሰጥሽና በድጋሚ አንቺ ጋ አልመጣም፤ ግን ለአንቺ የሚሆነውን እኔ ስለማውቅ የእኔን ፍላጎትና ምርጫ ብትጠቀሚበት የተሻለ ነው፡፡ ላንቺም የሚሻለው ያ ነውና!" "ያልከው ይሁን አባታችን!" በጣም ጥሩ ልጅ! ሁለተኛው ስራሽ ሶስት መቶ የሀይስኩል ሴት ተማሪዎችን በሌዚቢያኒዝም መንፈስ መሙላት ነው (ገጽ፣136)፡፡

በመጽሃፉ የተጠቀሰው ሃሳብ ከመናፍስት ጋር ለሚደረገው ትእዛዝ የማስተላለፍና ትዕዛዝ የመቀበል የሁለትዮሽ ግንኙነት ተራኪው ገለልተኛ ሆኖ ከመታየት ውጪ ለገለጻዎቹ ተጨባጭ የሆነ ማስረጃ አያቀርብም፡፡

የምትሃታዊ እውነታዊነት ባህሪ የሆነው የደራሲው ገለልተኛነት ተጨባጭ መረጃ የማይሰጥበት በመሆኑ የሚካሄደው ክዋኔ በምክንያታዊነትና ውጤት የታጀበ አይደለም፡፡ ባለታሪኳ ሊሊ ሽመክት በመናፍስት ትዕዛዝ እየተመራች ያደረገችው አሉታዊ ድርጊት በትረካው ውስጥ ቅደም ተከተሉን ይዞ የሚሔድ እንጂ ደራሲው በተጨባጭ ማስረጃ አስደግፎ ምላሽ የሚሰጥበት ሲሆን አንመለከትም፡፡ ይህም የምትሃታዊ እውነታዊነት አንዱ አሉታዊ ባሕሪ መሆኑን ኤጭ…! ልቦለድ እንድንገነዘብ ያደርገናል፡፡

ሊሊ ሽመክት ለገባችበት ችግር ይህ ነው የተባለ ተጨባጭ ማስረጃ ባታቀርብም በዘር ውርስ ሳቢያ ለጥንቁልና ዛር ተላልፋ ስለመሰጠቷ ትገልጻለች፡፡

ይህ ታሪክ የእኔ የሊሊ ሽመክት እውነተኛ ታሪክ ነው የምትለው ገጸባህሪዋ አስማታዊ ድርጊት ስትከውን የሚሆነው ጉዳይ እና በዚሁ ሳቢያ የደረሰባትን ችግር ስትናገር እንጂ ስለ ደረሰባት ክስተት የራሷ የሆነ ምክንያታዊ ማስረጃ አታቀርብም፡፡ በዚሁ ሳቢያ ሊሊ በኔ የደረሰ እንዳይደርስባችሁ መጠንቀቅ ይገባል ማለቷን ተራኪው ገለልተኛ ሆኖ ያስረዳናል፡፡

ይህ የእኔ የእሌኒ ፍቅር ታሪክ ነው፡፡ በሃሳብ የተንጸባረቀ ፈጠራ ሳይሆን በኢትዮጵያ ላይ የተከናወነ እውነተኛ ታሪክ ነው፡፡ ዛሬ አንዷት ሌላ ወጣት ስለሆንኩኝ እና ልቤ በፍቅር ስለተሞላች በገዛ አባቴ እና በብዙ ወንዶች በመደፈሬ የተነሳ የደረሰብኝን ፍራቻ እና ጥላቻ ቀርፌ አይኑን በድጋሚ

አላየውም ያልኩትን የአባቴን መልክ ቁርጥ የሆነውን የአባቴን ልጅ ትልቁ ወንድሜንና ሌሎችንም በእህትነት ቀርቤያቸዋለሁ (ገጽ፤190)፡፡

በዚህና በሌሎች በኤጭ...! ልቦለድ ውስጥ ደራሲው በተጠቀማቸው ተጨባጭ ማስረጃ ያለማቅረብ እና የገለልተኝነት ባህሪ የመጽሃፉን በምትሃታዊ እውነታዊነት ስልት ስለመቅረቡ ማሳያ ሆነው የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## 4.1.4. ጥንዳዊ ተቃርኖ /Binery opposition/

በቀረበው መጽሃፍ ውስጥ ጥንዳዊ ተቃርኖ በተለያዩ ስልቶች ይገለጻል፡፡ የፍቅር አብርሃም አጎት ሶቅራጥስ የምትሃታዊ እውነታዊነት ጥቁር አስማት መገለጥ የሆነው ሰይጣን መሸነፉ ባይቀርም የሰው ልጆችን ከፈጣሪ ማራቅ አላማው መሆኑን ይናገራል፡፡ በዚህ ሳቢያ ጸጋና ጸጋ አልባነት፤ ሞትና ሕይወት፤ በረከትና መርገም ምድራዊ ሕይወት በመሆን በጥንዳዊ ተቃርኖ አማካኝነት ይገለጣሉ፡፡

> "የሰው ዘር መነሻ አዳም በሚስቱ ሄዋን ቆስቋሽነት የተከለከለውን ፍሬ በላና ሞት እንዲመጣብን አስደረገ፤ ምስኪኑ እዮብን ሚስቱ ታላቁን ፈጣሪ እንዲሰድብ ቆሰቆሰችው፤ ስለ ታለቁ እየሱስ ክርስቶስ ሲሰብክ የነበረውን መጥምቁ ዮሃንስን ሄሮድያዳ የተባለች ሴት በወቅቱ ስልጣን ላይ የነበረውን ንጉሱ ቆስቁሳው አንገቱ በዘግናኝ ሁኔታ እንዲቆረጥ ምክንያት ሆነች፤ ደሊላ የተባለችው ሴት 'እኛ ለድካምሽ ገንዘብ እንሰጥሻለን አንቺ የጠላታችን ሳምሶን ሃይል ያለበትን የሰውነት አካል ንገሪን' ሲሏት ደሊላ የሳምሶምን የፍቅርኛዋን ሚስጢር አወቀችና የሳምሶንን ሃይል ያለበትን ጸጉር በመላጨቷ የሳምሶን ሃይል ተነጠቀ" (ገጽ፡36)፡፡

በቀረበው ትረካ ውስጥ ሕይወትና ሞት፤ እርኩሰትና ቅድስና፤ ፍቅርና ጥላቻ፤ ክፋትና የዋህነት በጥንዳዊ ተቃርኖ አማካኝነት የሃሳብ ጭብጥ መግለጫ ሆነው ቀርበዋል፡፡ ደራሲው የምትሃታዊ እውነታዊነት አሉታዊ ባህሪ ማሳያ ሆኖ በቀረበው ትረካ ውስጥ በጥንዳዊ ተቃርኖ አማካኝነት የአዎንታዊ እና አሉታዊ ጎኖች ሁለትዮሽ መጣረስን ለመመልከት አስችሎናል፡፡

> "ፍልስጤማውያን ሳምሶምን ያዙት፡፡ አይኑን በማውጣት የጨለማ እስር ቤት ውስጥ ጣሉት፤ ተሳለቁበትም፡ ምራቃቸውን ተፉበት፡ በዚያ ሰአት በልቡ ለታላቁ

ፈጣሪ ጸሎት አደረገ፤ አምላኬ ሆይ ሕይወቴ ከፍልስጤማውያን ጋር ትጥፋ በማለት ጸለየ፡፡ ከዚያም ሲያንገላቱት የነበሩትን ሰዎች 'እባካችሁ ወደ ምሶሶው አስጠጉኝ አላቸው፡፡' ያሰበውን አላወቁምና አስጠጉት፡፡ ሳምሶም ሃይሉን በመጠቀም ሁለቱን ግዙፍ የቤተ መቅደስ ምሶሶዎች አፈረሳቸው፡፡ በመቅደሱ የነበሩ ሶስት ሺ ሰዎች አለቁ፡፡ ሁሉ ነገር ለበጎ ነውና በዚህ ምክንያት እነዛ በአምላክ የማያምኑ ሁሉ አመኑ" (ገጽ፡36)፡፡

ሰይጣናዊ እሳቤና አምላካዊ እሳቤ በትረካው ውስጥ ጥንዳዊ ተቃርኖ ሆነው ይታያሉ፡፡ በትረካው ውስጥ ባለማመን ምክንያት ክፉ ተግባር ይከወናል፡፡ በማመን ምክንያት እንዲሁ ተአምር ሲፈጸም እንታዘባለን፡፡ በቀረበው ትረካ ውስጥ ማመንና አለማመን ጥንዳዊ ተቃርኖ ሆነው ታይተዋል፡፡ በዚህ ሒደት አንዱ ሃሳብ ሌላኛው ሃሳብ ላይ ተጽዕኖ ሲያደርስ ያሳየናል፡፡

በኤጭ...! ልቦለድ ውስጥ አሉታዊ የሆነው ምትሃታዊ እውነታዊነት ጥንዳዊ ተቃርኖ በመሆን ሲገለጥ እንመለከታለን፡፡ Zomra እና Faris (1995፣6) አዕምሯዊና አካላዊ፣ ሕይወትና ሞት፣ መንፈሳዊና ቁሳዊ፣ ገሃዳዊ ዓለምና ምናባዊ ዓለም፣ ሴትና ወንድ እንዲሁም መሰል ጉዳዮች በምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፍ ትረካዎች እንደገና እንደ አዲስ የሚመሰረቱ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

> "አትፍሪ እኔ አንደበት እሆንሻለሁ፤ አንደበትሽን ከምታስቢው በላይ እከፍተዋለሁ፤ የፈለግሽውን ቋንቋ እንድትናገሪ አደርጋለሁ፡ የተለያዩ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ቋንቋዎችን እንድትናገሪ አንደበትሽን እከፍታለሁ፤ በድፍረትና በራስ መተማመን እሞላሻለሁ፤ የወንዶች ማጥመጃ ጥበብ እሰጥሻለሁ" (ገጽ፡104)፡፡

በቀረበው ማሳያ ውስጥ የምትሃታዊ እውነታዊነት አሉታዊ ጎን በሚስተዋልበት ኤጭ...! ልቦለድ ውስጥ ሊሊ ዝምተኛ ሆና ሳለች ተናጋሪ፤ አንድ ቋንቋ ብቻ የምትናገር ብትሆንም በአንድ ጊዜ ግን በርካታ ቋንቋ ስትናገር መታየቷ፤ አይን አፋር ሆና ሳለች ባንድ ጊዜ ደፋር ሆና መታየቷን ስንመለከት የጥንዳዊ ተቃርኖ ግንኙነት በጥቂር አስማት ባህሪ አማካኝነት መጣሱን እንመለከታለን፡፡

በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ በጥቁር አስማት ተጽዕኖ ስር የወደቀችው ሊሊ ሽመክት በአስማንዲዮስ መንፈስ እየተመራች ከትዳር ጥምረት ይልቅ ለትዳር መፍረስ ስትባዝን ይታያል፡፡ በዚሁ ተቃራኒ መንገድ እየተጓዘች ከአንድ ሺ ባለትዳሮች ጋር ዝሙት መፈጸሟን ከቀረበው ትረካ እንረዳለን፡፡

በሊሊ ሽመክት ሕይወት ውስጥ የጥንቁልና መንፈስ ሰርጾ ያስጨንቃታል፡፡ በሌላ በኩል ተልዕኮዋን በማሳካት የምትፈልገውን ገንዘብ አግኝታ መኖር ትፈልጋለች፡፡ በሷ ፍላጎት ውስጥ አሉታዊ የሆነው ጥቁር አስማት የሌሎችን ሰዎች ሕይወት ሰላም ነስቶ መታየቱ ያንዱ በሕይወት ለመኖር የሚደረግ ትንቅንቅ በሌላው ሞት ውስጥ ያደፈጠ መሆኑን በመጽሃፉ ውስጥ በቀረበው ጥንዳዊ ተቃርኖ አማካኝነት እንመለከታለን፡፡

> እነሆ አትሌት ጉዲናም የአስማንዲዮስን ባንዲራ ከእኔ ተቀበለ፡፡ በሩጫው ዓለም ሲያሸንፍ የኢትዮጵያን ባንዲራ ያውለበልባል፡፡ ከዚህ በኋላ ሕይወቱ የላሸቀ ይሆናል፡፡ እናም ይህ አትሌት ለእኔ አንድ ሺኛው ሆነ፡፡ የሽልማት መቀበያዬ ሎተሪ ሆነኝ፡፡ ታላቁን ሽልማት ለመቀበል ወደ ቤቴ ሄድኩኝ፡፡ ከምሽቱ 6፡45 ደቂቃ ላይ አስማንዲዮስ መጣ፡፡ "የእኔ ትዕዛዝ ተቀባይ በስራሽ ኮርቼብሻለሁ፡፡ ታላቁ ሽልማት በዕጥፍ ያድግልሻል፤ ከዚያ በፊት ግን አሁንም አንድ ቀላል ስራ ይሰጥሻል፤ አይ ሽልማቴን አሁን እፈልጋለሁ ካልሽ እሰጥሽና በድጋሚ አንቺ ጋ አልመጣም፤ ግን ላንቺ ምርጥ የሚሆነውን እኔ ስለማውቅ የእኔን ፍላጎትና ምርጫ ብትጠቀሚበት የተሻለ ነው ላንቺም የሚሻለው እሱ ነውና! (ገጽ፣136)፡፡

በሊሊ ሕይወት ውስጥ ሕይወትና ሞት አድፍጧል፡፡ በሕይወት ለመኖር በእርኩስ መንፈስ እየተመራች የሌሎችን ሕይወት በመመርኮዝ የተስተካከለ ሕይወት ለመኖር የታዘዘችውን ሁሉ ስትፈጽም መታየቱ የጭብጡ ትኩረት በምትሃታዊ እውነታዊነት ስልት መቅረቡን እንድንረዳ ያደርገናል፡፡

### 4.1.5. ምስጢራዊነት

ምስጢራዊነት የምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፍ አሉታዊ ጎን ማሳያ ባህሪ ሆኖ ይጠቀሳል፡፡ በተለይም በምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፍ ውስጥ ምስጢራዊነት ዋነኛ ባህሪ ነው፡፡ Carpenter (1949) ምስጢራዊነትን አስመልክቶ "to…to seize the mystery that breaths behind things." ሲሉ ገልጸውታል፡፡

በኤጭ…! ልቦለድ አሉታዊ የሆነው የምትሃታዊ እውነታዊነት አቀራረብ በተለይም በጥቁር አስማት አማካኝነት የሚፈጸመውን የጥንቁልና ድርጊት ለመደበቅ ሲባል በምስጢር ተይዘው የሚከናወኑ ጉዳዮች ከፍ ያለ ቦታ እንዲይዙ ሲያደርጋቸው የምንመለከተውም ለዚሁ ነው፡፡

> እሁድ እሁድ ጠዋት እናቴ ቤተክርስቲያን ቀርታ አታውቅም፡፡ አንዳንዴ እኔንም ይዛኝ ትሄዳለች፡፡ በእርግጥ በጥያቄ ስለምወተውታት ይዛኝ ከመሄድ ጥላኝ መሄዱን ትመርጣለች፡፡ አንድ ጊዜ ቤተክርስቲያን ስንሄድ አንድ ወጣት ቄስ ወደ እናቴ መጣና ትንሽ ካወሩ በኋላ እናቴን በትኩረት እያያት ከእየሩሳሌም ድረስ ተባርኮ የመጣ ነው 235 ብር በማለት አንገት ላይ የሚታሰር መስቀል ያለው ማተብ ሰጣት ገዛችው፡፡ ወዲያው እሰሪው አለችኝ፡፡ በእሺታ ተቀብዬ አሰርኩት፡፡ ከዚያ ወደ ቤት ጸሎት ጨርሰን ስንመለስ "እናቴ ስለገዛሽልኝ አመሰግናለሁ ግን ለምንድነው? ማተብ አንገት ላይ የሚታሰረው?" አልኳት፡፡ "መታሰር ስላለበት ነዋ!" "ለምን?" "እንግዲህ አትጨቅጭቂኝ!" አለችኝ (ገጽ፡9)፡፡

ኤጭ…! ልቦለድ የምትሃታዊ እውነታዊነት ባህሪ በሆነው ምስጢራዊነት አማካኝነት ከላይ በቀረበው አስረጇ መሰረት ሚስጢራዊ ድርጊት እየተፈጸመ መሆኑን ይጠቁመናል፡፡ ምስጢራዊነት አሉታዊ ለሆነው የምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፍ መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑንም በዚህ አጋጣሚ እንድንረዳ ያደርገናል፡፡

በኤጭ…! ልቦለድ ሚስጢራዊነት የሃሳብ መሸጋገሪያ ዋነኛ ጉዳይ በመሆን ይታያል፡፡ የጥቁር አስማት ክፍል የሆነው ጥንቁልና በእሌኒ አባትና በመሪጌታው አማካኝነት በምስጢር እየተካሄደ መሆኑን እሌኒ ግራ በተጋባ ሁኔታ ትጠቁማለች፡፡ በመሪጌታው እና በእሌኒ አባት ፍቅር አብርሃም መካከል በምስጢር የተያዘ ጉዳይ በመኖሩ መሪጌታው በማይታወቅ ቋንቋ ከጸለየ በኋላ የወር አበባዋን ከሶስት ቀን በኋላ ይዘህ ና በማለት ትዕዛዝ ሲሰጠው እንመለከታለን፡፡ የታቀደው ጉዳዩ ምስጢራዊ ክዋኔን መሰረት አድርጎ የሚከናወን በመሆኑ ትረካው በምስጢራዊነት አማካኝነት በምትሃታዊ እውነታዊነት ስልት መቅረቡን ማሳያ በማድረግ አቅርቦታል፡፡

"አባቴ የምን የወር አበባ ነው?" አልኩት፡፡ "የመጀወሪያ የወር አበባሽን ማየት የምትጀምሪው ከሶስት ቀናት በኋላ ነው፡፡ አየሽ ወደፊት የተቃና ሕይወት እንዲኖርሽ የመጀመሪያው የወር አበባሽ ላይ ጸሎት መደረግ አለበት፣ ስለዚህ እኔ ደሙን ለመሪጌታ እውስድለትና ጸሎት ያደርግልሻል፡፡ ይህን የምናደርገው በዚህ ድንቅ ውበትሽ የተነሳ እጅግ በርካታ ፈተና እንዳይገጥምሽ ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ለማንም እናዳትናገሪ! በተለይ ለአጎትሽ እንዳትነግሪው! ብትነግሪው ዋ! የገባሁልሽን ቃል አፈርሰዋለሁ!" (ገጽ፣22)፡፡

አስማንዲዮስ በትዳር ማናጋት ላይ የተሾመ የጥልቁ መንፈስ አባል መሆኑንና ምስጢራዊ ተልዕኮውን ለመፈጸም ደግሞ በሊሊ ሽመክት አማካኝነት መዘጋጀቱን እንመለከታለን፡፡ ለምን? ለሚለው ጥያቄ ደግሞ በአባትሽ አማካኝነት ባንቺ ውስጥ በዝሙት አማካኝነት ገብቻለሁ በማለት ይህንኑ ምስጢራዊ ስውር ቁርኝት መጣስ እንደማትችል የሚያስጠነቅቃት መሆኑን ከማስረዳት ባለፈ በዚሁ አስረጂ ኤጭ…! ልቦለድ በምትሃታዊ እውነታዊነት ጭብጥ መጻፉን በተለያዩ አስረጂዎች ያረጋግጥልናል፡፡

ይህንኑ ምስጢራዊ ክዋኔ ተራኪው (ገጽ፣118) ላይ በጉልህ አቅርቦልናል፡፡ "የአባታችን መንፈስ አስማንዲዮስ ሃዋሳ ሲለኝ ሃዋሳ፣ ባህር ዳር ሲለኝ ባህርዳር፣ ሞያሌ ሲለኝ ሞያሌ፣ ቤተክርስቲያን ሲለኝ ቤተክርስቲያን፣ መስጂድ ሲለኝ መስጂድ፣ ጭፈራ ቤት ሲለኝ ጭፈራ ቤት…እያልኩ እንደመራኝ እሄዳለሁ፡፡ ሂጄም የዝሙት ባንዲራ አውለብልቤ እመለሳለሁ፡፡

ሚስጢራዊ በሆነ መንገድ በሚከናወነው ጥቁር አስማት አንድ ሺ ባለትዳሮችን በወሲብ አማካኝነት ከመበከል አልፋ ሊሊ ሽመክት 300 የሃይስኩል ሴት ተማሪዎች ላይ የሌዚቢያኒዝም መንፈስ እንድታጋባባቸው ሁለተኛ ትዕዛዙን በተለመደው ምስጢራዊ መንገድ እንድትፈጽም መደረጉን እንመለከታለን፡፡

የእኔ ትዕዛዝ ተቀባይ ኮርቼብሻለሁ! ታላቁ ሽልማት በእጥፍ ያድግልሻል ይህ ከመሆኑ በፊት ግን አሁንም አንድ ቀላል ስራ ይሰጥሻል፡፡ አይ! የመጀመሪያ ሽልማቴን ብቻ አሁን እፈልጋለሁ ካልሽም እሰጥሽና በድጋሚ አንቺ ጋ አልመጣም፣ ግን ላንቺ ምርጥ የሚሆነውን እኔ ስለማውቅ የእኔን ፍላጎትና

> ምርጫ ብትጠቀሚበት የተሻለ ነው ላንቺም የሚሻለው ያ ነውና! ያልከው ይሁን አባታችን! በጣም ጥሩ ልጅ! ሁለተኛው ስራሽ ሶስት መቶ የሃይስኩል ተማሪዎችን በሌዚቢያኒዝም መንፈስ መሙላት ነው፡፡ ስትጨርሺ ስሜን በክብር ጥሪ እመጣለሁ! አትፍሪ ካንቺ ጋር ነኝ! ሃይልና ግርማ ሞገስ እሰጥሻለሁ (ገጽ፣136-137)፡፡

በምትሃታዊ እውነታዊነት አሉታዊ ጎን የቀረበው ኤጭ…! ልቦለድ አሉታዊ ችግሮቹ ካንዱ ድርጊት ወደ ሌላኛው ድርጊት በምስጢራዊ መንገድ እየተሸጋገሩ የሚዘልቁ ናቸው፡፡

በመጽሃፉ ውስጥ ሁለተኛው የጥቁር አስማት ድርጊት ተጠናቆ በምስጢር ሶስተኛው የጥቁር አስማት ድርጊት አማካኝነት መጽሃፉ በምትሃታዊ እውነታዊነት አሉታዊ ጎን መቅረቡን ያረጋግጥልናል፡፡ ተራኪው ይህንኑ ሃሳብ (ገጽ፣140) አቅርቦልናል፡፡

> "በሶስተኛው ዙር ወላይታ ሶዶ እልክሻለሁ፡፡ በምሰጥሽ ስልክ ትደውይና ለምታገኚው ሰው 50 ህጻናትን እየጠለፍሽ መስጠት ብቻ ነው፡፡ ይህ የመጨረሻ ስራሽ ነው፡፡ "አይ ሽልማቱ አሁን ይሰጠኝ የሁለቱ ሽልማት ብቻ ይበቃኛል ካልሽም ሽልማትሽን አሁኑኑ በመስጠት ካንቺ ጋር መለያየት እንችላለን ውሳኔው ያንቺ ነው፡፡" "ወላይታ እሄዳለሁ አባታችን፡፡" "ጎበዝና አስተዋይ! የምታገኚው ሰው ጄቴ ይባላል፡፡ ተጨማሪ ሃይል ይኖርሽ ዘንድ ከጸጉርሽ መካከል ስድስት ፀጉር ነቅለሽ ስድስት ጊዜያት ስሜን ከጠራሽ በኋላ በዶሮ ኩስ፣ በስኳር እና ግራዋ ለውሰሽ አቃጥይው ይህን ነገር እንደተለመደው ለማንም መናገር የለብሽም!" በማለት አባታችን ተሰወረ፡፡

በኤጭ…! ልቦለድ መጽሃፍ ውስጥ ምስጢራዊነት የመጽሃፉ አሉታዊ ጭብጥ ዋነኛ ጉዳይ ሲሆን እንመለከታለን፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው የሚከናወኑት ድርጊቶች በሙሉ በምስጢር የተያዙና በምስጢራዊ መንገድ የሚከናወኑ መሆኑን ተከትሎ ነው፡፡ አሉታዊ የሆነው የጥቁር አስማት ክዋኔ በምስጢራዊ መንገድ ተጀምሮ በምስጢራዊ መንገድ ካንደኛው ድርጊት ወደ ሌላኛው ድርጊት እየተሸጋገረ ሚስጢራዊነት የኤጭ…! ልቦለድ ዋነኛ ጉዳይ መሆኑን አሳይቶናል፡፡

## 4.1.6. የፖለቲካ ትችት /poltical critique/

የአስማት ተጨባጭነት ያለው አማራጭ ዓለም በእውነታው ላይ የተመሰረቱ አመለካከቶችን እንደ እውነታዊነት፣ ተፈጥሯዊነትና ዘመናዊነት ያሉትን ለማስተካከል ይሰራል፡፡ በኤጭ...! ልቦለድ ውስጥ የእሌኒ ፍቅር የእናቷ ወንድም የሆነው አጎቷ ሶቅራጥስ መጽሃፍ አንባቢ በመሆኑ እሌኒን በተረት ተረትና መሰል ዘዴዎች ወደ ንባብ ልምድ እንድትሳብ ሲገፋፋት ይታያል፡፡ በዚሁ በተረት ተረት አማካኝነት ፖለቲካዊ ትችት ላይ ሲያተኩር እንመለከታለን፡፡

አሉታዊ በሆነው የጥቁር አስማት ጭብጥ የተጻፈው ኤጭ...! ልቦለድ በመጽሃፉ ትረካ ውስጥ የሚስተዋሉ አሉታዊ ችግሮች ምላሻቸው አዎንታዊ እንዲሆን በፖለቲካ ትችት አማካኝነት ሃሳብ ይሰነዝራል፡፡ የእሌኒ ቤተሰቦች የሚያደርጉትን የጥንቁልናና ለዕርኩስ መንፈስ የማደር አምልኮ በመኮነን የእሌኒ አጎት ሶቅራጥስ እሌኒን መልካም ስብዕና የተላበሰችና ለሀገሯ ጠቃሚና ብቁ ዜጋ እንድትሆን በተረት እየመከረ ሊያንጻት ጥረት ያደርጋል፡፡ ደራሲው እግረ መንገዱን በተረት አስታኮ የፖለቲካ ትችቱ ይሰነዝራል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ (ገጽ፣11) ላይ ሶቅራጥስ ለእሌኒ ተረት ይነግራታል፡፡ የተረቱ ጭብጥ አራት የተለያየ ደረጃ ያላቸውን ሰዎች የሚመለከት ነው፡፡ እነዚህ አራት ሰዎች ዶክተር፣ ፖለቲከኛ፣ ሽማግሌና ህጻን ልጅ ሆነው ቀርበዋል፡፡ አራቱ ሰዎች በትንሽ አይሮፕላን ተሳፍረው ሲሄዱ በድንገት አይሮፕላኑ የመበላሸት አደጋ ይደርስበታል፡፡ አይሮፕላኑ ውስጥ ያለው መዝለያ ፓራሹት ደግሞ ሶስት ብቻ ነበር፡፡ ስለሆነም አንድ ሰው መሞቱ አይቀሬ ሆነ፡፡ ከነዚህ አራት ሰዎች አንዱ ዶክተር ነው፡፡ የአይሮፕላኑን በድንገት መበላሸት እንዳወቁ ዶክተሩ "እኔ የማክማቸው ብዙ በሽተኞች ስላሉ መሞት የለብኝም" በሚል አንዱን ፓራሹት ወስዶ ወደ ምድር ዘለለ፤ ሁለተኛው ሰው ፖለቲከኛ ነበር እሱም "እኔም አስራ ሰባት አመት ሙሉ ተዋግቼ መሞት የለብኝም በዚያ ላይ ባለስልጣን ነኝ ዘጠኝ ያሰጀመርኳቸው ፎቆችም ስላሉ መሞት የለብኝም" በሚል ሁለተኛውን ፖራሹት ወስዶ ዘለለ፡፡ ሁለቱ ሰዎች ወደ ምድር ዘለው ሽማግሌውና ትንሹ ልጅ ብቻ ይቀራሉ፡፡ በዚሁ ጊዜ ሽማግሌው "የኔ ልጅ እኔ ስላረጀሁና መሞቻዬ ስለደረሰ መትረፍ አልፈልግም አንተ ግን ልጅ ነህ ብዙ ይጠብቅሃል ስለዚህ የቀረውን ፖራሹት ይዘህ ውረድ ይሉታል፡፡" ልጁ ሽማግሌውን "አባባ ሁለታችንም አንሞትም እንተርፋለን" አላቸው፡፡ ሽማግሌውም በመገረም

"እንዴት ይሆናል ልጄ!" ቢሉት ልጁም መልሶ "ፖለቲከኛው የዘለለው ፖራሹት መስሎት የኔን የትምህርት ቤት ሻንጣ ይዞ ነው" ማለቱን በመጽሃፉ ትረካ ውስጥ ተጠቅሷል፡፡

በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ ግለኝነትና ለኔ ብቻ ማለት በማህበራዊ መስተጋብራችን ውስጥ በፖለቲካ ሹመኞች አማካኝነት የሚካሄድ መሆኑን በፖለቲካ ትችት አማካኝነት ያሳየናል፡፡

ኤጭ…! ልቦለድ በተጨማሪ ባልተገባ የጥንቁልና አምልኮ ሳቢያ ለቤተሰብ መፍረስ ምክንያት እንደሆኑት እንደ እሌኒ ቤተሰቦች መጨረሻው መጥፋት መሆኑን በሀኪሙ እኔ ልቅደም ማለት በፖለቲከኛው ከሕዝብና ከሀገር ጥቅም በላይ የግል ጥቅምን ማስቀደም ፖለቲካን ተገን አድርገው የሚፈጸሙ መሆናቸውን በፖለቲካ ትችት አማካኝነት ያሳየናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለእውነት የቆሙ መልካም አሳቢዎች መጨረሻ ላይ አሸናፊ እንደሚሆኑ ይጠቁማል፡፡ ሶቅራጥስ እሌኒን ይህንን የሞራል አስተምህሮት በማስተማር መልካም ስብዕና የተላበሰች ዜጋ እንድትሆንና ከአሉታዊ ይልቅ አዎንታዊ ድርሻ እንዲኖራት በፖለቲካ ትችት አማካኝነት ስብዕናዋን ሲገነባ እንመለከታለን፡፡

በተጨማሪም በቀረበው የፖለቲካ ትችት ውስጥ ለኔ ብቻ ማለት፣ ስግብግብነት፣ ሙስናና የፖለቲካ የበላይነት ሀገር ላይ የተጋረጡ አሉታዊ ችግሮች መሆናቸውንም ይጠቁመናል፡፡

> ምንግዜም በውስጥህ መቻልህን መናገር አለብህ! ለውስጥህ አለመቻልህን የምትነግረው ከሆነ ውስጥህ መልሶ አለመቻልህን ይነግርሃል፡፡ ይህ ትልቁ ወርቃማ ሕግ ነው፡፡ ለውስጥህ ምንግዜም አሸናፊነትህን የምትሰብከው ከሆነ ታሸንፋለህ (ገጽ፣12)፡፡

ሰርቶ በመለወጥ ሳይሆን ሳይሰሩ ተስፋ ቆርጦ በመቀመጥ የምናማርር በርካቶች ነን፡፡ ይህ የፖለቲካ ትችትን የተንተራሰ ማህበረሰባዊ ጉዳይ ነው፡፡ በአንችልም ምክንያት ሀገር ከአዎንታዊ እድገት ይልቅ አሉታዊ ውድቀት የተጋረጠባት መሆኑን ማሳያ አድርጎ አቅርቦልናል፡፡

በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ የአዲስ አበባ ዘርፈ ብዙ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች በፖለቲካ ትችት አማካኝት (ገጽ፣48) ተንጸባርቋል፡፡

"አዲስ አበባ ምትሃት የሆነች ከተማ! አዲስ አበባ ዘወትር በግርግር፣ በጫጫታ፣ በሁካታ፣ በራስ ወዳድነት፣ በግለኝነት፣ በወከባ፣ በእርካታ አልባነት የተሞላች ከተማ! አዲስ አበባ ጥቂት ሊደረስባቸው የማይችሉ ጥቂት እብድ ያሉ ሃብታሞች መኖሪያ ከተማ! አዲስ አበባ የሚላስ የሚቀመስ ነገር ያጡ በሚሊየን የሚቆጠሩ ምንዱባኖች ከተማ! አዲስ አበባ የበርካታ ጉላንጆች ፌጠኞችና እፉኝቶች መኖሪያ ከተማ! አዲስ አበባ የእባብነትና የበግነት ከተማ! አዲስ አበባ የህልምና የህልም አልባነት ቅይጥ ግርንቢጥ ከተማ!..."

አሉታዊ ጭብጥ ይዞ በቀረበው ኤጭ...! ልቦለድ ውስጥ የፖለቲካ ትችት አንዱ የአሉታዊ ጎን ጥቁምታ ማሳያ በመሆን ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ስለ አዲስ አበባ ከተማ ማህበራዊ መስተጋብር አስመልክቶ አሉታዊ በሆነ ችግር ውስጥ ተተብትባ የምትገኝ መሆኑን በምትሃታዊ እውነታዊነት ስነፅሁፍ ውስጥ አንዱ ባህሪ በሆነው በፖለቲካ ትችት አማካኝነት እንድንመለከት አድርጎናል፡፡

ደራሲው አሉታዊ የሆነው የጥቁር አስማት ጥንቁልና የሚፈጸምበት ዋነኛ ስፍራ አዲስ አበባ ከተማ መሆኗን ሊሊ ሽመክት ስትከውን በነበረው የእርኩስ መንፈስ ዓላማን የማስፋፋት ተልዕኮ አሳይቶናል፡፡ እነሆ ስለ አዲስ አበባ ከተማ አሉታዊ ችግር ደግሞ ሌላኛዋ ገጸባህሪ እሌኒ ፍቅር በፖለቲካ ትችት አማካኝነት ሒስ ስትሰነዝር ይታያል፡፡

እነዚህን አስረጂዎች ስንመለከት ኤጭ...! ልቦለድ አሉታዊ በሆነው ጥቁር አስማት ዘርፍ ተዘጋጅቶ መቅረቡን መገንዘብ እንችላለን፡፡

በኦጭ...! ልቦለድ ውስጥ ሌላው የፖለቲካ ትችት ማሳያ ሆኖ የቀረበው ሁለተኛዋ ገጸባህሪ ሊሊ ሽመክት የአስማንዲዮስ ትዳርን በዝሙት የማፈረስ ተልዕኮ ስትፈጽም ካገኘችው የፊልም ደራሲና አዘጋጅ ጋር ስለ ኢትዮጵያ የፊልም አዘገጃጀት ፊር የሳተ አካሄድ ትተቻለች፡፡

(ገጽ፣116) ላይ የፊልም አዘጋጁ የሊሊ ሽመክትን ሴትነት ስለፈለገ ብቻ ፊልም ላሰራሽ በሚል አንሶላ ሊጋፈፋት ጥረት ያደርጋል፡፡ ሊሊ ባንጻሩ በፊልም ሙያ ተመርቀው የሚንከራተቱ በበዙበት ሀገር እንዴት ምንም የማታውቅን ሴት ጭኗን በመመኘት ብቻ ለፊልም ስራ ትጋብዛለህ? የኢትዮጵያ የፊልም ኢንዱስትሪ ችግር ከዚህ ችግር የሚላቀቀው መቼ ነው? በሚል ስትሞግተው ያሳየናል፡፡ እሱም በማፌር አብዛኛዎቹ

ይማራሉ እንጂ ምንም እውቀት የሌላቸው ናቸው፡፡ ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ደግሞ ተመልካቹ ሕዝብና መንግስት ነው ሲል ይመልሳል፡፡ ሊሊ በርካታ ሃሳብ አንስታ ካሳመነችው በኋላ ፊልም አልሰራም ግን ፍላጎትህን እቀበላለሁ ብላ በዝሙት ቀሪ የሕይወት ዘመኑን አርክሳ መሄዷን ተራኪው ያትታል፡፡

> "በሀሳብሽ እስማማለሁ የዚህ ሁሉ ችግር መንስኤ ግን ተመልካችና መንግስት ናቸው"
>
> "ማለት?"
>
> "የሀገራችን ፊልም ተመልካች ራሱ ቅል ራስ ነው፡፡ ማየት የሚፈልገውና አዳራሹ ግጥም ብሎ የሚሞላው ሊያስቁ የሚችሉ ፊልሞችን፣ በስድብ የተሞሉ ፊልሞችንና በቧልት የተሞሉ ፊልሞችን ብቻ ነው፡፡ በሌላ በኩል መንግስት ሳንሱር ያደርጋል የፈለግሽውን ፊልም መስራት አትችይም" (ገጽ፣117)፡፡

ተገቢውን ሙያ ከተገቢው ባለሙያ ጋር የማገናኘት ሀገራዊ ችግር ትላንትም ዛሬም በአደባባይ የሚታይ የፖለቲካ ችግር መሆኑን መታዘብ ይቻላል፡፡ ይህ አሉታዊ የሆነ ችግር በፊልም ኢንዱስትሪው ላይ የከፋ ችግር መሆኑን ለማመልከት ተራኪው የፖለቲካ ትችትን መሳሪያ በማድረግ ተጠቅሞበታል፡፡

የመጽሃፉ ሃሳብ ጥቁር አስማት እያደረሰ ያለውን አሉታዊ ችግር ማስረዳት ቢሆንም እግረ መንገዱን ግን በፖለቲካ ትችት አማካኝነት በሀገር አቀፍ ደረጃ አሉታዊ የሆኑ ችግሮችን በማንሳት ያለውን አሳሳቢ ችግር ለማመልከት ተጠቅሞበታል፡፡

## 4.2. ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት /Theortical fram work/

### 4.2.1. ቀዳማይ ንድፈ ሃሳብ

ለቀዳማይ ጽንሰ ሃሳብ አራማጆች ምትሃታዊ እውነታዊነት የወርቃማው ዘመን አሳቢያን መገለጫ ነው፡፡ በላቲን አሜሪካ ሀገራትና በአርጀንቲናም እንዲሁ ጠቀሜታው የጎላ እንደሆነ ይናገራል (Elkins 1959)፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በእኛም ሀገር ኢትዮጵያውያን የምትሃትን ጥበብ በባህላዊ መንገድ ከእርኩስ መንፈስ መጠበቂያ በማድረግ ይጠቀሙበት ነበር፡፡

በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ የደብረ ማርቆስ ከተማ ሰብአዊ ማንነት ባልነጠፈባቸው የኢትዮጵያ የገጠር ከተሞች ላይ ያለውን አዎንታዊ እሴት የሚያመለክት ሆኖ ሲቀርብ አዲስ አበባ ደግሞ በዘመናዊነት ሳቢያ ኢትዮጵያዊ ባህል፣ ወግ እና እሴት እንዲሁም የተበከለ አየርና ለኔ ብቻ ማለት የሰፈነባት የአሉታዊ ጉዳይ ማሳያ ሆና ቀርባለች፡፡

> አዲስ አበባ ከተማ ሳትሆን ሀገር ናት፡፡ በጣም የተለጠጠች አስቀያሚና የምታምር ጉራማይሌ የሆነች ከተማ ናት፡፡ ማርቆስ ትንሽና ወጣ ገባ ናት፡፡ የደብረ ማርቆስ ድንጋይ ገር ነው፡፡ የአዲስ አበባ ድንጋይ ተንኮለኛ ነው፡፡ የደብረ ማርቆስ አየር ንጹህ ነው፡፡ የአዲስ አበባ አየር ይወብቃል፡፡ የደብረማርቆስ ሕዝብ ፈሪሃ እግዚአብሄር ያለው ነው፡፡ የአዲስ አበባ ህዝብ ፈሪሃ ምንም ነው፡፡ የአዲስ አበባ ሕዝብ በፈጣሪ ይመካል፡፡ የአዲስ አበባ ሕዝብ በገንዘብ ይመካል፡፡ የደብረ ማርቆስ ሕዝብ እምነት አለው፡፡ የአዲስ አበባ ሕዝብ ፍልስፍና አለው፡፡ የደብረ ማርቆስ ሕዝብ ልብን ያያል፡፡ የአዲስ አበባ ሕዝብ ኪስን ያያል (ገጽ፣48-49)፡፡

ለቀዳማይ ንድፈ ሃሳብ አራማጆች የምትሃት ጥበብ ለፈውስ፣ ከችግር ለመዳን፣ የፈጣሪን ተዓምር ለማሰብ እና ለአዎንታዊ ጉዳይ የምንጠቀምበት እንጂ ምትሃት የአሉታዊ ጉዳይ መከወኛ አይደለም የሚል እሳቤ አላቸው፡፡

## 4.2.2. ድሕረ ዘመናዊያን ምድፈ ሃሳብ

ከ1970ዎቹ ጀምሮ የተነሳው ድሕረ ዘመናዊነት ቀደምት ሕይወትንና ታላላቅ ትረካዎችን ያፈራረሰ ክስተት ነው፡፡ ድህረ ዘመናዊነት አፈታሪኮችን የማናምንበት፤ የጋራ እውነት የሚባል የሌለበት፤ ሰዎች ሁሉ ትክክል የሆኑበት፤ እውነት በገሃዱ ዓለም የሚገኝ ሳይሆን በቋንቋ፣ በፖለቲካና በዲስኩር የሚገለጽ ነው በሚል የሚያምኑ ናቸው፡፡

በኤጭ…! ልቦለድ በድሕረ ዘመናዊያን ጽንሰ ሃሳብ አራማጆች እንደሚታየው ከአብሮነት በላይ ግለኝነት፤ ከሰብአዊነት በላይ የሰብአዊነት መንጠፍ፤ ከጋራ እሴት በላይ ግለኝነትና የግለሰቦች ውሳኔ ብቻ ትክክል እንደሆነ ተቆጥሮ ማሕበረሰብን ለጉዳት የሚዳርግ ሲሆን የምናይበት ነው፡፡ በኤጭ…! ልቦለድ ትረካ ውስጥ ቀዳሚ ገጸባህሪ የሆነችው እሌኒ ፍቅር ይህንኑ ሃሳብ ስትኮንን ያሳየናል፡፡

> አባቴ እና እናቴ ገንዘብ አፍቃሪዎች ናቸው፡፡ ወሬያቸው ሁሉ ዘወትር ስለ ገንዘብ ነው፡፡ እንዴት ሀብታቸው ይበልጥ እንደሚጨምር ሰርክ ማውራት ልምዳቸው ነው፡፡ ለኔ በቂ ጊዜ አልሰጡኝም፡፡ ለእኔ በቂ ፍቅር አልሰጡኝም፡፡ በእርግጥ የጠየኩትን ከልክለውኝ አያውቅም፡፡ ፍቅር ግን አልሰጡኝም ፍቅርን የተቀበልኩት ከአጎቴ ነው፡፡ አጎቴ የእኔ ብርሃን ነው (ገጽ፣17)፡፡

በድህረ ዘመናዊነት ንድፈ ሃሳብ እንደሚታየው ሰዎች ከቤተሰብና ከማህበረሰብ የጋራ እሴት በመራቅ ለግል ፍላጎት ተገዝተው ለወለዷቸው ልጆች ሳይቀር ፍቅር ሲነፍጉ ይታያል፡፡ ይህ እውነታ በእሌኒ ሕይወት ላይ ሲከሰት ተራኪው ያሳየናል፡፡ እናትና አባቷ ገንዘብ የሚያገኙበትን መንገድ እንጂ ቤተሰባዊ ፍቅር ሲሰጧት አልታየም፡፡ ከዚህ ባለፈ በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ ከማህበረሰባዊ አብሮነት በላይ ግለሰባዊ ፍላጎት አይሎ መታየቱ ለአስከፊና ማህበረሰባዊ ቀውሶች መንስኤ ሲሆን መብቃቱን ያመለክተናል፡፡

የጋራ እሴት መጣስና በዘመናዊነት እሳቤ ለግል ሃሳብ ብቻ መገዛት የኋላ ኋላ የሚኖረው ተጽዕኖ አስከፊ መሆኑን ከእሌኒ ቤተሰብ ታሪክ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህም በድህረ ዘመናዊነት በኩል ያለው የግለሰብ ነጻነትና የፈለገውን የማድረግ መብት ተጽዕኖው የከፋ መሆኑን እንድንገነዘብ ያስችለናል፡፡

በኤጭ…!ልቦለድ ውስጥ የዘመናዊ ጽንሰ ሃሳብ እሳቤ የሚታይባቸው ሃሳባች በተደጋጋሚ ሲሰነዘሩ እንመለከታለን፡፡ የእሌኒ አጎት ሶቅራጥስን (ገጽ፣35) ላይ እሌኒ "ዝሙት ማለት ምን ማለት ነው?" ብላ ስትጠይቀው እሱም በምላሹ "ዝሙት ማለት መረን የለቀቀ የሴትና የወንድ ግንኙነት ሳይሆን በበርካታ ጉዳዮች ላይ ገደብ አልባ አጸያፊ ተግባር ማከናወን ነው ሲል ይመልስላታል፡፡" ድህረ ዘመናዊያን የጋራ እሴት የሚባል የለም በሚል መነሳታቸው በጋራ እሴት መንጠፍ ምክንያት የሚደርሰው ማህበረሰባዊ ቀውስና የሚደርሰው ሃገራዊ ችግር የሚያሳስባቸው አይመስልም፡፡ ለእኔ ብቻ በሚለው ስግብግብነትና ግላዊ ፍላጎት ምክንያት የዝሙት ትርጓሜ በርካታ ፍቺዎች እንዳለው እንድንረዳ ያደርገናል፡፡

> የእኔ ልጅ ዝሙት ማለት ከጋብቻ ውጪ ከሌላ ሴት ጋር ወሲብ መፈጸም ብቻ ማለት አይደለም፡፡ ፈጣሪን መርሳትም ዝሙት ነው፡፡ ፈጣሪ የለም ማለት እራሱ

ዝሙት ነው፡፡ ሰይጣንን ማምለክ ዝሙት ነው፡፡ በጣኦት ማምለክ ዝሙት ነው፡፡ በገንዘብ፣ በዝና፣ በስልጣን መመካት እና መታበይ ዝሙት ነው፡፡ አዕምሮን በታላቅ ፈንጣዝያ ውስጥ መዝፈቅ ዝሙት ነው፡፡ በዘርና በዘረኝነት መታጠር ዝሙት ነው (ገጽ፣35)፡፡

እንዲህ አይነት እሳቤዎች የሚስፋፉት ሰዎች በግላዊ ፍላጎት ተመርተው በሚያደርጉት እሽቅድምድም በመሆኑ የግለሰብ ነጻነት ብቻውን ድህረ ዘመናዊያን እንደሚሉት ለውጥ ያመጣል በሚል ማሰብ አዳጋች ይሆናል፡፡

ሁለተኛዋ ገጸ ባህሪ ሊሊ ሽመክት እንዲሁ አሉታዊ የሆነውን የዝሙት መንፈስ ስታስፋፋ ያገኘችው አንድ ሰው ከትዳሩ ውጪ ሚስቴ ግላዊ ነጻነት ስለሰጠችኝ ከማንኛዋም ሴት ጋር ዝሙት መፈጸም እችላለሁ ሲል እንመለከታለን፡፡ ይኸው አሉታዊ ሃሳብ በኤጭ…! ልቦለድ (ገጽ፣124) ቀርቦ እንመለከታለን፡፡

"ግን ድንገት አሁን ባለቤትህ ሰርፕራይዝ ላድርግህ ብላ ብትመጣስ?

ለዚያውም የግል አልጋችሁ ላይ ከሌላ ሴት ጋር?"

"ፈቅዳልኛለች"

"ፈቅዳልኛለች ማለት?"

"የፈለኩትን እንዳደርግ ከዚህ ቤት ውጪ ግን እንዳይሆን"

"እየቀለድክ ነው?"

"እሷም ጎዞ ላይ እያለች ተመሳሳይ ነገር ለማድረግ ፍቃድ አላት፡፡

አንድ ለአንድ በይው!"

እንዲህ አይነት ግለሰባዊ ነጻነት በዘመናዊነት መንፈስ የማህበረሰብን ወግ፣ ልማድና ባህላዊ እሴት ከመጣሱም በላይ ቤተሰባዊ አንድነትን የሚያናጋ በመሆኑ ጎልቶ የሚታየው ጸያፍነቱ እንጂ አዎንታዊ ተምሳሌትነቱ አይደለም፡፡ እዚህ ላይ ድሕረ ዘመናዊያን የግለሰብ ነጻነት ሊጠበቅ ይገባል ማለታቸው ነጻነት ሲባል እስከምን ድረስ ነው የሚለውን ጉዳይ በትኩረት እንድንመለከት የሚያደርገን ነው፡፡

## 4.3. ዘመናዊነትና ማህበራዊ ሒስ

ዘመናዊነት ሁለት ተቃርኖች አሉት፡፡ በአንድ በኩል ከሰው ልጅ ነጻነትና አብርሆት ጋር ከሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ጋር እንዲሁም ከኢኮኖሚያዊ ብልጽግና ጋር ይያያዛል፡፡ በሌላ ገጹ ግን ዘመናዊነት ውስጥ የዘር ጭፍጨፋና ኢ-ሰብአዊ የሆኑ ጭካኔዎች አሰቃቂ የዓለም ጦርነቶችና የሕይወት ትርጉም የለሽነት ተስፋፍቶ ይገኛል (Elkins 1959)፡፡

ማሕበራዊ ሒስ እ.ኤ.አ. በ1920ዎቹ እና በ1930ዎቹ ከጀርመን ፍራንክፈርት የፍልስፍና ትምህርት ቤት የተነሳ አዲስ የፍልስፍና ንቅናቄ ሲሆን ይህም ንቅናቄ በዘመናዊነት ውስጥ ያጋጠሙንን ማህበራዊ ችግሮች መንስኤያቸውን ነቅሶ የሚያወጣና ከችግሩ ውስጥ መውጫ መንገዱንም የሚጠቁም ፍልስፍና በመሆን ይጠቀሳል፡፡

በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ በዝሙት አማካኝነት የአንድ ሺ ባለትዳሮችን ኑሮና ሕይወት ለማናጋት የተነሳው የአስማዲዮስ ሰይጣናዊ መንፈስ በሊሊ ሽመክት አማካኝነት የሚፈልጋቸውን ሰዎች እያጠመደ ተልዕኮውን ከዳር ለማድረስ ሲጣደፍ ይታያል፡፡ በዚሁ ሒደት ውስጥ ለምን ከማለት ይልቅ በምንቸገረኝነት አሉታዊ ተጽዕኖ ያለው ዝሙት እንደ ዘመናዊነት ተቆጥሮ በበርካቶች ዘንድ ያለችግር ሲከወን መታየቱ ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ ቀውስ እየተከሰተ መምጣቱን እንድንገነዘብ ያደርገናል፡፡

ሊሊ ሽመክት ካጋጠሚት አንድ ሺ ባለትዳሮች ውስጥ ከአንድ ባለትዳር ውጪ ሁሉም እንደ መስዋዕት በግ እየተሳቡ የዝሙት ጭዳ ሲሆኑ እንጂ ለምን በማለት ቆም ብለው ሲያስተውሉና አይሆንም በሚል እራሳቸውን ሲያቅቡ አይስተዋልም፡፡

ሊሊን ያጋጠማት እምቢተኛና ብቸኛ ግለሰብ በዘመናዊነት ስሜት በመነዳት ለዝሙት ሲንበረከክ አይታይም፡፡ ምክንያቱም ያለፈባቸው መንገዶች ይህን አሉታዊ ጉዳይ አስተምረውት ያለፉ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ ካለፈ ሕይወቱ የተማረው ይህ ወጣት በዘመናዊነት መንፈስ እየተመራ ለዕርኩስ መንፈስ ሃይል ከመጋለጥ ይልቅ ካለፈ ሕይወቱ በመማር ለራሱ ሕይወት የራሱን የጥንቃቄ መርህ ሲተገብር ታይቷል፡፡

የማህበራዊ ሒስ ዋነኛ ዓላማ በዘመናዊነት ስሌትም ሆነ በሌላ ጉዳይ ሰዎች ችግር ውስጥ ገብተው መልሰው ከገቡበት ችግር የሚወጡበትን መንገድ ማመልከትና ማሳየት ነው፡፡ ቀጣዩ ሃሳብም ይህንኑ ጉዳይ እንድንረዳ ያደርገናል፡፡

> አመሰግናለሁ አየሽ ባለፈው ሕይወቴ እንደ መግደላዊት ማርያም በሰባት አጋንቶች የተያዝኩ ሰው ነበርኩ፡፡ ዝሙተኛ፣ ውሸታም፣ የስንፍና መንፈስ፣ ሌብነት፣ እምነት የለሽነት፣ ተስፋቢስነትና ዘረኝነት አራማጅ ወጣት ነበርኩ፡፡ አልማርም በማለት በአስራ አራት አመቴ ከቤት ጠፋሁ፡፡ ቤተሰቦቼ ፈልገው ወደ ቤት መለሱኝ፡፡ በድጋሚ ግን በአስራ ሰባት አመቴ ጠፋሁ፡፡ ሕይወቴን ለመቀየር ጠንቋይ ቤት ወሰዱኝ፡፡ ሰይጣን ግን ከአንዱ ሐጢያት ወደ ሌላ ሐጢያት ያሸጋግራል እንጂ አንዳችም ጥቅም የለውም፡፡ ሰይጣን ለትንሽ ቀናት ማር ያበላሻል፤ ከዚያ ግን ለዘመናት ድንጋይ ያበላሻል (ገጽ፣127)፡፡

ኤጭ…! ልቦለድ በአሉታዊ የአስማት ዘርፍ የተጻፈ በመሆኑ ከላይ በቀረበው ሐተታ ውስጥ ይህንኑ ጉዳይ የሚያጠናክሩ ሃሳቦች እንመለከታለን፡፡ የመጽሃፉ ትኩርት አሉታዊ የሆነውን የአስማት ጭብጥ በመጠቀም በተለይም በጥንቁልና ምክንያት የደረሱ ማህበረሰባዊ ችግሮችን ያሳየናል፡፡ የተዘረዘሩት ሀሳቦች አብዛኛዎቹ አሉታዊ የሆነውን የምትሃታዊ እውነታዊነት ስልትን የሚያመለክቱ ተጨማሪ አስረጂዎች በመሆናቸው ኤጭ…! ልቦለድ አሉታዊ በሆነው ጥቁር አስማት ጭብጥ የቀረበ መሆኑን ለመረዳት ያስችሉናል፡፡

ከሊሊ ጋር እሰጥ አገባ የገባው ሰው እንደገና (ገጽ፣129) ሊሊ ከገባችበት የችግር ማጥ ውስጥ እንድትወጣ በድጋሚ ሲሞግታት ይታያል፡፡

> የእኔ እህት ውስጥሽ ያለውን አንዳች እርኩስ መንፈስ ተረድቼዋለሁ፡፡ ወንዶችን በዝሙት መንፈስ ለመጣል ወጥመድ እየዘረጋሽ እንደሆነ ውስጤ ያለው የሰላም አለቃ መንፈስ ይነግረኛል፡፡ እኔ ከሃጥያት መንደር እርቄያለሁ፡፡ ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ የሚመለስ ሕይወት የለኝም፡፤ በክርስቶስ አሁን አዲስ ማንነት ተቀብያለሁ፡፡ ላንቺም የምነግርሽ አሁን ያለሽበት መንገድ ጨርሶ ስለማያዋጣሽ የሰላም አለቃሽን እንድትፈልጊ ነው፡፡

አሉታዊ የምትሃታዊ እውነታዊነት ባህሪ አጻጻፍ ስልት ማሳያ ሆኖ የቀረበው ኤጭ…! ልቦለድ በዘመናዊነት መንገድ የሚደርሱ ማህበራዊ ችግሮች በርካታ መሆናቸውን ያሳየናል፡፡ ማህበረሰቡ አዳዲስ ነገሮችን ከዘመናዊነት ጋር በማስተሳሰር በተመሳሳይ መንገድ በመጓዝ ተመሳሳይ ድርጊት መፈጸም እንጂ እንዲህ የማደርገው ለምንድነው?

በሚል ቆም ብሎ ማሰብ አልተለመደም፡፡ ኤጭ...! ልቦለድ ለሉታዊ የምትሃታዊ እውነታዊነት ችግሮች እርኩስ መንፈሳዊ በሆነ ተልዕኮ በዝሙት፣ በማሳጅ ቤቶች፣ በንቅሳትና በሴቶች ጸጉር ቤት አማካኝነት እየተስፋፋ መሆኑን ማመልከቱ መጽሃፉ በምትሃታዊ እውነታዊነት አሉታዊ መንገድ መቅረቡን አስረጂ ነው፡፡ ቀጣዩ ሃሳብም ይህንኑ ሃሳብ ያጠናክራል፡፡

> ለማንኛውም በንቅሳት የተነሳ ኤች.አይ.ቪ. በሽታ ሊተላለፍብህ ይችላል፡፡ የጉበት አልያም የወፍ በሽታ ሊይዝህ ይችላል፡፡ የተነቀስክበት ቦታ ላይ ቆዳህን የጸሃይ ብርሃን ሊነካውና አለርጂክ ሊይዝህ ይችላል፡፡ ንቅሳት አስከፊ ጠባሳ ያመጣል፡፡ የቆዳ ኢንፌክሽንም ያመጣል፡፡ ለቲታነስ በሽታ ያጋልጣል (ገጽ፡134)፡፡

**Elikans (2005) እንደሚለው ዘመናዊነትን የምንረዳባቸው አራት ዋና ዋና መንገዶች አሉ፡፡**

### 4.3.1. ዘመናዊነት /Modernity/

የሰውን ልጅ ነጻነት የሚመለከት ሲሆን ይህም አመለካከት "የሰው ልጅ እራሱን ከውጫዊ ሃይሎች ባህል፣ ተፈጥሮና ሐይማኖት ነጻ ባደረገ ቁጥር የተሻለ ሕይወት ይኖረዋል፡፡" በተጨማሪም "ዕውቀት የመቻቻልና የማህበራዊ ፍትህ መሰረት የግለሰብ ነጻነት ነው"፡፡

በኤጭ...! ልቦለድ ውስጥ የእሌኒ አጎት ሶቅራጥስ በማህበረሰብ ሕግጋት ሳይሆን በግለሰብ ነጻነት የሚያምን ነው፡፡ በዚህ ምክንያት (ገጽ፣10) ላይ "እኔ ሰዎች በሚያወጡት የሕግ ኮተት መታሰር አልፈልግም" ሲል ይታያል፡፡

አፈንጋጭነትና ለግለሰብ ነጻነት መከበር ብቻ መቆም ከአዎንታዊ ተግባር ይልቅ ለአሉታዊ እሳቤ ያጋልጣል፡፡ ግለሰብ ለማህበረሰብ የጋራ ህግጋት የማይገዛ ከሆነ በኤጭ...! ልቦለድ ላይ እንደሚታየው የሰው ልጆች በግለኝነትና ለኔ ብቻ በሚል እሳቤ በመመራት በወለዷቸው ልጆች ላይ ሳይቀር አውሬ ሆነው የመታየታቸው ነገር ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ሊተኮርባቸው ከሚገቡ ጉዳዮች ውስጥ በዘመናዊነት እሳቤ የሚመራ ከባህል ከሃይማኖትና ከማንነት ያፈነገጠ ግለሰባዊ ነጻነት ሳይሆን ከዚህ በተቃራኒው ለባህል፣ ለሐይማኖትና ለተፈጥሮ የሚገዛና ይህንንም እሴት

የሚያከብር ማህበረሰብ ሊኖር የሚገባ መሆኑን በኤጭ...! ልቦለድ ከቀረቡት አሉታዊ ችግሮች መገንዘብ እንችላለን፡፡

(ገጽ፣14) ላይ ይህንኑ ሃሳብ የሚያጠናክር ግለኝነት የሃጢያት ሸክም ማክበጃ በመሆኑ መጠንቀቅ እንደሚገባን ለማመላከት ቀጣዩ ሃሳብ ቀርቧል፡፡..."የሰው ልጅ ዕድሜ ከዘመን ዘመን እየቀነሰ የመጣው የሰው ልጅ ሃጢያት እየበዛ በመምጣቱ ነው፡፡ በ2929 ዓ.ም. የሰው ልጅ ትልቁ የእድሜ ጣሪያ 25 ዓመት ብቻ ይሆናል የሚል አወዛጋቢ ትንቢት አለ፡፡" "2929 ምንድነው?" ስትል እሌኒ አጎቷን ትጠይቃለች፡፡ "666 ዓለምን ሙሉ በሙሉ መግዛት የሚጀምርበት ነው" ሲል አጎቷ ይመልስላታል፡፡

በኤጭ...! ልቦለድ መጽሃፍ ውስጥ እንደታየው ለግላዊ ነጻነታቸው ብቻ ሲሰሩ የነበሩ ግለሰቦች ከራሳቸው ሕይወት አልፈው የሌሎችን ሕይወት ይጎዳሉ፡፡ የእሌኒ አባት አቶ ፍቅር አብርሃም በግል ነጻነት በማመን ገንዘብ ለማግኘት ሲል ብቻ ለጥንቁልና መንፈስ በማደር የገዛ ልጁን በ13 ዓመቷ ደፍሮ ዘግናኝ ድርጊት ፈጽሞባታል፡፡

የሌላኛዋ አባት አቶ ሽመክት እንዲሁ የገዛ ልጁን በጥንቁልና ተመርቶ በመድፈር ተደጋጋሚ ዝሙት ፈጽሟል፡፡ ሊሊ ሽመክት እንዲሁ በጥንቁልና ተይዛ ለምታገኘው የእርኩስ መንፈስ ሽልማት ስትል አንድ ሺ ባለትዳሮችን በዝሙት አርክሳ፣ ሶስት መቶ የሃይስኩል ተማሪዎችን በሌዚቢያኒዝም መንፈስ በክላ፣ ወላይታ ሶዶ ከተማ ላይ 50 ህጻናትን ሰርቃ ሕይወታቸው እንዲያልፍ አድርጋለች፡፡ ይህ ሁኔታ በግለሰቦች ነጻነት ሳቢያ የተፈጠረ አሉታዊ ጉዳት መሆኑንና መጽሃፉም ምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፋዊ ስልትን መሰረት አድርጎ መቅረቡን ለመረዳት እንችላለን፡፡

### 4.3.2. ወቅትን የተከተለ ዘመናዊነት /Modernization/

የዘመናዊነት ሃሳቦች በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂና በኢኮኖሚያዊ እድገት የሚገለጹበት ሒደት ነው፡፡ ይህም ሃሳብ በአብዛኛው "መዘመን ማለት እንደ ምዕራባውያን መሆን ማለት ነው የሚል አመለካከት አለው፡፡

በአጭ...! ልቦለድም እንዲህ አይነቱ እሳቤ ይስተዋላል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ አውሮፓውያን ስላደረጉ ብቻ ምንም ሳይገባን እኛም መልሰን የምናደርጋቸው ነገሮች በርካታ ናቸው፡፡ በኤጭ...! ልቦለድ (ገጽ፣67) ላይ አጎቷ ሶቅራጥስ የእሌኒን ወቅትን የተከተለ የልደት አከባበር አስመልክቶ ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ያለውን

ሁኔታ ለማመልከት "ስንት ሕዝብ በሚራብበት ሃገር ልደት ማክበር ግፍ ነው፡፡" ሲል ይገስጻታል፡፡

በኤጭ...! ልቦለድ ውስጥ አሉታዊ የሆነው የጥቁር አስማት ባህሪ በጸጉር ስራ በኩል የአስማንዲዮስን ትዳር የማናጋት መንፈስ አወል በተባለ ወጣት አማካኝነት ሲከወን ይታያል፡፡

> የጸጉር ባለሙያ ነኝ፡፡ ጸጉር ቤት የሚመጡ ትዳር ያላቸውን ሴቶች የአባታችን መንፈስ እንዲጋባባቸው እያደረኩ ነው፡፡ አሁን 820 ደርሻለሁ፡፡ በቅርቡ አንድ ሺ ሲሞላኝ ትልቁን ሽልማቱን ከአባታችን አስማንዲዮስ እቀበላለሁ (ገጽ፣105-106)፡፡

ወቅትን የተከተለው የሹርባ ስራ በርካቶችን በሰልፍ ከማጋፋት አልፎ የሚያመጣው ችግርና የሚያስከትለው ተጽዕኖ አይታሰብም፡፡ አሉታዊ የምትሃታዊ አውነታዊነት ማሳያ ሆኖ ብቅ ያለው ኤጭ...! ልቦለድ ወቅትን የተከተለ ዘመናዊነት ከጥቅሙ ባልተናነሰ ሁኔታ አሉታዊ ጉዳቱ ከፍተኛ መሆኑን ይጠቁመናል፡፡

በኤጭ...! ልቦለድ ወስጥ ሌላው አሉታዊ የጥቁር አስማት ባህሪ ማሳያ ሆኖ የቀረበው ወቅትን የተከተለ የንቅሳት መስፋፋት ጉዳይ ነው፡፡ በመጽሃፉ (ገጽ፣106) ንቅሳትን በአሉታዊ መንገድ የመጠቀም ተግባር ምን ያህል እንደተስፋፋ እንመለከታለን፡፡

"ሰውነትሽ ላይ ሶስት ቦታዎች ንቅሳት ይሰራልሻል፡፡ የአባታችን ተጨማሪ ሃይል በንቅሳቱ አማካኝነት ከደምሽ ጋር ይዋሃዳል፡፡ ከዚያ ተጨማሪ መነቃቃትና ጠላትን መዋጊያ ሃይል ጭምር ይሆንሻል ማለት ነው፡፡" ከዚህ ማሳያ ሃሳብ በተጨማሪ በመጽሃፉ ውስጥ የንቅሳትን አሉታዊ ጎን ለማሳየት (ገጽ፣107) ላይ ተከታዩ ሃሳብ ተጠቅሷል፡፡

"ለንቅሳት ከሚመጡት ተማሪዎች፣ ሴተኛ አዳሪዎች ውበትን ፈላጊ ሴቶች እና ወንዶች ምንም ነገር ሳያውቁና ሳይነገራቸው በንቅሳት አማካኝነት የአስማንዲዮስን መንፈስ እንደሚያጠልቅባቸው ነግሮኛል፡፡ አወል ከወሰደኝ ዘመናዊ ህንጻ ላይ የሚገኙ ወጣቶች አላማቸው ንቅሳት እየሰሩ ገንዘብ ማግኘት ሳይሆን ተመጣጣኝ ብር እያስከፈሉ የጋሼን መንፈስ ለማስረጽ ስራቸውን በይፋ በስመንቅሳት እየሰሩ ከሚገኙት Natic tattoos ንቅሳት ጨርሼ ወጣሁ፡፡"

ኤፍ...! ልቦለድ ወቅትን በተከተለ ዘመናዊነት ስንመራ ከላይ ከጠቀስናቸው ጉዳዮች በተጓዳኝ እንደ እንጉዳይ የፈሉት ማሳጅ ቤቶችም ተመሳሳይ የአሉታዊ ድርጊት መፈጸሚያ ስለመሆናቸው እንድንገነዘብ ያደርገናል፡፡

### 4.3.3. ዘመናዊ አስተሳሰብ /Modernism/

ይህ እሳቤ "የሰው ልጅ ቁሳዊ እድገት ስላመጣ፤ ከተማ ውስጥ ስለኖረ፤ እንዲሁም በሳይንስና ቴክኖሎጂ ስላደገ ብቻ ዘምኗል፣ ሰልጥኗል፣ አድጓል ማለት አንችልም የሚል እሳቤ የሚያራምዱ ናቸው፡፡ አሉታዊ የምትሃታዊ እውነታዊነት ትረካ ማሳያ የሆነው ኤፍ...! ልቦለድ ዘመናዊ አስተሳሰብ ማለት አሉታዊ በሆነ መንገድ ሕዝብና ሀገርን ከሚጎዳ ተግባር በመራቅ ሰብአዊነትን ተላብሶ መልካም ዜጋ በመሆን የሚገለጥ መሆኑን ያስረዳናል፡፡

> አስራ አምስት ዓመት ሞላሽ! ሀገርሽን ኢትዮጵያን ለማገልገል እየቀረብሽ ነው፡፡ አየሽ የእኔ ልጅ እድሜሽ በጨመረ ቁጥር ትልቅ ሃላፊነት እንደሚጠበቅብሽ እየተሰማሽ መምጣት አለበት! ሀገርሽ ኢትዮጵያ አንቺንም እውቀትሽንም ትፈልጋለች! አምላክሽ ትልቅ እውቀትና ማስተዋል የሰጠሽ እንዲሁ በዋዛ አይደለም፡፡ ለሀገርሽ ኢትዮጵያ አንዳች ነገር እንድትሰሪበት ነው (ገጽ፣67)፡፡

ኤፍ...! ልቦለድ አሉታዊ ከሆነ ድርጊት በመራቅ ልጆች የሚፈለገውን ሰብአዊነት እንዲላበሱ ገና ከመነሻው ውስጣቸውን ብሩህ ማድረግ እንደሚገባ ያስረዳናል፡፡

ከዚህ ባለፈ ሊሊ የአስማንዲዮስን መንፈስ ለማሰራጨት ስትንቀሳቀስ የገጠማት ወጣት ዝም ብሎ ወደ ወጥመዷ ሲገባ አይታይም፡፡ በመጽሃፉ ውስጥ ይህን አሉታዊ ችግር ለመቋቋም በሚደረግ ትንቅንቅ ውስጥ እራስን አውቆ በጽናት መቆም የዘመናዊ አስተሳሰብ ባለቤት እንደሚያደርግ ከወጣቱ ጠንካራ ምላሽ መረዳት እንችላለን፡፡

"የእኔ እህት ውስጥሽ ያለውን አንዳች አጉል መንፈስ ተረድቼዋለሁ፡፡ ወንዶችን በዝሙት መንፈስ ለመጣል ወጥመድ እየዘረጋሽ እንደሆነ ውስጤ ያለው የሰላም አለቃ መንፈስ ይነግረኛል፡፡ እኔ ከሃጢያት መንደር እርቄያለሁ" (ገፅ፤129)፡፡

ዘመናዊ አስተሳሰብ በሌሎች ወጥመድ ውስጥ በመግባት እራስንም ሆነ ሌላውን በሚጎዳ ተግባር መሳተፍ ማለት አይደለም፡፡ በዘመናችን የሚታዩት የማንነት ቀውስ ችግሮች ዘመናዊነት ነው ብለን በጅምላ የምንከተላቸው እንጂ በዘመናዊ አስተሳሰብ

የምንጠቀምባቸው አይደሉም፡፡ በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ የንቅሳት፣ የማሳጅ ቤቶች፣ የጸጉር ስራ እና ልቅ የሆነ የወሲብ ግንኙነት በዘመናዊነት ስሜት ተመሳስለን የምንነዳባቸው እንጂ በዘመናዊ አስተሳሰብ ተመርተን በምክንያት የምንመራባቸው ሲሆኑ አይታይም ይህ ደግሞ የዘመናዊነት አስተሳሰብ መገለጫ አለመሆኑን እንረዳለን፡፡

## 4.5. የምትሃታዊ እውነታዊነት ጭብጥ ለልቦለድ ያለው አስተዋጽኦ

### 4.5.1. ማህበረሰባዊ ችግሮችን ነቅሶ ለማሳየት ይረዳል

ከሰው ልጆች ሕይወት ተቀድቶ መልሶ ለሰው ልጆች የሚቀርበው ስነጽሁፍ ማህበራዊ ህጸጾችን፣ ባህላዊ ወግና ስርአቶችን፣ ማንነትን፣ እንዲሁም የኋላ ታሪክን በማመልከት፣ በማሳወቅና በማስተማር ረገድ የላቀ ሚና ያለው ነው፡፡

ኤጭ…! ልቦለድ በምትሃታዊ እውነታዊነት አሉታዊ ጎን በጥቁር አስማት አማካኝነት እየደረሱ ያሉ ማህበረሰባዊ ቀውሶችን በተለያዩ አስረጂዎች አቀርቦልናል፡፡ በምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፋዊ ስልት የቀረበው ኤጭ…! ልቦለድ ከዘመን መንፈስ ጋር ተያይዞ የሰው ልጆች ከፈጣሪ ልዕልና አፈንግጠው ለእኔ ብቻ በሚል ስግብግብነት ሳቢያ ለሰብአዊ ቀውስ መጋለጣቸውን በማመልከት ቆም ብለን እራሳችንን እንድንመለከት ያደርገናል፡፡

ኤጭ…! ልቦለድ ባልተለመደ መልኩ በምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ የቀረበ መሆኑ በምትሃት ምክንያት እየደረሰ ያለውን ግለሰባዊ፣ አካባቢያዊና ሀገራዊ ችግር በግልጽ እንድንረዳ በማድረግ ረገድ ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑን እንድንገነዘብ አድርጎናል፡፡

### 4.5.2. የአፃፃፍ ስልት ልዩነት ለማምጣት ያገለግላል

በሀገራችን የስነጽሁፍ እድገት ውስጥ የምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፍ ስልት በቅርብ ጊዜያት ከሚታዩ አንዳንድ ምትሃታዊ እውነታዊነትን መሰረት አድርገው ከሚቀርቡ ስራዎች ባሻገር በስፋት ትኩረት አግኝቶ የተሰራበት ዘርፍ አይደለም፡፡ በተለይም በምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፍ ስልት አሉታዊ የአስማት ክዋኔዎች ላይ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ የስነጽሁፍ ውጤቶችን አዘውትሮ ማየት የተለመደ አይደለም፡፡

ኤጭ…! ልቦለድ በእውነተኛ ጭብጥ ላይ ተመስርቶ በአዲስ መልክ የምትሃትን አሉታዊ ጉዳይ ያስነበበ በመሆኑ በሌሎች ጸሃፊያን ዘንድ የአጻጻፍ ስልት በመፍጠር በተመሳሳይ መንገድ ለሚዘጋጁ የድርሰት ስራዎች የአጻጻፍ ስልት ማሳያ በመሆን ያገለግላል፡፡

እንደ ኤጭ…! ልቦለድ አይነት ስራዎች ተበራክተው ቢቀርቡ በተመሳሳይ ስልት ለሚዘጋጁ የስነጽሁፍ ውጤቶች እንዲበራከቱና እንዲለመዱ በማድረግ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚስተዋሉና ይፋ የማይወጡ ችግሮችን ነቅሶ በማሳየት የአጻጻፍ ስልት ልዩነት ለመፍጠር ያስችላሉ፡፡  ኤጭ…! ልቦለድ ብዙም ባልተለመደው በዚሁ ስልት ተጽፎ መነበቡ ሌሎች መሰል ስራዎች እንዲበራከቱ ከማድረግ ባለፈ በዘልማድ በወሬ ብቻ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚነገሩ ድብቅ ችግሮችን በማሳየት ጥንቃቄ እንድናደርግ ለማስገንዘብ ያገለግላል፡፡

## 4.6. የኤጭ…! ልቦለድ አውዳዊ ፍቺ

በኤጭ…! ልቦለድ ውስጥ ምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግን መሰረት በማድረግ አስማት በጥንቁልና ሰበብ ያደረሳቸው ማህበረሰባዊ ቀውሶች በግልጽ በመጠቆም ዛሬ ላይ ጥንቃቄ የማናደርግ ከሆነ መጪው ጊዜ እጅግ ፈታኝ ከመሆን አልፎ የሰው ልጅ ሕይወት አደጋ የተጋረጠበት መሆኑን በአውዱ ያመለክተናል፡፡

እነሆ በዚህ ወቅት በበርካቶች ዘንድ የሚታየው የትዳር መፍረስ፣ የህጻናት ስርቆት መባባስ፣ የንቅሳትና የማሳጅ ቤቶች ስውር ተልዕኮ በቀጣዮቹ ጊዜያቶች እጅግ የምንፈተንባቸው መሆኑን ከኤጭ…! ልቦለድ  አውድ አንጻር እንድንረዳ ያደርገናል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ እና አስተያየት

### 5.1. ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ ገድልና አፈታሪክን መነሻ በማድረግ ከግዕዝ ወደ ዘመናዊ የአማርኛ ስነ ጽሁፍ በመሸጋገር ወቅትን ተከትሎ ዘውዳዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን እያጠነጠነ ዘመናትን በፈጀ ጉዞው እዚህ ደርሷል፡፡ በዚሁ መነሻነት የቀደሙ የስነጽሁፍ ውጤቶች በምናብ የገዘፉ፤ ወደ አፈታሪክነት የሚያደሉ፤ ሞራላዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን የሚያትቱ ሆነው መታየታቸው በቀደመው የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ ታሪክ ውስጥ የምትሃታዊ እውነታዊነት ንድፈ ሃሳብ ስነጽሁፋዊ እሳቤ ጭራሹን የለም እንዳንል ያደርገናል፡፡

በኢትዮጵያ ስነጽሁፍ ውስጥ ምትሃታዊ እውነታዊነት ንድፈ ሃሳብ ቀደም ባለው ጊዜ ቢስተዋልም በዚህ ዘርፍ ግን ጠለቅ ያለ ጥናትና ምርምር ባለመካሄዱ በዘርፉ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በስነጽሁፍ ውጤቶች አማካኝነት መመልከት አዳጋች ሆኖ ቆይቷል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ክቡር ድንጋይ፣ የኦጋዴን ድመቶችና ኤጭ…! ልቦለድ የምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፍ ስልት ተከትለው የጭብጥ ማጠንጠኛ ሆነው መቅረባቸው ዘርፉ ትኩረት እያገኘ መምጣቱን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡

በምትሃታዊ እውነታዊነት አሉታዊ የስነጽሁፍ ጭብጥ አማካኝነት ኤጭ…! ልቦለድ የጥቁር አስማት ፈርጅ የሆነው ጥንቆላ ያደረሰውን ሀገራዊ ቀውስ በአዲስ የአጻጻፍ ስልት አስነብቦናል፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረት ኤጭ…! ልቦለድ በምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ ተዘጋጅቶ መቅረቡን ማመልከት ነው፡፡ ጥናቱ የምትሃታዊ እውነታዊነት ስነጽሁፋዊ ጅማሮ ምን ይመስላል?" ምትሃት ምንድነው?" የምትሃት ወይም የአስማት ክፍሎች የትኞቹ ናቸው? የአስማት ክፍሎች ትርጓሜ እንዴት ይገለጻል? የምትሃታዊ እውነታዊነት አቀራረብ ስነጽሁፋዊ አበርክቶ ምንድነው? የምትሃታዊ እውነታዊነት ንድፈ ሃሳብ፣ ጽንሰ ሃሳብና ባህርያት የትኞቹ ናቸው? የሚሉ ጥያቄዎችና መሰረት አድርጎ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

ይህ ጥናት የምትሃታዊ እውነታዊነትን ዘውግ  ያቀረበ በመሆኑ በተመሳሳይ ጥናት ለሚሳተፉ እንደ መነሻ ሃሳብ በመሆኑ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 5.2. አስተያየት

በዚህ ጥናት ኤጭ…! ልቦለድ የምትሃታዊ እውነታዊነት ጥቁር አስማት ባህርያትን በሚያሳይ መልኩ ምን ያህል ተሟልቶ ቀርቧል? መጽሃፉ ምን ያህል የጥቁር አስማት ባህርያትን ተላብሷል? የሚሉና የምትሃታዊ እውነታዊነት አሉታዊ የስነጽሁፍ ስልትን መጠቀም ለስነጽሁፍ እድገት የሚኖረው ጠቀሜታ ምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎች በትንታኔ ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

በኤጭ…! ልቦለድ መጽሃፍ እንደታየው ጥቁር አስማት እያደረሰ ያለውን ማህበረሰባዊ ቀውስ ትኩረት አድርገው ለሚጽፉ ደራሲያን በተመሳሳይ መንገድ ስራዎቻቸውን እንዲያቀርቡ እና ማህበረሰባዊ ችግሮችን በመንቀስ መልሰው ለማህበረሰቡ እንዲያቀርቡ ያስችላል፡፡ በጥንቁልና ሳቢያ እየደረሱ ያሉ ሀገራዊ ችግሮችን በትኩረት በመመልከት በምትሃታዊ እውነታዊነት ዘውግ ላይ ጥልቅ ጥናት ቢካሄድ በዘርፉ ለሚኖረው የስነጽሁፍ እድገት  ፋይዳ እንደሚኖረው መረዳት ይቻላል፡፡

# ዋቢ ጽሁፎች


መዝገቧ ታደሰ፡፡ (2012)፡፡ *የምትሃታዊ እውነታ ንጽጽራዊ ጥናት፡፡* one hundered Years of solitude and the famished road. አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ያልታተመ)

ማዕበል ፈጠነ፡፡ (2011)፡፡ *ሐሸማል፡፡* ግራፊክስ ማተሚያ ቤት፡፡

ሰለሞን ተሾመ፡፡ (2007)፡፡ *ፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ ትኩረት አቅጣጫ፡፡* አዲስ አበባ፡፡ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኀላ. የተ. የግ. ማ፡፡

በእናትላይ አየነው፡፡ (2010)፡፡ የምትሃታዊ እውነታ መገለጫዎች በተመረጡ ልቦለዶች በክቡር ድንጋይና ኦጋዴን ድመቶች፡፡ (ያልታተመ ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት)፡፡ ባህር ዳር፣ ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ፡፡

ባህሩ ዘርጋው፡፡ (2004)፡፡ *ዘርጋው ከፍተኛ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* ሮሆቦት አሳታሚዎች፡፡

ተስፋ በላይነህ፡፡ (2013)፡፡ *የይስማከ በአስማት የተሞላው ክቡር ድንጋይ* www. Adis Admass news com. Julay 13 ያልታተመ፡፡

ታደለ ገድሌ፡፡ (2017)፡፡ electronics var መላዕከ ሞትን ለሰባት ዓመታት ገዝቶ ያቆመ ባለቅኔ፡፡ አዲስ አድማስ ጋዜጣ፡፡ www. Adiss admass news. Com.

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ (2001)፡፡ *በይነ ዲስፒሊናዊ የስነ ጹሁፍ ንባብ፡፡* አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፡፡ commercial prenting Press.

አሌክስ አብርሃም፡፡ (2013)፡፡ *ከዕለታት ግማሽ ቀን፡፡* ፋር ኢስት ትሬዲንግ ማተሚያ ቤት፡፡

አባይነህ አስፋው፡፡ (2012)፡፡ *መጽሃፈ ሔኖክ፡፡* ትንሳኤ ማተሚያ ድርጅት፡፡

አቤኔዘር ታዬ፡፡ 2012፡፡ *የምትሃታዊ እውነታ መገለጫዎች በኦጋዴን*

*ድመቶች መጽሃፍ፡፡* ጂማ ዩኒቨርስቲ፡፡ (*ያልታተመ*)

አለማየሁ ዋሴ፡፡ (2007)፡፡ *እመጓ*፡፡ ኢስት ትሬዲንግ ማተሚያ ቤት፡፡

------------------፡፡ (2008)፡፡ *ዝጎራ*፡፡ ኢስት ትሬዲንግ ማተሚያ ቤት፡፡

-----------------፡፡ (2010)፡፡ *መርበብት*፡፡ ኢስት ትሬዲንግ ማተሚያ ቤት፡፡

አለማየሁ ገላጋይ፡፡ (2012)፡፡ *ሀሰተኛው በእምነት ስም፡፡* ትንሳኤ ማተሚያ ቤት፡፡

አዘርግ፡፡ (2010)፡፡ *ኤጭ…! ፡፡* አዲስ አበባ፡፡ ፋር ኢስት ትሬዲንግ ማተሚያ ቤት፡

እስጢፋኖስ አበራ፡፡ (2006)፡፡ *ውስጥ አዋቂ ከአዲስ አበባ ጓዳ እስከ አደባባይ፡፡*

ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማህበር፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ (1992)፡፡ *የስነጹሁፍ መሰረታዊያን፡፡* አዲስ አበባ፡፡ ኢትዮጵያ፡፡

የብሉይና አዲስ ኪዳን መፅሃፍት፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ዮናስ አድማሱ፡፡ (1992)፡፡ *"አስረኛንኩዋ?"* ሀዲስ አለማየሁና ማህበራዊ

ሂስ ስልታቸው፡፡የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ መጽሄት፣ ቁ 10፡፡

ይስማከ ወርቁ፡፡ (2005)፡፡ *ክቡር ድንጋይ፡፡* አዲስ አበባ፣ ዴርቶጋዳ ማተሚያ ቤት፡፡

------------------፡፡ (2009)፡፡ *የኦጋዴን ድመቶች፡፡* አዲስ አበባ፣ ዴርቶጋዳ

ማተሚያ ቤት፡፡

ፀደይ ወንድሙ፡፡ (2007)፡፡ *ብሌን፣ ቅጽ ቁ. 1፡፡* አክሊፕስ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ግርማ ወንድሙ፡፡ (2006)፡፡ በማለዳ መያዝ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

Abrhams, M.H. (1971) A Glossery of literary terms, Delhi: Macmillan

India Ltd,

Aldea, Eva (2011) Magical realism and Deluze, London; Continumm.

Allen, W. (1985). *The Purple Rose of Cairo.*

Alejio Carpenter (1960) realism magico. The kingedom of this world.

Allmann Emma. "*What is magical realism?*" bookiot.com.Retrived
21 July 2020.

Ashcroft, B. Griffiths. G. Tiffin, H (2002). *The Empire writers Back; Theory and Practice in post colonial literature.* London and New work Routledge.

Angel Flores (1955) magical realism in Spanish American Fiction.

Borges, J. (1935). *History of universal information*.

Bowers, A. Maggie (2004) *Magical realism:* the new critical Idiom. Londone And New work: Routledge.

Bontompelli, Massimo (1974) Lavvetura novecentistia. Flornce, Italy: Vallecch.

Braziller, G. (1979) *Ethiopia magic scrolls; new work.*
21 Julay 2020.

Eliade, Mircea. (1959) The secred and the Performance. Trans, willian Weaver, London ventage.

Elkins (1959) selavery was an invitation to American and berazilian selavery.

Faris B.Wendy (2004) ordenery Enchantmentes magical realism and the Ramystification of narrative. Nashavalle: Vanderbilt university perss.

Hegerfeldt, Anne (2005) C. lies that tell the truth: Majic realism senn through Contomprary fiction from Britain.

Horkheimer (1937) Tradtonal and critical theory. Britanica.

*https://www.google.com ስለ ጠልሰምና አስማት*

*https//m facebook,com/Zarayaqobe 2008.*

Joice (2002) A proteriait of artist as ayoung man, after the race movement Stayle Modernism.

Potter, H. (1750) *a magic history in Ethiopia.*

Pratchet (1986) The coloure of magic. England.

Marquez, G.G. (1967) *one hundered years of solitude*.

Mattew Stercher (1999) *magic realism* is brodely dicriptive rather than Critically regorios.

Melakeneh Mengistu (2010) *Post colonialism and mainsterim Anglophone*, African novel Themantic and staylitic Intertextuality.

Mezgebua Taddesse (2012). A comparative study of Magical realism in one Handered years of solitude and the famished road. (Unpublished M.A. Thesis). Addis Abeba University.

Roh, Franz (1925) magical realism post expernessionism.

Rushed Salman (1992) Gabriel Garcia Marquze; Imagenery Homlands Londen

Kundera, M._ *the unbearable ligness of Being.*

Kusturica, E. (1988) *Time of the Gypsies.*

Warnes, C. (2009) *Magical realism and the post colonial novel.*

Shultz Chiristopher. "*How is magical realism different from Fantasy?"*

Julay 2020.

Sleman, Stephen magical realism as post colonialism discourse.

Taye Assefa and Shiferaw, (2000). *The study of institute of Ethiopia studies,*

Tonie Morison (2019) The source of self regared.

Vol. 33, No.2, special issue dedicted to the xiv the

Iinternational conference

Of Ethiopian studies (November 2000), pp.27%73.

Wolfe Thomas (1935) From death to morning.

Spindlers, W. *magic realism a typology.*

Zamora, L. (1995) *magical realism theory history community*.

Zamora, P. Lois and Faris, B Wendy (Eds) (1995) Magrical realism: Theory

History, community, Drham Nc and London: Duke University press.

© 2021 shmoop university inc.

www. Encarta (2009.